# ክፍል ስምንት

## የመነጠቅ ዓላማዎች

ቀደም ባሉት ዐቢይና ንዑሳን ርዕሶች ስለመነጠቅ በዛ ያሉ ሐሳቦች ተመልክተናል። ለቀረቡት እውነቶች ከጥቂት ሐሳቦች በስተቀር መሠረቱ ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የመነጠቅ አቃጅና ፈጻሚ ባለቤ እግዚአብሄር ነው። ጌታ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩ መነጠቅን ለምን አዘጋጀ? ይህስ ስርዓት እንዲኖር ለምን ፈለገ? የእነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በሚቀጥሉት ዝርዝር ሃሳቦችና የመጽሐፍ ቅዱ ጥቅሶች እንመለከታለን።

### 8.1. ቅዱሳንን በእግዚአብሔር ፊት ለማቅረብ

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ህልውናው ወይም ማንነቱ ፈጽ ከኃጢአት ጋር በተያያዘ አይነቀፍም። ማንም ሊቀርበው በማይችል ድን ብርሃን ይኖራል። አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያየው አይችልም ።1ኛጢሞ 6:16። ሐዋርያው ጳውሎስም በኤፌሶን 5:27 ውስጥ: «ዕድፈት ወይም የፊ መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆ ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» በማለ ስለ መነጠቅ ገልጾአል። በነዚህ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር አብ ፊ ለመቅረብ የሚቻለው የክርስቶስ ኢየሱስን አካል የሚመስል በመልበስ ብ ነው። ይህንንም ደግሞ ማከናወን የሚቻለው ሞትን ድል አድርጐ የተነሳው ጌታ ኢየሱስን በማመን ብቻ ነው። በተጨማሪም በ1ኛተሰ. 3:13፤ይሁዳ 2 ላይ ስናነብብ በአምላካችንና በአባታችን ፊት እንደምንቀርብ ተገልጿል። ይህ የሚፈጸመው እግዚአብሔር ባዘጋጀው የመነጠቅ ስርዓት ብቻ ሲታሰፍ ነው።



### 8.2. ያንቀላፉትን ቅዱሳን ከኃጢአተኞች ሙታን መካከል ለመለየት

ለረዥም ዘመናት የጌታ ኢየሱስ አዳኝነት ተመስክሮላቸው ጌታን አምነውና እንደ አዳኛቸው ተቀብለው፤ ከሥጋ የተለዩ (የሞቱ) ወይም ያንቀላፉና በመቃብር ያሉ ቅዱሳን ብዙ ናቸው። እነዚህ ቅዱሳን እንደሌላው ሰው ተቀብረዋል። ሆኖም የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ከኃጢአተኞች ሙታን መካከል ይነሱና ይነጠቃሉ። በእነዚህ ቅዱሳንና በኃጢአተኞች ትንሳኤ መካከል ቢበዛ የአንድ ሺህ ዓመታት ልዩነት ይኖራል። እግዚአብሔር ይህንን የመነጠቅ ስርዓት ያዘጋጀው በቅዱሳን ማንቀላፋትና በኃጢአተኞች መካከል ልዩነት መኖሩን ለማሳወቅም ነው። የመነጠቅ ስርዓት ካልሆነ የሁለቱ ሙታን ሁኔታ ልዩነቱ ጐልቶ አይታይም። ይህንን ሃሣብ በደንብ ለመረዳት 1ኛተሰ. 4:14፤ ራዕይ 20:4-6፤ 1ኛቆሮ. 15:20-23 ይመልከቱ። እነዚህ ጥቅሶች የሙታን ትንሳኤ ለህይወትና ለፍርድ ቀደም ተከተል እንዳለው ይገልጻሉ።

### 8.3. ቅዱሳንን ወደ አዘጋጀላቸው ስፍራ ለመውሰድ

በ1ኛተሰ. 4:17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ..እንነጠቃለን... ብሏል። መነጠቅ ካለ የግድ ማረፊያ (መድረሻ) ደግሞ ይኖራል። ይህም መድረሻ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ.14:1-3 ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው መንፈስ አዳሽና ታላቅ ተስፋ ነው። በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ...ስፍራን አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና... ሲል ወደዚያ ወዳዘጋጀው ስፍራ ቅዱሳኑን የሚወስደው ..በመነጠቅ.. ሥርዐት ውስጥ በማሳለፍ ነው። እውነተኛዎቹ አማኞች ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ በመነጠቅ ይቀርባሉ፤ ይሄዳሉ ኤፌ. 5:27። በሰማያዊ ስፍራ እግዚአብሔር በልጁ በጌታ ኢየሱስ በኩል ወዳዘጋጀው ቦታ መድረስ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ መነጠቅ ነው።ከዚህ ውጪ የተሰጠ ተስፋ የለም።

## 8.4. የቅዱሳንን አካል ወደማይሞት አካል ለመለወጥ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በ1ኛቆሮ. 15:35-57 ስንመለከት ስለ ፍጥረታት ልዩ ልዩ አካል ይናገራል:: ስለ በራሪ ወፎች አካል፣ በባህር ስለሚኖሩ አሶች አካል፣ ስለ እንስሳት አካልና፣ ስለምድራዊ ሰው አካል ስለ ሰማያዊ፣ ስለ በሰባሽ፣ ስለ ፍጥረታዊና መንፈሳዊ አካልም በዝርዝር ገልጾ ጽፏል:: ቁጥር 40 ላይ ስለ ሰማያዊና ምድራዊ አካል ክብር ልዩነት ያመለክታል:: ሰማያዊ አካል ሲል አሁን በገነት ..በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ.. ያሉት የሰው መንፈሶች በትንሳኤ ጊዜ ሊለብሱት ስላለው አካል ነው:: ይህ አካል የሚለበሰው በሰማያዊ ስፍራ ሄደን ነው:: ይህንንም የማይሞት፣ የማይፈርስና፣ የማይጠፋ አካል ለመልበስ አሁን ያሉት ቅዱሳን በቅጽበተ ዓይን መለወጥና ያንቀላፉትም አማኞች መነሳት ይኖርባቸዋል:: ይህ ቅዱሳን የሚለብሱት መንፈሳዊ አካል ጌታ ኢየሱስ ከትንሳኤ በኋላ የለበሰውን ይመስላል:: «እርሱም ሁሉን እንኳን ሰራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል» ፊልጵ.3:21:: ልክ መነጠቁ ከመሆኑ በፊት ወይም ልክ በሚሆንበት ጊዜ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ሰውነታችን ይለወጣል::

## 8.5. ቅዱሳንን በመንፈስ፣ በነፍስና በሥጋ ፍጹማን ለማድረግ

በዚህ ክፍል የተጠቀሰው የመነጠቅ ምክንያት በተራ ቁጥር 4 ከተጠቀሰው ጋር የሚገናኘው በሥጋ መለወጥ አኳያ ነው:: ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ግን እግዚአብሔር የመነጠቅን ሥርዓት እንዲኖር የፈለገበት ሌላኛው ምክንያት ስለ ሰው ነፍስ ወደ ፍጹምነት ደረጃ መድረስም ጭምር ነው:: አስቀድሞ ሲፈጠር የሰው መንፈስ ፍጹም ነበረ:: ለኃጢአትም ሆነ ለሞት እንዲሁም ለዲያብሎስ ተገዝቶ አያውቅም ነበር:: ከውድቀት በኋላ ግን ለክፋት ኃይላት በተለያዩ ሁኔታዎች ተገዢ ሲሆን በዚያም ዲያብሎስን ሲከተል ሰው ልጅነቱ በቀጥታ ለሰይጣን ሆኖአል:: ይህም መንፈሳዊ ሞት ተብሎአል:: በአማኝም ህይወት ይህ የመንፈስ ሞትና የትንሳኤ ህግ



ሊሰለጥንበት ችሎአል:: ለምሳሌ በ2ቆሮ. 7:1 ላይ ...ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ.. ሲል፤ የሰው መንፈስ እንደ ምሳሌ 25:28 ካልተጠበቀ ሊረክስ እንደሚችል ከረከሰም ሞት ሊሰለጥንበት እንደሚችል በግልጥ ያሳየናል::

ቅዱሳን ከተነጠቁ በኋላ በሙሉ ማንነታቸው (በሦስትነታቸው ወይም በሁለትነታቸው) ፍጹም ይቀደሣሉ:: በሰማይ ፍርድ ይኖራል:: ይህ ፍርድ አማኙን ወደ ዘላለም እሳት (ሞት) የሚወስደው ሳይሆን የተወሰነውን ሽልማት እንዳያገኝ የሚያደርገው ነው:: በዚህ ፍርድ ሰዎች ማንነታቸውን የቀድሞ ህይወታቸውን ጉድለትና የእግዚአብሔርን ፀጋ ካዩ በኋላ በመንፈስ በነፍሳቸውና በስጋቸው በዘላለም ቅድስና ይታተማሉ:: ለምሳሌ በ1ኛተሰ. 5:23 ላይ «የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፡ መንፈሳችሁም፡ ነፍሳችሁም፡ ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ:: ፊልጵ. 3:21:: ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ወደ ተለወጠ ደረጃ የምትደርሰው ከመነጠቅ ጊዜ ጀምሮ ነው::

## 8.6. ቅዱሳን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሽልማትን እንዲቀበሉ

ከመነጠቅ በኋላ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 14:1-3 እንደተናገረው ቅዱሳንን ወዳዘጋጀው ቦታ በመውሰድ ያኖራቸዋል:: በኢየሩሳሌም (በተዘጋጀው ስፍራ) ደርሰው መኖር ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ በምድር ስለ ሰራው ነገር ፍርድ በጌታ ኢየሱስ ይሰጣል:: ይህ ፍርድ ሽልማት የሚያስገኝ ወይም የማያስገኝ ይሆናል የሕይወትን አክሊል የሚያሳጣ ፈጽሞ አይሆንም:: ዮሐ. 14:1-3፣ 2ኛቆሮ. 5:10፣ ራዕይ 19:1-10፣ ሮሜ 14:10፣1ኛቆሮ. 3:11-15::

## 8.7. ቤተ ክርስቲያንን ከታላቁ መከራ ለማዳን

በመጨረሻው ዘመን ከሚከሰቱ ታላላቅ አስፈሪ ትዕይንቶች ውስጥ አንደኛው በ70ኛው ሱባኤ የሚገለጸው ታናሹና ታላቁ መከራ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅዱሳን ከዚህ መከራ ሊያመልጡ እንደሚችሉና

የሚያመልጡበትም መንገድ ምን እንደሆነ ተገልጧል:: በራዕይ መጽሐፍ ከምዕራፍ 6-19 ስንመለከት በዚህ መከራ ዘመን በኃጢአተኛው ዓለም ላይ የሚወርደውን የቁጣ (የመቅሰፍት) ዓይነቶች በዝርዝር እናገኛለን:: የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በዚህ ውስጥ እንዲያልፉ እግዚአብሔር አልፈቀደም:: ሆኖም ግን የመከራው ዘመን እውነተኛ አማኞች(የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) በመስዋዕትነት በዚህ መከራ እንደሚያልፉ ከራዕይ 6:9-11፣ 13:7-10 እና 20:4 መረዳት ይቻላል:: በሉቃስ 21 ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ስላሰው ልዩ ልዩ መቅሰፍት ከተናገረ በኋላ ቁጥር 36 ላይ ግን ..ከዚህ ሁሉ.. ለማምለጥ መፍትሔው በፀሎት መትጋት እንደሆነም አስተምሯል:: ..ከዚህ ሁሉ.. ሲል በ በማቴ. 24: ሉቃ. 21ና ራዕይ 6-19 የተጠቀሱትን መቅሰፍቶች ማለቱ ነው:: በተጨማሪም 1ኛተሰ. 5:9 «እግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቁጣ ወስኖ አላስቀመጠንም» የሚል ተጽፎ እናነብባለን:: እግዚአብሔር ኖህንና ሎጥን ከቁጣ ሰውሮ እንደ አዳነ በዚህ ዘመን መጨረሻም በመነጠቅ ቤተ ክርስቲያንን ያድናል:: በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚሆነው ከመከራው በፊት ነው:: እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ከመከራው ለማዳን የመነጠቅን ሥርዓት አዘጋጅቷል:: መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን ሲነገር ግን መከራውን የፈሩ ቅዱሳን ጩኸት እንደሆነ ሲተረጐም ፈጽሞ አይገባም::

## 8.8. ቅዱሳን በበጉ ሠርግ ተካፋይ እንዲሆኑ ለማድረግ

የዘመናት ቅዱሳን ተካፋይ የሚሆኑበት መንፈሳዊና ሰማያዊ ሠርግ ለሺህ ዓመት ሥርዓት ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳን ወደ ምድር ከመመለሳቸው በፊት ይሆናል:: ራዕይ 19:7-8:: ይህ ሠርግ የሚሆነው ወደ 70ኛው ሱባኤ (የመከራው ዘመን) ማብቂያ ላይ ነው:: በራዕይ 22:11 ላይ ዓመጸኛው እንዲያምጽ ጻድቁም ጽድቅ እንዲያደርግ ሲፈቀድ ሊከፈለውም ካለው ዋጋ ጋር ተነጻጽሮ ነው:: ዋጋውም ለሁሉ እንደሥራው ይሆናል:: ከዋጋዎቹ አንዱ በ2ኛተሰ. 1:6-7 ተጠቅሷል:: መልካም ላደረጉ ሽልማት ሲሆን ክፉ



ረጉ ደግሞ ቅጣት ይሆናል:: ዮሐ.5: 28-29:: ቅዱሳንን መከራ ያሳዩ ሁሉ
ቱ ዓመታት መከራ ሲቀበሉ በሰማይ ደግሞ እግዚአብሔር ለልጆቹ ሠርግ
ርጋል:: ይህ ሠርግ በዓይነቱ ልዩ ነው:: ልዩም የሚያደርገው ብዙ
ርያት ስላሉት ነው:: ይኸውም 1. እግዚአብሔር የተመሰገነበት 2.
ላቆችና ታናናሾች አምላክን እንዲያመሰግኑ ጥሪ የተደረገበት 3. በራዕይ
5 የተጠቀሱት ምናልባትም 24ቱ ሽማግሌዎች: 4ቱ እንስሳት: በቅድመ
ከራና መንፈቀ መከራ (ከታላቁ መከራ) በክርስቶስ ደም ተዋጅተው በዙፋኑ
ያ የተገኙት ታላቅ ሕዝብና ቅዱሳን መላዕክትም ጭምር ደስ የተሰኙበት
ሆነ 4. ተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሱት ሁሉም ሐሴት ያደረጉበትና 5.
ታችንና ከአምላካችን መንገስ ጋር የተያያዘ በመሆኑና 6. ክብር ለጌታ
ዲቀርብ ጥያቄ የቀረበበት ትዕይንት በመሆኑ ነው:: ሬዕይ 19: 7-10::
ህ ሠርግ ግን ተካፋይ ለመሆን የግድ በመነጠቅ ውስጥ ማለፍ
ፈልጋል::

## . ሐሰተኛው ክርስቶስ (የአመጽ ሰው) እንዲመጣ በር ለመክፈት

በ2ኛተሰ. 2:7 እና በ1ኛዮሐ. 4:3 የሐሰተኛው ክርስቶስ ወይም
ርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ በዓለም እንዳለና በግልጽ እንዳይሰራ አደናቃፊ
ደተደረገበት ተገልጿል:: እስካሁን ድረስ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ
ራውን እያካሄደ ያለው በሚስጢር ነው:: ይህንንም ያደረገበት ምክንያት
ካይ ስላለ ነው:: ከልካዩም ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን
:: መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን በምድር መኖሩን በክፍል ስድስት
ራርቷል:: ስለዚህ የዓመጽ ሰው በግልጽ እንዳይሰራ ከብዙ ዓመታት
ሮ የሚከለክለው ..የክርስቶስ አካል.. ነው:: በማቴ. 16:18 ላይ
ንደተገለጸው ክርስቶስ ኢየሱስ ታላቅ ተጋድሎን ያቆመው በገሃነም ደጆችና
ቤተ ክርስቲያን መካከል ነው:: ለዚህም ተጋድሎ በሐሥ. 1:8 እና 2:1-4፣
እንደምናነበው ኃይል ሰጪው መንፈስ ቅዱስ ነው:: በ2ኛተሰ. 2:6-7
ንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን (የክርስቶስ አካል) ስትነጠቅ ሐሰተኛው
ርስቶስ በር ስለሚከፈትለት ሥራውን በግልጽ ያከናውናል:: እስከአሁን

በተመለከትናቸው የመነጠቅ ዓላማዎች ውስጥ ዘጠኝ ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ተመልክተናል:: እግዚአብሔር ማንኛውንም ሥራውን የሚፈጽመው በዕቅድ ነው:: ዕቅዱንም በራሱ አሰራር ይፈጽመዋል:: ጌታ ያዘጋጃቸውን የመነጠቅ ዓላማዎች በዝርዝር ስንመረምራቸው በሙሉ በሰው ህይወት ላይ ያተኮሩ ናቸው:: ቅዱሳኑን ከመከራ ለማዳን፣ ሰውን ለማሳረፍ ቦታ ማዘጋጀቱ፣ በበጉ ሠርግ ለማሳተፍ፣ በመንፈስ ነፍስና ሥጋ ሰውን ፍጹም ለማድረግ ማቀዱ ሌሎችንም ማመቻቸቱ እኛኑ ሐጢአተኞች የነበርነውን ሰዎች ከክፉ ለማዳንና ከፍ ለማድረግ ብሎ ነው::

እግዚአብሔር ለውን ሁሉ እጅግ ያፈቅራል፤ ይወድዳልም:: የእግዚአብሔር ፍቅር ድፍንና አፋዊ ብቻ አይደለም:: የተገለጸና በብዛት ደግሞ የሚገለጽ ነው:: በምድራችን ላይ የሰው ልጅ በከፍተኛ ደረጃ አስቀምጦ ከሚጠቀምባቸው የከበሩ ዕንቁ ድንጋዮች ውስጥ ወርቅ፡ ብርና አልማዝ ጥቂቶቹ ናቸው:: ይህም እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር ይገልጻል:: ሆኖም ግን በራዕይ 21:10-21 የተጠቀሱት እንደ በሉር፣ ያክንት፣ ወራውሬ፣ አሜቴስጢኖስ፣ ክርስጵራስስ፣ ሰርዶንክስና ሌሎችም ከመነጠቅና በትንሳኤ በኋላ በሰማይ የተዘጋጁ ክቡር እንቁዎች የተለዩ ናቸው::

ማንኛውም ሰው ለዚህ ለከበረ ህይወት ራሱን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊያዘጋጅ ይገባል:: የመነጠቅ ቀን ቀርቧል:: ዳግም ልደትን ያላገኘ ቅዱሳንን ጠይቆ በስርዓት ቁጭ ብሎ ሊመሰከርለት ይገባል:: ጌታን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለ ማንኛውም ክርስቲያን ደግሞ በስርዓት ስለ መነጠቅ ሊያውቅና ለመነጠቅ የሚያበቃውንም ዝግጅት ሊያደርግ ይገባል:: ኃይል በመስጠት ወደ እውነት ሁሉ ለመምራት ክብርንም ለማቀዳጀት ሙሉ ስልጣን ያለው የእግዚአብሔር ፀጋ ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን!



## ልዩ ትኩረት

ልዩ ትኩረት ሲባል መነሳት ያለበትን አንድ መሰረታዊ እውነት ለማሳየት ነው:: ይኸውም ለመነጠቅ ሲታሰብ ሌላ አደጋ ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ስለሚወሰድበት ጉዳይ ነው:: የመነጠቅ ጉዳይ ሲነሳ ልብን በጣም ይሰቅላል:: ያስናፍቃል:: ቀኑም ቶሎ እንዲደርስና እንድንገባበት ሁኔታው ያስቸኩለናል:: ከዚህም የተነሳ እንደ ተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ከአዕምሮአችን ቶሎ ልንናወጥና ወደ ባሰው አደናቃፊ ልምምድ ውስጥ እንዳንገባ ልንጠነቀቅ ይገባናል:: መነጠቅ የሚሆነው ሁሉም በተሰማራበት ስፍራ ማንም ሳያስበው በድንገትና በቅጽበተ ዐይን ነው:: ስለሆነም ማንም የመነጠቅ ቀን በዚህና በዚያ ቀን ነው በማለት ነውጥና አደጋ መፍጠር እንደሌለበት በጥብቅ ይታሰብበት::

# ክፍል ዘጠኝ

## ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች

ከመነጠቅ በኋላ ስለሚፈጸሙ ትዕይንቶች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ ነገሮች እንደሚሆኑ ማየት ይቻላል:: የድህረ-መነጠቅ ክንዋኔዎችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሰይተን እንመለከታለን:: እነርሱም፣

9.1. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በሰማይ

9.2. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በምድር ናቸው::

### 9.1. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በሰማይ

በክፍል 6.2.1. ውስጥ ስለ ራዕይ መጽሐፍ አከፋፈል ተመልክተናል:: ከክፍልፋዮቹ ውስጥ ራዕይ 4 እና 5 በሰማይ ስለሚሆኑ ነገሮች የሚገልጽ ነው:: ይህ የራዕይ 4 እስከ 5 ትዕይንት የሚጀምረው በራዕይ 4:1 ላይ መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ የሚፈጸመውን ሥርዓት በማገልጽ መልኩ ነው:: ሌሎችም የራዕይ ምዕራፎች የራዕይ አራትና አምስትን ትዕይንት የሚደግፉ አሉ::

### 9.1.1. በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ

የኋለኛው መለከት ተነፍቶ ያንቀላፉት ቅዱሳን ከተነሱ በኋላ በህይወት ያሉት ቅዱሳን ደግሞ በቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ወደ ክርስቶስ ይቀርባሉ:: ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ከአብ የተቀበላቸውን የእግዚአሔር ልጆች በሙሉ ለእግዚአብሔር አብ ያቀርባል:: ዮሐ. 17:6-11፣ 6:37፣44:: እነዚህን ጥቅሶች ስናነብብ ሰዎችን ስለድነታቸው ለጌታ ኢየሱስ የሰጠ አብ ነው:: አብ ለጌታ እንደሰጠው፣ ጌታም በዘመኑ መጨረሻ በደሙ የዋጃቸውን እነዚህን የመንፈስ_በኩራት ያላቸውን ልጆቹን በአብ ፊት ያቀርባቸዋል:: ይህ ስርዓት ደግሞ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክት ሁሉ እጅግ ሊታይ የሚናፈቅ ነው:: 1ኛጴጥ. 1:12፣ ሉቃስ 15:7 እና 10:: እስከ ዛሬ ድረስ ጌታ በደሙ የዋጃቸው ቅዱሳን እንኳን ለመላዕክት ይቅርና በዚህ በምድር ለሚኖሩ እንስሳትም ሆነ



ዎች የተገለጠ አይደለም:: ሮሜ 8:19-24:: በምድር ስለ ሰዎች መዳን መላዕክት ሪፖርት ይቀርብላቸዋል እንጂ የሚድኑትን ነፍሳት የዩአቸውም:: 1ኛጴጥ.1:12:: ሆኖም ከተወሰኑ መላዕክት ጋር እግዚአብሔር ዕቅድ የጥበቃ ግንኙነት ሊደረግ ይቻላል:: ቅዱሳን እግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርቡ ከኤፌ. 5:27፣ ቆላ. 3:4 እና 1ኛተሰ.3:13 ይበልጥ መረዳት ይቻላል::

### 9.1.2. የቅዱሳን በዘላለም ቅድስና መታተም

ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳን በአየር ላይ ተገናኝተው በተራ ቁጥር አንድ እንደተጠቀሰው በአብ ፊት ይቀርባሉ:: ከዚያም ወደፊት በኃጢአት ሊከሰሱና ሊወድቁ ወደማይችሉበት ህይወት ውስጥ ይገባሉ:: ይህንን ህይወት የሚያገኙ ት ከእግዚአብሔር ነው:: 1ኛተሰ. 3:13:: እዚህ ላይ ሊተኮርበት የሚገባ እውነት አለ:: ይኸውም በዳንኤል 9:24 ላይ ስለ አይሁዶች የተጠቀሰውን እውነት በተመለከተ ነው:: በዚህ ጥቅስ ላይ አይሁዶች ሰባኛው ሱባኤ ካለቀ በኋላ ኃጢአታቸው ፈጽሞ ይቅር እንደሚባል በደል እንደማይቆጠርባቸውና ወደ ዘላለም ቅድስና እንደሚገቡ ተጠቅሷል:: ይህ የሚሆነው ጌታ ለሺህ ዓመት ለመንገስ ወደ ምድር ሊመጣ ሲል ነው:: የተነጠቁት ቅዱሳን ግን በዘላለም ቅድስና የሚታተሙት በሰማይ ነው:: (1ኛተሰ. 5:23)

### 9.1.3. የተነጠቁ ቅዱሳን ፍርድ

አንዳንድ አማኞች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይህ ፍርድ የሚሆነው በምድር ነው የሚል ሃሣብ ሲኖራቸው ይችላል:: ሆኖም ግን ይህ የምድሩን ፍርድ አያመለክትም:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የታወቁ ሰባት ዋና ዋና የፍርድ ዓይነቶች አሉ:: እነርሱም፣

9.1.3.1. የአማኞች ኃጢአት በመስቀል ላይ መፈረድ ::ዮሐ. 12:31-32

9.1.3.2. የአማኞች ራሳቸውን መፍረድ/መመርመር፤ይህ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከሚለሩት

9.1.3.3. ነገር አኳያ በእግዚአብሔር ቃል ራስን መበየን ነው:: 1ኛቆሮ. 11:31-32:: የእስራኤል ፍርድ እስራኤላውያን ለረጅም ዘመናት በእግዚአብሔር ስቁቋስ ፍርድ አሉ:: ሕዝ.20:33-44::

9.1.3.4. የመላዕክት ፍርድ ይህ በእግዚአብሔር ላይ ያመጹትን መላዕክት ይመለከታል:: 2ኛጴጥ.2:4፣ይሁዳ 1:6-7::

9.1.3.5. የተነጠቁ ቅዱሳን አማኞች ሥራ ፍርድ፤ ሮሜ. 14:10፤ 2ኛቆሮ.5:10-11፤1ኛ ቆሮ.3:11-15::

9.1.3.6. በምድር ያሉ መንግሥታት ፍርድ፤ይህ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ በሺሁ ዓመት መንግሥት መጀመሪያ የሚሰጠው ፍርድ ነው:: ማቴ.25:31-46::

9.1.3.7. የሙታን ኃጢአተኞች ፍርድ፤ ይህ ከሺሁ ዓመት ፍጻሜ በኋላ ትንላኤ ሆኖ የሚከናወን ፍርድ ነው:: ራዕይ 20:11-15 ሮሜ 2:16፣ ሐሥ.17:31::

በተራ ቁጥር 5 ላይ እንደምንመለከተው የቅዱሳን አማኞች ፍርድ በሰማይ ይሆናል:: ከመነጠቅ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙት ትዕይንቶች ውስጥ አንዱ ይህ ፍርድ ነው:: ፍርዱ ሽልማት የማያስገኝ ዓይነት እንጂ ከዘላለም ሕይወት የሚለይ አይደለም::

## 9.1.4. ወደተዘጋጀላው ስፍራ መወሰድ

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 14ኛው ምዕራፍ ውስጥ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ አለ:: ይህም ተስፋ ስፍራን ካዘጋጀ በኋላ በዚያ ቅዱሳኑን ማስቀመጡ ነው:: በዕብ. 11:10 ላይ ከተማይቱ መሠረት ያላት፣ እግዚአብሔር የሰራትና የፈጠራት እንደሆነች ተገልጿል:: በተጨማሪም ጌታን አምነው የሚከተሉ እውነተኛ አማኞች ሁሉ በዕብ. 13:14 እንደተጠቀሰው ሰማያዊቱን ከተማ ይናፍቃሉ:: ጌታም በተናገረው ቃልና በሰጠው ተስፋ መሠረት ቅዱሳኑን ወዳዘጋጀልን ስፍራ ይወስደናል:: ሪዕይ 3:12፤ 1ኛቆሮ. 2:9::



## 9.1.5. በተዘጋጀላቸው ስፍራ መኖር

ይህ ሃሣብና በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው ተቀራራቢነት ያለው ቢመስልም ሁለቱ ልዩነት አላቸው:: መወሰድ ቀዳሚ ነገር ሲሆን ..መኖር.. ደግሞ ሌላ ተከታይ ጉዳይ ነው:: አሁን በዚህ በተረገመ ዓለም ስንኖር ሐዘን፣ ለቅሶ፣ ዋይታ፣ ረሃብ፣ ስቃይ፣ ጉስቁልና፣ ድካም፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ደዌ፣ ሁከት፣ ማጭበርበር፣ ሽፍጥና ልዩ ልዩ እስራት ለፍሮበት ይታያል:: በተዘጋጀልን ስፍራ መኖር ማለት ግን ከበጐ ተቃራኒ ሁሉ ተለይቶ በደስታ፣ በሰላምና በአስፈላጉ ነገሮች ሁሉ ብልጽግና በመሞላት መቀመጥ ነው::በ1ኛ ቆሮ. 2:9፣ ..ነገር ግን ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ... የተባለው ቃል ተፈጻሚነት ከሚያገኙባቸው ቦታዎች አንዱ በሰማይ ነው:: ይህ ቃል በከፊል ተፈጻሚነት ቢያገኝም በዘላለም ሕይወት የሚፈጸሙ ግን ሌሎች ብዙ ተስፋዎች ገና ይቀራሉ:: ዮሐ.14:1-3::

## 9.1.6. ቋሚ አምልኮ ማካሄድ

የቅዱሳን መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙ ነገሮች ውስጥ አንደኛውና ትልቁ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ አምልኮ ማድረግ ነው:: የአምልኮው ፕሮግራም ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ መዝሙር መዘመር፣ ለእግዚአብሔር መስገድ፣ ክብር ውዳሴና ምስጋናን ማቅረብና ወዘተ ይገኛሉ::ራዕይ 4:10-11፤ 5:14፤ 7:9-17፤ 19:1-9::

## 9.1.7. የጌታን እራት ስርዓት ማከናወን

ይህ ሥርዓት ጌታ ኢየሱስ እስኪመጣ ቅዱሳኑ በምድር እንጠብቀዋለን::1ኛቆሮ. 11:23-26:: ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ የሰማያዊ ስርዓት ፈቃድ ደግሞ ለዘላለም ይታሰባል:: ይህንንም ከማቴ. 26:29፤ ማር. 14:25፤ ሉቃስ 22:18 እና 30 መመልከት ይቻላል::

## 9.1.8. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሰማይ መከፈት

በራዕይ 11:19 ላይ በሰማይ ቤተ መቅደስ ሲከፈት ይታያል:: የዚህ ቤተ መቅደስ መከፈት በራዕይ 4:1 ካለው የሰማይ ደጅ መከፈት ጋር ተቀራራቢነት አለው:: በዚህ ክፍል በዕብ. 8:5 እና 9:23 የተጠቀሰውም የታቦቱ ሁኔታም ተጠቅሷል:: እግዚአብሔር ብዙ ታላላቅ ነገሮቹን የሚፈጽመው ከቤተ መቅደሱ ሆኖ ነው::

## 9.1.8. የቅዱሳን በበጉ ሠርግ ስርዓት መካፈል

ይህ ሠርግ ታሪኩ በራዕይ 19:1-9 ተጠቅሷል:: በዚህ ሠርግ ተካፋይ የሚሆኑት በቁጥር 7 ላይ ..የበጉ ሚስት.. በሚል መጠሪያ የተጠቀሱት ..ቅዱሳን.. ናቸው:: ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቷታልና ይላል:: ይህም ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ ካመለከተ ቅዱሳን የሚባሉት በ5ቱ የመነጠቅ ዓይነቶች አልፈው በሰማይ የተከማቹ ከትንሳኤ በኋላ በተዘጋጀላቸው ስፍራ የኖሩ እውነተኛ አማኞች ናቸው::

ሌሎች ስለ በጉ ሚስት የሚጠቅሱት ሃሣብ አለ:: የበጉ ሚስት ቤተ ክርስቲያን ናት፤ እስራኤል ናት የሚሉ አሉ:: ሆኖም ግን ይህ አመለካከት ለብቻው እውነት አይሆንም:: ሁለቱም ክፍሎች በበጉ ሚስት ውስጥ ይካተታሉ:: በራዕይ 19:8 ላይ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የተሰጣቸው በቁጥር 14 ደግሞ እነዚያው ጌታን ተከትለው ወደ ምድር ሲመለሱ ያሳያል:: በትንሳኤና በመነጠቅ ሥርዐት ያለፉ ቅዱሳን ናቸው ማለት ነው::

## 9.1.9. ወደ ምድር ለመመለስና የመጨረሻውን ጦርነት ለመዋጋት መዘጋጀት

በራዕይ 19 የበጉን ሠርግ ከፈጸሙ በኋላ የሚቀጥለው ደረጃ የአርማጌዶንን ጦነት ከመሪያችን ከጌታ ኢየሱስ ጋር ሆነን የምድርን ነገስታት ለመዋጋት መዘጋጀት ነው:: በራዕይ 19:11 ላይ ጌታ ኢየሱስ ተዋጊ



እንደሆነ፤ በራዕይ 17:14 ደግሞ ከእርሱ ጋር ያሉን የታመኑን፣ የተመረጡን፣ የተጠሩን ደግሞ እንደምንዋጋ ይናገራል:: በዘካርያስ 14:5 ላይ ጌታ ከቅዱሳኑ ጋር እንደሚመጣ ይናገራል:: በተጨማሪም ራዕይ 19:11-21 በዝርዝር መመልከት ይቻላል:: በዚህ ጦርነት አሸናፊው ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳኑ ይሆናሉ:: በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ጦርነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሆን ነው:: ይህ ጦርነት በነቢዩ ኢሳይያስና (2:2-4) ሚክያስ (4:1-5) የተነገረው ጦርነት ነው:: ጦርነቱ አህዛብ ሰይፋቸውን ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ የሚቀጠቅጡበት ነው:: በኢዩኤል 3:9-10 ላይ የዓለም መንግስታት ለጦርነት ዝግጅት እያደረጉ ያሉበት ጊዜ ነበር:: ሆኖም ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በአርማጌዶን ጦርነት አሸናፊነቱ ከተረጋገጠና ሁሉም መሸነፉን ካወቀ በኋላ ሁሉም ለክርስቶስ ተገዢ ይሆናል ማለት ነው:: ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ማለት ይህ ነው:: 3ኛው የዓለም ጦርነት እዚህ ላይ ያበቃል:: የዓለም መንግሥታት ከ130 ዓመታት በላይ በኢንተርናሲዮናል መዝሙር አማካይነት የፍጻሜው ጦርነት ነው ሁሉም ዘብ ይቁም በቦታው በማለት ሲዘምሩትና ሲናፍቁት የነበረው ጦርነት እዚህ ላይ ይፈጸማል:: የምድር ትዕቢተኞችም ዕድል ፈንታ በራዕይ 14:20 እና 19:17-21 እንደተጠቀሰው ደማቸው እስከ 1600 ምዕራፍ ወይም 320 ኪሎ ሜትር በመፍሰስና ሥጋቸውም ለምድር ዐራዊትና ለሰማይ አዕዋፋት በመሰጠት ይሆናል:: ፍጻሜ የሚያገኙት እነዚህ የአርማጌዶን ጦርነት ተሳታፊዎች ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንቀሳቃሽ ክፉ መላዕክቶቻቸውና ሰይጣን ናቸው:: ራዕይ 20:1-4:: ታዲያ ዛሬ በምድራችን ያሉ ልዩ ልዩ ዘማናዊ የጨረር፤ የኑክለርና የኮምፒዩተር የጦር መሳሪያ ያላቸው የጦር ሐይሎች ካላቸው የጦር ሐይልና ከትምክህታቸው የተነሳ ንስሐ የሚገቡ ይመስላል? አሁን በምድሪቱ ላይ ያሉ የጦር ሰራዊቶች ካላቸው የጦር መሳሪያ ጋር የመጨረሻ ዕድላቸው በራዕይ 16:15 ላይ እንደተጠቀሰው ማፈር ብቻ ነው:: አይገርምም?!

የቤተ ክርስቲያንና የመከራው ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙት ዐበይት ትዕይንቶች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ተሞክሮአል:: ጌታ ኢየሱስ ጌታ ነው:: እርሱ የፍቅር ጌታ ነው:: ጌታ ኢየሱስ እንደ ሰይጣን ራሱን ሸፍኖ አልኖረም:: ለሰው ልጆች ጥንቃቄና ዝግጅት የሚያስፈልገውን ነገር ራሱ ወደ ምድር በመምጣት በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ሆኖ አስተምሯል:: ደቀ መዛሙርቱን አሰልጥኖ እውነትን ገልጿል:: በተጨማሪም ከሰማይ እውነተኛ አጽናኝ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ልኳል:: በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ሰውን ፈጽሞ አልበደለውም:: ምንም አልጐዳውም:: ሰው ግን አላወቀም:: ወዴት መጠጋት፣ እንዴት መጠጋትና ተጣብቆ መኖር እንዳለበት ባለመረዳቱ የማያስፈልግ ብዙ ነገሮችን ያዘ::ጉዳቱም እጅግ የከፋ ሆነ::

## 9.2. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በምድር

ስለ ድህረ- መነጠቅ ክንዋኔዎች በምድር ስናስብ በቀጥታ ከራዕይ ምዕራፍ 6-19 ያለውን የመከራ ዘመንና በውስጡም የሚያልፈውን የእግዚአብሔር ምህረት ለመጠቆም እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል:: የዚህ የመከራ ዘመን ምንነት ወደፊት በዝርዝር ይቀርባል:: ሆኖም አንዳንድ በአቀራረባቸው ለየት ያለ መልክ ያላቸውን ዋና ዋና ነገሮች ማንሳቱ ጠቃሚ ነው:: የራዕይን መጽሐፍ ትንታኔ ስንመለከት የመከራውን ዘመን ልብ እንላለን:: ልክ አውሬው በራዕይ 6:2 ላይ እንደተለቀቀ ሰባቱ ማህተሞች ሲፈቱ የመከራው ዘመን ይቀጥላል:: መከራው የሚፈጸመው በሶስት ዋና ዋና መንገዶች ማለትም በ7ቱ ማህተሞች፤ በ7ቱ መለከቶችና በ7ቱ ጽዋዎች እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ መቅሰፍቶች አማካይነት ነው:: ይህ ጊዜ የሰዎች ሁሉ ትምክህት የሚመታበት ጊዜ ነው:: ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ውሖች፤ ውቅያኖሶች፤ተክሎችና የተፈጥሮ ጥቅማጥቅሞች በሲሶ ደረጃ የሚመቱበት ጊዜ ይሆናል::



ውድ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠርክ ሰው ሆይ! ጠንክር በል! አስተውል! ዛሬ እያብለጨለጨ ያለው ውብ መሳይ ሁሉ አንድ ቀን ወይ ጥለኸው ወይም ደግሞ እንደ ፓኪስታኑና እንደ አሜሪካው የምድር ነውጥና የጎርፍ መጥለቅለቅ ጥሎህ ይሄዳል:: ነገርን መርምር፣ እውነትን ያዝ፣ በዚያም ጽና:: ምንም ቢሆን ምን የእውነተኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ይፈጸማል:: የዓለም ፍጻሜ በፊትህ ቀርቧል:: በራስህ ጥረት ከፍርድ ማምለጥ አትችልም:: መናቅ የትዕቢት ምልክት ነው:: ትክክል የሆነውን የምትሰማውን ዕውነት ያዝ፤ የያዝከውን ደግሞ አትልቀቅ:: በአሁኑ ጊዜ ብዙ መጻሕፍት ዋጋ አጥተዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ብዙ መከራና ስደት ደርሶበት፡ የብዙ አሉታዊ የሂስ መደሻዎችን ሰባብሮ ለሰው ልጆች ድነት እዚህ አለ:: አልጠፋም፤ አይጠፋምም:: ምክንያቱም የኋላ ደጀኑና ጠባቂው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው:: እውነት ነው:: እውነቱን ያዘው ያከብርሃል:: ሊያዋርድህ ከተዘጋጀውም ምናምንቴ ያላቅቅሃል:: የክርስቶስ መስካሪው መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይምራህ:: አሜን!

# ክፍል አሥር

## ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸው ልምምዶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገለጸልን እውነቶች ውስጥ መንፈሴንና ነፍሴን በሐሴት የሚሞላ ቃል (ንግግር) አለ:: ይኸውም፤

በሉቃስ 21:14 ... *በልባችሁ አኑሩት*.. በቁጥር 28 ..ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቧልና *አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሱ*..፣ ቁጥር 34 ላይ ደግሞ ..... *ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ*..፣ ቁጥር 36 ላይም ..... በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ *ስትፀልዩ ትጉ*..፣ በማር. 13:23ና በማቴ.24:25 ደግሞ *..እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኳችሁ..* የተሰኙት የጌታ የፍቅር ማስጠንቀቂያዎች ናቸው:: ጌታ ለሚያምኑበት ሁሉ እውነተኛ የሆነ ያልተለበጠ ፍቅር አለው:: ፍቅሩ ፍጹም ስለሆነ ማንም ሰው ከአእምሯዊና መንፈሳዊ ጽልመት (አለማወቅ) የተነሳ እንዲጐዳ አይፈልግም:: ከዚህም የተነሳ የወደፊቱን ክፉ ነገር መምጣት ገልጾ ከዚያም ሊዳን የሚቻልበትን ዘዴ ሁሉ አዘጋጅቷል:: ደጋግሞም አስጠንቅቆአል::

ጌታ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋል:: ከዚህም በመነሳት ከክፉ ሊድኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ሁሉ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ በኩል አመቻችቷል:: ጌታ ኢየሱስ ስፍራ ሊያዘጋጅልን ሲሄድ ለተዘጋጀልን ቦታ ብቁዎች የምንሆንበትንም መንገዶች ጠቁሞናል (አመልክቶናል):: ጌታ ብቻ ሳይሆን የምጽዐቱና የዓለም ፍጻሜ እውነተኛ ምስክሮችም አጠንክረው አስተምረዋል::

የኋለኛው መለከት በሚነፋት ጊዜ ሙታን ሲነሱና ህያዋንም ሊለወጡ ለመነጠቅና ጌታን በአየር ለመቀበል ወደ እረፍት ስፍራችንም ለመሄድ እያንዳንዱ ቅዱስ አማኝ ሊያሟላቸው ወይም ህይወቱን ሊመረምርባቸው የሚገቡ እውነቶች የሚከተሉት ናቸው::



አንድ አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነና በመነጠቅ የዘላለሙን ሕይወት ለማግኘት ከፈለገ ለመነጠቅ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በጥንቃቄና በማስተዋል ሊከታተልና ሊኖር ይገባዋል::

### 10.1. የክርስቶስ ኢየሱስ መሆን

ጌታ ኢየሱስም ሆነ ደቀመዛሙርቱ በዚህ ዓለም በምድር ላይ ሲኖር ሁለት ዓይነት ልጆች እንዳሉ ተናግረዋል:: እነርሱም የእግዚአብሔርና የዲያብሎስ ናቸው:: ዮሐ. 8:38፣ 41፣ 44 እና ሐዋርያው ዮሐንስም እንደገለጸው በ1ኛዮሐ. 3:10 ላይ የተጻፉት ናቸው:: የክርስቶስ መሆን ማለት ልክ ጌታ በቃሉ እንዳስተማረው በሐዋርያቱም እንደተጻፈው በትክክለኛው መንገድ፣ ውሸት ባልተደባለቀበት እውነት ገብቶ በዘላለማዊው ህይወት በክርስቶስ ኢየሱስ መኖር ነው:: ህይወት ክርስቶስ ነው:: ህይወት ወይም በክርስቶስ መሆን ማለት በዮሐ. 8 እንደተጠቀሰው የራስን ፍላጐት ለማጽናት ጌታንና የእርሱን እውነት (መንገድ) ተከታዮች ሸንጥን ገትሮ መከራከር አይደለም:: የክርስቶስ ኢየሱስ መሆን ማለት ከአስመሳይነት ህይወት መውጣት ነው::

በ1ኛቆሮ. 15:20-23 እንደተጠቀሰው የመጀመሪያው ትንሳኤ ባለቤት (ተካፋይ) የሚሆኑት ጌታን አምነው ያንቀላፉ (የሞቱ) ብቻ ናቸው:: መነጠቅም የሚሆነው ከትንሳኤ በኋላ ወዲያው ነው:: ለመነጠቅ በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ ማንኛውም አማኝ ነኝ ባይ በቂ (ያረፈ) የልብ ምስክርነት ሊኖረው ይገባል ይህም ደግሞ ስም ብቻ ከመሆን የተለየ ህይወትንና የእግዚአብሔር ልጅነትን ይጠቀልላል ::ገላ. 5:24፣ ዮሐ. 1:12-13::

### 10.2. በክርስቶስ ኢየሱስ ብርሃን መጓዝ

ጌታ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነው:: በዮሐ. 1:4-5፣ 8:12፣ 9:5 እና 12:35-46 ስንመለከት ጌታ ..እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ.. ሊል ህይወቱ፣ ንግግሩ፣

ትምህርቱ፣ ፍቅሩ፣ ጥበቡ፣ ርህራሄው፣ ባጠቃላይ ተግባሩ ሁሉ ትክክለኛና እውነተኛ ምንም ዓይነት ነውር የሌለበት መሆኑን ሊያመለክት ነው:: ብርሃን የጽድቅና የእውነት ምሳሌ ሲሆን ጭለማ ደግሞ የኃጢአትና የርኩሰት ምሳሌ (መግለጫ) ነው:: በብርሃን መመላለስ (መኗዝ) ማለት ከክርስቶስ ጋር በኅብረት መኗዝ ማለት ነው:: ይህ ኅብረት ደግሞ ፈጽሞ ጌታን መምሰል ይኖርበታል:: 1ኛዮሐ. 1:5-7 ስንመለከት .....ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን፣ እውነትንም አናደርግም::.. ማለቱ እውነተኛ አማኝ ኃጢአትን አይሰራም ማለቱ ነው:: በተጨማሪም በ1ኛዮሐ. 2:8-11 በአጠገብ ያለውን ጐረቤት፣ የሥጋ ዘመድንም ሆነ ባዕድ የሆነውን በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ሰው መጥላት ነፍስ ገዳይነትና፣ በጨለማ መመላለስም እንደሆነ ይገልጻል:: ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 5:14 ላይ ..እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ::.. ሲል ከእኔ የተቀበላችሁትን በመንፈስ ቅዱስ የሆነውን የጽድቅ ሥራ በኃጢአት ለሚኖሩ (ዓለማውያን) ትገልጻላችሁ ማለቱ ነው:: ይህ ንግግሩ ግን እኔ የእግዚአብሔር ልጅ እናንተም የእግዚአብሔር ልጆች፤ እኔ አምላክ እናንተም አምላክ ናችሁ ማለቱ አይደለም:: በብርሃን መመላለስ ማለት ጌታ ባስተማረው የህይወት ኑሮ፣ (ዮሐ. 14:6) እርሱን መስሎ መኗዝ ማለት ነው:: ቆላ. 2:6::

ታዲያ እነዚህ ራሳቸውን በቤተ ክርስቲያን ክልል በክርስቶስ ወዳጅነትና በብርሃን መስመር እንደሚኗዙ አጥብቀው የሚያስተምሩ፣ ነገር ግን በስውር የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት የሚያሳድዱ የሚገድሉና የሚያስገድሉ ምን ይባላሉ? ለመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ሰው ጥሉ፣ አስወግሩ፣ በቀል የእናንተ ነው፣ ብድራቱን ክፈሉ፣ ክፉን በክፉ አሸንፉ ብሏል? ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች አሁን እንነጠቃለን ብለው ያስባሉ ወይስ ያምናሉ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ/ያልተገኘ እምነት ከየት ይሆን? እንግዲህ ራሳችሁን መርምሩ:: ራሳችሁን አታስቱ:: በብርሃን የማይመላለስ፣ በ1ኛቆሮ. 11:1 እንደተጠቀሰው ልክ የጌታን ህይወት መስሎ የማይኖር ፈጽሞ አይነጠቅም:: መነጠቅ በኃይለ-ቃልና ኮስተር ባለ ፊት በነጐድጓድ ድምጽ ..እነጠቃለሁ! በሚል ኀይለኛ



ንግግርና ምኞት አይገኝም:: መነጠቅ በመፈክር አይደረስበትም:: የቆምህ መስሎህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ::

## 10.3. <u>በመንፈስ መኖርና መመላለስ</u>

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሁለት ሃሣቦች አሉ:: እነርሱም፣ በመንፈስ መኖርና በመንፈስ መመላለስ (መኗዝ) ናቸው::

በመንፈስ መኖር ማለት ከኃጢአት በክርስቶስ ደም የሚያነጻውን፣ የህይወት መንፈስ የሆነውን ከጌታ መቀበልና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ነው:: አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ በመንፈስ ይኖራል ማለት ነው:: ለዚህም አማኙ ሊኖርባቸው የሚገቡ ብዙ የህይወት ልምምዶች አሉ::

በመንፈስ መመላለስ ማለት በሮሜ 8:14 እንደተጠቀሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት በማግኘት መኗዝ ማለት ነው:: አንድ ሰው ጌታን እንደግል መድኃኒቱ ሲቀበል የእግዚአብሔር ልጅ የሚያደርገውን መንፈስ ቅዱስ ያገኛል:: ለዘላለም በውስጡ በሚኖረውም መንፈስ አማካይነት በገላ. 5:22-23 የተጠቀሱትንና ሌሎችንም የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራል:: ከእነዚህም ፍሬዎች ውስጥ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም (ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ወዳጅነት እንዲኖረው የሚረዱት)፤ ትዕግስት፣ ቸርነትና በጐነት ደግሞ (ከሰውና ከፍጥረታት ጋር የጠበቀ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረው የሚረዱት)፣ እምነት የዋህነትና ራስን መግዛት ደግሞ (ከራሱ ጋር ትክክለኛ ሕብረት እንዲኖረው የሚረዱት) የመሳሰሉትም ይገኛሉ::

በመንፈስ መመላለስ ማለት ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኙ ከእግዚአብሔር ጋር በማይጋጩ ባህርያት መኗዝ ማለት ነው:: ሰው ሦስትነት አለው:: ይህም በ1ኛተሰ. 5:23፣ በዕብ. 4:12 እና በዘፍ.2:7 ላይ ተገልጿል:: ሰው መንፈስ ነፍስና ሥጋ አለው:: እግዚአብሔር ሰውን ለምን እንዲህ ፈጠረው? በሦስትነት የተፈጠረበት ምክንያት ሰው በመንፈሱ ከመንፈሳዊው ዓለም በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ፤ በነፍሱ የአእምሮን፣

የማውጠንጠንን፣ የስሜትና የፈቃድ ሥራዎችን እንዲሰራና ሥጋው ደግሞ ከውጫዊው ዓለም ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ነው:: ስመሆኑ እግዚአብሔር በመንፈስህ በኩል በቅዱስ መንፈሱ ተራክቦ (ህብረት) ሲያደርግ ትረዳለህ (ጃለሽ)? ለከንቱ ጉዳይ መንፈስ አልተለጠንምና ተጠንቅቀን መንፈስ ቅዱስ ሲናገረን አዳምጠን ልንታዘዝ ይጠበቅብናል::

## 10.4. ብጹዕና ቅዱስ መሆን ያሻል

ብጹዕ ማለት የተባረከ፣ የተመረቀ፣ እጅግ ደስተኛ የሆነ የሐሴት ሰው ማለት ነው:: ቅዱ ማለት ደግሞ ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚያምን የሚኖር፣ ከኃጢአት የራቀ፣ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ እንደተባለ የሚኖር ማለት ነው:: ማንኛውም ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኙ አድርጐ የተቀበለ ሁሉ በቅድስናና በንጽሕና ሲኖር ይገባዋል::

ብዙ አማኞች በቅድስና መኖር አይቻልም ይላሉ:: ሆኖም ግን ይህ የኃጢአተኞች ወይም የክርስቲያን መሳይ ሰዎች ጩኸት፣ የስጋውያን ልፋፌ ነው:: ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ቅዱስ መሆን ይቻላል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 17:17 ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው፣ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ ሲል፤ ጴጥሮስም በ1ኛ ጴጥ. 1:16 ስለ ቅድስና ሲናገሩ ለማስመሰል አልገለጹትም:: ስለሆነም ከትንሳኤ በኋላ የመነጠቅን ህይወት ለማየት ብጹዕና ቅዱስ መሆን ያሻል:: ለሚያምን ደግሞ ሁሉ ይቻላልና:: ራዕይ 20:4-6፣ ማር. 9:23::

## 10.5. በክርስቶስ ኢየሱስ መሆን

ይህ ሃሣብ በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ..የክርስቶስ መሆን.. ትንሽ ይለያል:: የመጀመሪያው ከሰይጣን ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት መሰወጥ ሲሆን ይህ ግን ወደ እግዚአብሔር ከመጡ በኋላ ወደ ዓለም ላይመለሱ ጌታንም ሳይክዱ በጌታ ኢየሱስ እቅፍ እስከ መጨረሻ ጸንቶ መቆምን የሚያመለክት ነው:: ይህም እውነት በ2ኛቆሮ.5:17-18 ተጠቅሷል::



ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ይላልና:: አንዳንድ ክርስቲያኖች ጌታን ከተቀበሉ በኋላ እስከ መጨረሻ ጌታን በመታዘዝ የመትጋታቸውን ጉዳይ ቸል ይሉታል:: ውጤቱም ህይወታቸው ወደ ቀድሞው መመለስ ነው:: አንዳንዶች ደግሞ ..እኔን ጌታ ኢየሱስ በህይወት መጽሐፍ ስሜን ከጻፈ በኋላ ብዕር አንስቶ ስሜን የሚሰርዝ ሕጻን አይደለም:: ጌታ የዚህን ያህል ፈጽሞ ጨካኝ አይደለም በሚል ከንቱ ምኞት አንጸ ተጽፌአለሁ በማለት የኃጢአት ወዳጆችና እስረኞች ከሆኑ ዋል አደር ብለዋል:: ቃሉ ግን የሚለው እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል ነው::

## 10.6. ያለ ማቋረጥ መትጋት ያስፈልጋል

በምሳሌ 12:27 ላይ ..ታካች ሰው አደን ምንም አያድንም ለሰው የከበረ ህብት ትጋት ነው.. ይላል:: ሰው በመንፈሳዊውም ሆነ በቁሳዊው መስክ ተሰማርቶ በደንብ ቢተጋ የልቡን መሻት ከእግዚአብሔር ያገኛል:: የትጋት ዋነኛ አስፈላጊነቱ የያዙትንና ያልጨበጡትን መልካም ነገር አጥብቆ ለመያዝ፣ የማያስፈልገውንም ለማራቅ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ ትጋት ስናስብ ትኩረት ልንሰጥበት የሚገባው አቅጣጫ፣

10.6.1. መመረጥንና መጠራትን ከማጽናት አኳያ
10.6.2. ሲመጣ ካለው ክፉ ከማምለጥ አኳያ
10.6.3. መንፈስ ቅዱስን ካለማሳዘን አንጻር
10.6.4. በፀሎት ከመጠንከር አኳያ
10.6.5. የጌታን ምጽዐት ከመጠበቅና ፊቱ ከመቆም አንጻር
10.6.6. ሙሉ ደመወዝን ከማግኘት አኳያ
10.6.7. የእግዚአብሔርን እውነት (በተቀበሉት መክሊት ከመነገድ-ካለመቅበር) ከማካፈል አንጻር
10.6.8. ሥራ ፈትና ፍሬቢስ ካለመሆንና ከሌሎችም እውነቶች አኳያ ናቸው:: ሉቃ. 21:34-36፤ 1ኛጴጥ. 5:8::

## 10.7. መልካም መሆንና ማድረግ

በሮሜ 12:9፣ 14-21፣ 1ኛጴጥ. 3:10-12ትን በተጨማሪም የ 5:28-29ን ስናነብ ጌታ ምን ያህል ክፉ ነገርን እንደሚጠላ ያሳየናል:: የሆነውን እንደ ልዩ ርኩስ ነገር ተጸይፈን ከመልካሙ ነገር ጋር መጣ ይኖርብናል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ...መልካም ያደ ለህይወት ትንሳኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና... ሲል መስራት ሰውን ምን ያህል ለዘላለም ጥፋት የማዘጋጀት ኃይል እንዳለ በግልጽ መረዳት ይቻላል::

በአሁኑ ወቅት በዓለማችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ረሃብተኞ የተራቆቱ፣ ህመምተኞች ... እያሉ እግዚአብሔር ፀሐይና ዝናብ ሰጥቶ ም ያበቀለችውን እህል ወደ ባህር ማፍሰስና በየማከማቻው አበስብሶ ማቃ እንዴት ያለ ታላቅ ክፋት ይሆን? ሆኖም በፍርድ ቀን ምላሽ ይሰጡበታ ለሌላው ማካፈል መልካም ከመሆን የሚገኝ (የሚመነጭ) መልካም (በ ተግባር ነው:: ህይወታችንን ስናየው ምን ያህል ስውርና ግልጽ የሆነ ክፋ አለበት? መልካምነት ከችግር የተነሳ ርቆን ይሆን?

## 10.8. ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ መሆን ያሻል

ጌታ ኢየሱስ የሚመጣው በኤፌ. 5:27፣ 1ኛዮሐ. 3:2 እንደተጠቀሰው ያለ ነውርና ነቀፋ ያሉትን እድፈትና የፊት መጨማደ የሌለባቸውን ልጆቹን ሊወስድ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ንጹህ ነው:: ንጹህ (ቅዱ የሆነውን) ለማየት ዘወትር ንስሃ መግባት ያስፈልጋል:: ከድካም የተ ዘወትር ኃጢአት ውስጥ ከመዘፈቅና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ በፍርሃት በመንቀጥቀጥ በንስሃና በቃሉ በፀሎት ወደ በሰጠው ፈተና ሳለመግባ መታጠብ እጅግ ይጠቅማል::



## 10.9 በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ መግባት ያሻል፤

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ሁለት ዓይነት ቤተ ክርስቲያናት ተጠቅሰዋል:: እነርሱም፣ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያንና ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::

### 10.9.1. እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን

ይህች ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው እንደ ህይወታቸው መሪና አዳኝ አድርገው ጌታ ኢየሱስን የተቀበሉ ዘወትር በንጽህናና በቅድስና እንደ ቃሉ የሚኖሩ ቅዱሳን የተከማቹበት ናት:: የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት በሁለት ስፍራ ማለትም በምድርና በሰማይ (በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ) ይገኛሉ:: ይህች ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም የህይወቷ እንቅስቃሴ ጌታን የሚመስሉ አባላትን ትይዛለች:: በክርስቶስ ደም የተዋጁ ናቸው፤ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁም ናቸው:: የሰማይ ርስት መያዣም አላቸው:: ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው:: ማንኛውም የክርስቶስ ነኝ የሚል ሁሉ ሆኖም በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ክፍል ወይም የክርስቶስ አካል መሆን አይችልም:: ቆላ. 1:18፣ 1ኛቆሮ. 12:13፣ ኤፌ. 1:13-14 ስንመለከት የሰማዩ ርስታችን መያዣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ መታተም ነው:: ይህም መታተም ሰው ጌታን ሲቀበልና በላዩ ያለው ኃጢአት በጌታ ኢየሱስ ደም በመንፈስ ቅዱስ አሰራር ነጽቶ ስሙ በህይወት መጽሐፍ ሲጻፍ ነው:: ኤፌ. 1:20-23:: ለመነጠቅ በመንፈስ ቅዱስና በእውነተኛው ቃሉ አማካይነት የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ መግባት ያስፈልጋል::

### 10.9.2.. ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን

ጋለሞታ ማለት ባሏን ቤት አስቀምጣ ከሌላ ወንድ ጋር የምታመነዝር ሴት ማለት ነው:: እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ግን ከአንዱ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ..ባልሽ ፈጣሪሽ ነው.. እንደተባለ የምትጣበቅ ናት:: ከኢየሱስ ሌላ ማንም

በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፈጽሞ አይስለጥንባትም:: የጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን መሪና አንቀሳቃሽ የጥፋት ልጅ የሆነው ሐሰተኛው ክርስ ነው:: ይህች ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካውም በሐይማኖቱም ቁልፍ የሆነ ስፍራ ትይዛለች:: ህይወቷ በሙሉ ከዓለማዊ ኑሮ አይለይም:: የሃይማኖ ስርዓቷ ገንዘብ ለማግኘትና የራሷን የገነነ ስም ለማስጠራት ነው:: ከአለ መንግሥት ስደትና መከራ እንዲደርስባት ፈጽሞ አትሻም:: ባለማወቅ ይ በማወቅ ከገዢዎች፣ ከአለቆችና ከባለሥልጣናት ጋር ወዳጅነቷ የጠነ ነው:: በማንኛውም ሁኔታ መገፋትን አትፈልግም:: ክብሯ፡ ማዕረጓና ጤን እንዲጠበቅ ትናፍቃለች:: የነፍሳት መዳን፣ የዘላለምን ህይወት መው ተቀዳሚ ተግባሯ አይደለም:: በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የቆሙት የሚጓዙትን ከዓለማዊ መንግስት ጋር በመተባበር ያለ በቂ ምክንያትና ማስረ ታሳድዳለች፣ ትይዛለች፣ ትወግርና ትገድላለች::ዘርዘር ባለ መል የጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ባህርይ በራዕይ 17 ውስጥ በግል ተቀምጧል::

10.9.2.1. በመጨረሻ ዘመን አብዛኛው ህዝብ በዚች ቤተ ክርስቲያን አባ ናቸው:: ቁጥር 1፣ 15::

10.9.2.2. የምድር ነገስታትና ነዋሪዎቹም ወዳጆቿ ናቸው፤ ቁጥር 2::

10.9.2.3. በራዕይ 13:5-7 እንደተጠቀሰው እግዚአብሔርንና መላዕክትን ወዘ የሚሳደበው አውሬ ወይም ሐሰተኛው ክርስቶስ መሪ ና (በሐይማኖት ጉዳይ) ቁጥር 3::

10.9.2.4. በብዙ አቅጣጫ የራሷን ክብርና መቀማጠል ፈላጊ ናት፤ቁጥር 3-4::

10.9.2.5. ስሟ ነው እንጂ ..የእግዚአብሔር ተከታይ.. ኑሮዋ በሙሉ በርኩሰትና አጸያፊ ነገር የተሞላ ነው:: ቁጥር 5-7::

10.9.2.6. ሰዎች (አባሎቿ) የሚያውቁት እውነት የሚመስል ውጪአዊ መጠሪያ (መታወቂያ) አላት፤ ውስጣዊ (ሚስጢር የሆነ ስምም አላት):: ቁጥር 5::

10.9.2.7. ስለ ጌታ ኢየሱስ በእውነት የሚቆሙትንና የሚመሰክሩትን ቅዱሳን አማኞች ደም ታፈሳለች:: ቁጥር 6::



ዛሬ ታዲያ እንዲህ የሚያደርጉ እግዚአብሔርን እንከተላለን የሚሉ የሉም? ሐሰተኞች ናቸው በሚል ስም ቅዱሳንን እንደ ጳውሎስ (ሳውል ሳይለወጥ እንደነበር) የሚያስቃዩ በአብያተ ክርስቲያናት ስም የቆሙ የሉም? ጌታ ኢየሱስ ንቀኗቸው፣ አጥፏቸው፣ ግደሏቸው ፈጽሞ አላለም:: እስከ መከር ተዉአቸው ነው ያለው:: ታዲያ ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ውጪ የሆነ ህይወት የማን ነው? መሪውስ ማን ነው? የጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ይህ ነው:: የከፋት ሥራዋ በእርግጥ እጅግ ያስደንቃል:ቁ.7:: የአውሬውና (ሐሰተኛው ክርስቶስ) የምድር ነገስታት በራዕይ 19:11-20 እንደተጠቀሰው ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳኑ ከሰማይ ሲመጡ ለመውጋት የሚዘጋጁ ከሆነ በአውሬው ራስ ላይ የተቀመጠችውም ጋለሞታ ቤተክርስቲያን እንዲሁ ታስተባብራለች:: ራዕይ 17:12-14፣ 19:19::

ማንኛውም እግዚአብሔርን ጌታ ኢየሱስንና መንፈስ ቅዱስን እወዳለሁ፣ አከብራለሁ፣ እታዘዛለሁ የሚል ሁሉ ከዚች በስም ከምትኖር ጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ሊያነጻ ይገባል:: ይህ ዘመን የእውቀትና የምርመር ዘመን ነው:: ሐዋ. 17:10-11፣ ዳን. 12:4:: በሌላው ሰው ግፊትና ልመና ልምጥምጫም የሚኖርበት ጊዜም አይደለም:: እውነትን ለሚፈልጉ ቅኖች እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል እጅግ ቅርብ ነው:: ወደ እውነትም ሁሉ ይመራል:: ዮሐ. 16:13:: ስመኖር ብላችሁ ሁሉን የፈጠረውን በእውነተኝነት የሚያፈቅራችሁን ጌታ ኢየሱስን በኑሯችሁ የምትበድሉት በፊልጵ. 3:18-19 እንደተጠቀሰው ከማያምኑ ጋር በመመሳጠር የጌታን ቁስል የምትወጉ የአብያተ ክርስቲያናት ክፍል አማኞች ነን የምትሉ ወዮላችሁ! እውነተኛ ክብር የሚገኘው ከጌታ ጋር በመጣበቅ እንጂ የአውሬውን መንፈስ በማገልገልና የዓለም ወዳጅ በመሆን ፈጽሞ አይደለም:: እኔ ይህንን ጽሑፍ ስጽፍ ማንንም ልፈርድ አይደለም:: ለመንቃት፣ ለመዳንና ለመንፈሳዊ ትግል ለመነሳሳት ሁኔታዎችን ላመቻች እንጂ:: ለ30 እና ለ80 ዓመት ምድራዊ ደስታ ተብሎ ዘላለማዊውን ባርኮት ማጣት ምንኛ የሚዘገንን

ነው:: ስለዚህ የምድራዊ ኑሮ እየተበከለ ሁሉ እየጨለመ ሲሄድ የወፍ ድም እንኳን ሰውን በሚያስበረግግበት በዚህ ዘመን በፍጹም ልብ ..ፍራ እን የትዕቢትን ነገር አታስቡ. እንደተባለ በመፍራት ወደ ጌታ ኢየሱ በተከታታይ ንስሃና ከሐጢአት በመራቅ መመለስ ያስፈልጋል:: ይህ ጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ለክብሯ ብትሮጥና ከከሃ መንግሥታት ጋር ብትሰበጣጠርም በራዕይ 17:16-17 እንደተጠቀሰው ባከበሯት መንግሥታት እጅ መልሶ እግዚአብሔር ያደቅቃታል:: ሰው በምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ካልጀመረ በቀር ለኑሮው ትክክለኛ በረከትን (ጥቅምን) ለማግኘት ወሳኝ አይደለም:: ደግሞም ፈጽሞ አያውቅበትም:: ስለሆነም እምነቷ ያልተበረዘውን፣ መሳይ ህይወት የሌለባትን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ፈልገን እንጠጋ:: ተጠንቀቁ::

## 10.10. <u>የሦስቱን ሰባኪዎች ምስክርነት አጥብቆ መከታተል</u>

ለሰው ልጅ የውስጥ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ ሰጪ እንደ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ምንም የለም:: የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማቴ. 18:16 ላይ ...በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና... ይላል:: የአንድ የክርስቶስ ተከታይ ነኝ የሚል ሰው ህይወት ያለ ውጪአዊና ውስጣዊ ማስረገጫ (ምስክር ሰጪ) ዝም ብሎ እርቲ ቡርቲ (ከንቱ) በሆነ ነገር ሊመራ ፈጽሞ አይገባም:: የህይወቱን አቋም እንዲመዝን ትክክለኛ ምስክር ሰጪ ኃይላት ያስፈልጉታል:: እነዚህም ቢያንስ ሁለት ቢበዛ ሦስት መሆን አለባቸው:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሰዎች፣ መላዕት፣ እግዚአብሔር ተፈጥሮ፣ ጽሑፎችና እንስሳት ስለ ሰው ህይወት ምስክርነት ሲሰጡ ተመልክተናል:: እኔ ግን ከእነዚህ ውስጥ በ2ኛ ተሰ. 2:1-2 ወደ ተጠቀሱት መስካሪዎች እድንመለከት እፈልጋለሁ::

በዚህ ክፍል ስለ ጌታ ኢየሱስ መምጣትና ስለ ቅዱሳንም ወደ ጌታ መሰብሰብ የሚመሰክሩ ሦስት ክፍሎች ተጠቅሰዋል:: እነርሱም፣



10.10.1. መንፈስ ቅዱስ (ትንቢት)
10.10.2. ቃል (ተናጋሪዎች፣ ሰባኪዎች)
10.10.3. መልዕክት (የሚጻፉ ደብዳቤዎች) ናቸው::

### 10.10.1. <u>መንፈስ ቅዱስ</u>

በሮሜ 8:14-16 እንደተጠቀሰው አንድን አማኝ (ቅዱስ) የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚመጣው ነገር ሊነግረው ይችላል:: ዮሐ. 16:13 በዚህ ክፍል የሚመጣውንም ይነግራችኋል ይላል:: ሰው መንፈሱ ከኃጢአት ነጽቶ ትንሳኤን ካላገኘ ከእግዚአበሐር መንፈስ ጋር ግንኙነት አይኖረውም:: የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ለመስማት ከኃጢአት ተጽዕኖ መላቀቅ ያሻል:: ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በትንቢት ወይም በማይነገር መቃተት ተናግሮ ይመራዋል::

### 10.10.2. <u>የተናጋሪዎች (ሰባኪዎች) ቃል</u>

በአሁኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ አገልጋዮች እግዚአብሔር አሉት:: ወደፊትም ይመጣሉ:: በምድረበዳ እንደጮኸው መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን ምጽዓት የሚናገሩ በሐጢአት የሚኋዙትንም የሚገስጹ ባሪያዎች አሉ:: የእነርሱንም ምስክርነት ጠጋ ብሎ በማማከር መቀበል ያሻል::

### 10.10.3. <u>መልዕክት</u>

በአሁኑ ዘመን በጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍት በኩል ብዙ መንፈሳዊ ጽሑፎች ይወጣሉ:: የእነርሱንም ምስክርነት ማዳመጥ እጅግ ይጠቅማል::

እዚህ ላይ በማሳሰቢያነት ልጠቅሰው የምወደው ነገር አለ:: ይኸውም የሰይጣን አገልጋዮችም በእነዚህ በሦስቱና በሌሎችም ሊጠቀሙና ሊያምታቱ እንደሚችሉ ነው:: እውነትን ለሚፈልግ ሰው ከላይ በጠቀስኳቸውም ሆነ

በሌሎች እግዚአብሔር ሲመሰክርለት ቢያንስ የሦስቱ ልክ ከሆነ የሚቀጥለው የቀደመውን ያጸናል:: ግን እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላውም ሲናገር ማስተዋል ያሻል :: ኢዮብ 33:14:: በህይወትህ ስትጓዝ በውስጥህ መንፈስ ቅዱስ በማይነገር መቃተት ሊናገርህ ይችላል:: ያንን ድምጽ ወደ ልብህ ልታመጣው ትችላለህ:: እየተጓዝ(ሽ)ክበት ያለው የህይወት መንገድ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በውስጥ መንፈስህ ሰላምን፣ ደስታንና ኃይልን በመስጠት እንድትጓዝበት ያጸድቅ(ሻ)ሃል:: ያበረታታሀል:: ነገር ግን በተበላሸ ጐዳና እየሄድክ ከሆነ ሁልጊዜ ያለማቋረጥ የሚሰማህን ስሜት ይልካል:: ይህም ..የበደለኝነት ስሜት.. ይባላል:: ልብ እናድርግ! የበደለኝነት ስሜት ማለት እየተጓዝንበት ያለው መንገድ ልክ አለመሆኑን የሚያመለክት ማለት ነው:: እውነትን ፈልገህ ስታገኘው ስትጓዝበትም ሰላምና ጸጥታ ይሰማሃል:: ያኔ የበደለኝነት ስሜት ካንተ ይለያል::

የመነጠቅ ቀን እጅግ ቀርቧል:: ጌታ ኢየሱስ ወንዶችና ሴቶች ቅዱሳኑን ሊወስድ ቶሎ ይመጣል:: ለመነጠቅ ከፈለግን ከላይ ከቁጥር 1-10 ያሉትንና ሌሎችንም እግዚአብሔርን መስለህ እንድትጓዝ የሚረዳህን መንፈሳዊ መመሪያዎች ልትከተል ይገባል:: እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጅ መሆን ያሻል:: ያኔ ብርሃን ይበራልሃል::ከምታፍርበትም ምናምንቴ ሁሉ ታመልጣለህ:: ፀጋ ይብዛልን:: አሜን!!!



# ክፍል አሥራ አንድ

## መነጠቅን የምንናፍቅበት ምክንያቶች

እግዚአብሔር በዕውቀቱና በሁሉንቻይነቱ ፍፁም ነው:: ሁሉን በሚያውቅ ማንነቱ ስለማይጠራጠር ተስፋ ይሰጣል:: የሰጠውንም ተስፋ ይፈጽማል:: እርሱ የሚሰጠውም ተስፋ ፍፁም በረከት ያለበት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉት 6208 ትንቢቶች ውስጥ ዋነኛው ጌታ ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያቱ ስለመነጠቅ የተናገሩት ነው:: ዩሐ14:1-3፤1ተሰ.4:17:: መነጠቅ አማኞች በሙሉ ሊናፍቁት የሚገባ የሕይወት ልምምድ ነው:: ስለሆነም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አኳያ አማኞች ልባቸውን በመነጠቅ ላይ ሊያኖሩ ይገባል::

እውነተኛ ዳግም ልደትን ያገኙ ክርስቲያኖች በሙሉ መነጠቅን ሊናፍቁ ይገባል ምክንያቱም:-

### 11.1. <u>ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠው ህያው ተስፋ ስለሆነ ነው::</u>

ጌታ እየሱስ በምድር ቆይታው ለደቀ መዛሙርት እጅግ የተከበሩ ትምህርቶችን አስተምሮአቸዋል:: ካስተማራቸውም ውስጥ አንዱ የእርሱን መሄድ አስበው ሲያዝኑ በጊዜው ተመልሶ መጥቶ ሊወስዳቸው እንደሚችልም በማጽናኛ ቃል መናገሩ ነው:: ስፍራን ካዘጋጀ በኋላ «ወደ እናንተ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ.14:1-3) ማለቱ ታላቅና ክቡር ተስፋን መስጠቱ ነው:: ይህ ቃል ለዘመኑ አማኞችም የሚያስተላልፈው ዕውነት አለ:: ክርስቲያኖች የጌታን መሄድ ሲያስቡ መመለሱንም ይናፍቃሉ:: ይህ ተስፋ በእርግጠኝነት ተሰጥቷቸዋል:: ተስፋውም እነዚህ ቃሎች የታመኑና ዕውነተኛዎች ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ የታመነና ዕውነተኛ ተስፋ ነው:: ስለሆነም ዳግም ልደትን ያገኙ ክርስቲያኖች በሙሉ ተስፋው እስኪፈፀም ድረስ ዘወትር በጉጉት የመነጠቁን ቀን ሲጠባበቁ ይገባል:: ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠውን የተስፋ ቃል ቸል ማለት ወደ ሙሉው መርገም መግቢያ መንገድ

ነው:: ጌታ በዘህ ቸልታ ምንም አይደሰትበትም:: ክርስቶስ የሰጠውን ተስ
መጠበቅ ጌታን የማክበሪያው አንደኛውና ትልቁ መንገድ ነው:: አሜን!!

## 11.2. ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ ለመግባት

ነብዩ ዳንኤል ከመልዓኩ ገብርኤል ስለ 70ኛው ሱባኤ መልዕክት ተቀብሏል:: 70ኛው ሱባኤ ሲያልቅ ለእስራኤላውያን የሚፈፀሙላቸው ስድስት ልምምዶች ተጠቅሰዋል /ዳን9:24/ እነዚህም ልምምዶች የአመፃ ማብቃት፣ የኃጢአት መፈፀም /ማለቅ/፣ የበደል መስረይ፣ ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ መግባት: የራዕይና ትንቢቶች መታተምና የቅድስተ-ቅዱሳኑ መቀባት ናቸው:: ይህም ማለት ሰባኛው ሱባኤ ሲያልቅ ስለ እስራኤላውያን የተነገሩት ትንቢቶችና የታዩት ራዕዮች በሙሉ ተፈጻሚነት ያገኛሉ:: ከኃጢያትም ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይለያያሉ፣ ኃጢያት መስራት ስለማይኖር የአይሁዶችም በደል አይቆጠርም፣ መተላለፋቸው በሙሉ ይደመሰሳል:: ምክንያቱም የሰቀሉትን ኢየሱስን ሙሉ በሙሉ አውቀውትና ተረድተውት ስለሚቀበሉት ከሰቀሉት ጌታ ም ጋር የሚኖራቸው እርቅ ሙሉ ስለሚሆን ዓይኖቻቸውም ስለሚበሩ ነው:: በተጨማሪም ሱባኤው ሲያልቅ የቤተመቅደሱ መረገጥና የቅድስተ-ቅዱሳንም መርከስ ይወገዳል፣በዚህም ዘላለማዊው ፅድቅ ውስጥ ይገባሉ:: ይህም ማለት ሁልጊዜ ልክ የሆነ ሥራ መስራት ሕይወት ውስጥ መግባት ማለት ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት ስድስት መሠረታዊ ሐሳቦች በሰፋት ቢተነተኑ ብዙ ማለት ይችላል:: ሆኖም ግን አንድ ሊተኮርበት የሚገባ ነገር አለ:: ይኼውም አይሁዶች /እስራኤላውያን/ ከጌታቸው ጋር ታርቀው ዘላለም ፅድቅ ውስጥ ሲገቡ አይሁድ ያልሆኑ ሌሎች ክርስቲያናዊ አማኞችም ወደ ዘላለም ፅድቅ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ይመቻቻል:: ይህም የሚሆነው መነጠቅ በሚፈፀምበት ጊዜ ነው:: በመነጠቅ ጊዜ ያንቀላፉት /የሞቱት/ አማኞች በማይሞት በማይበሰብስ ፣ በማያረጅ፣ ኃጢያት በማይሰራና በማይወድቅ አዲስ አካል ስለሚነሱ፣ ያልሞቱት ደግሞ በተመሳሳይ ሰውነት ስለሚለወጡ



ሁለቱም ወደ ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ ይገባሉ ማለት ነው:: ጊዜው ይርዘም እንጂ አህዛብም ካመኑ ክርስቶስ በምድር በሚነግስበት ጊዜ ይህ ዕድል ለእነርሱም ይደርሳቸዋል::

## 11.3. ከሰማይ /ከገነት/ ቅዱሳን ጋር ለመገናኘት

ከመጀመሪያው ፃድቅ ከአቤል ጀምሮ እስከ መጨረሻው ጋለሞታይቱ ደሙን የምታፈሰው ቅዱስ/ቅድስት/ ያለበትን ስፍራና ማንነታቸውን ማየት የሚቻለው በመነጠቅ ነው:: መነጠቅ ወደ ፃድቃን መንፈሶች መድረሻው ብቸኛው መንገድ አይደለም:: አማኞች በማንቀላፋት ወይም በመሞት እዚያ ይገባሉ:: ዕብር. 12፥22-24:: በገነት፣ በደስታ የተሰበሰቡ አእላፋት መላዕክት፣ በብሉይ ኪዳን ከታችኛው ገነት /የአብርሃም እቅፍ/ የተነጠቁና ወደ ሰማይ የተዘዋወሩ ቅዱሳን፣ የሁሉ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔርና ፍፁማን የሆኑ የፃድቃን መንፈሶች ወዘተ ይገኛሉ::ፍፁማን የሆኑ ፃድቃን መንፈሶች ስንል ከዚህ ከደካማው ሰውነት የተለዩና ኃጢአት መስራት የማይችሉ በዘላለም ቅድስና የተሞሉ ማለት ነው:: እነርሱ ያሉበት ቦታ ለመድረስ እያንዳንዱ አማኝ ማንቀላፋት ወይም መነጠቅ ይኖርበታል::

## 11.4. የክርስቶስን የሚመስለውን አዲሱን አካል ለመልበስ

አካል ሁሉ የተለያየ ነው:: ምድራዊ፣ ሰማያዊ፣ የሚሞት፣ የማይሞት፣ ተፈጥሯዊና ልዕለ ተፈጥሯዊ፣ ሰዋዊና እንስሳዊ፣ ወዘተ አካል ይገኛል:: ጌታ ኢየሱስም ሆኑ ሐዋርያቱ በተለይ የክርስቶስን ስለሚመስለው አካል ግልጽ አድርገው ተናግረዋል፤ ፅፈውማል:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን፣ የሚሞተውም የማይሞተውን ሊለብስ ይገባልና፣ ይላል:: 1ኛቆሮ15፥53::የምንለብሰው አዲሱ አካል ከክርስቶስ አካል ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በተጨማሪም በራሱ እንደሚሆን አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሰውነታችንን ይለውጣል ይላል ::ፊሊጵ3፥21:: ይህ የለበስነው አካል ደካማ ስለሆነ ኃጢአት ሲሠራ ሊሞትና ለአዳጋ ሊጋለጥ የሚችል ሲሆን: ከመነጠቅ /ከትንሳኤ/ በኋላ የምንለብሰው

አካል ግን የመሬት ስበት ሳይዘው በቀጥታ ወደ ላይ መውጣት የሚች ነው:: ሐሥ.1:9-11:: በሥጋ ዓይንም ይታያል:: የተዘጋ በር፣ጥቅጥ ሐይል፣ የሰው ተግዳሮት ሊቋቋመው አይችልም:: በአብ ፊት መቆ /መቀመጥ/ይችላል:: የፀሓይ ኃይልም ሆነ የኒውክለር የጨረር ሐይ ሊያቃጥለውና ሊያጠቃው አይችልም:: ከተፈጥሮም ሆነ ከሰው ሰራሽ ኃይ ውጪ መሆን የሚችል ነው:: ስለሆነም መነጠቅን የምንናፍቀው ያ አስደና የክርስቶስ አካል ምን እንደሚመስል ለማየት ነው::

## 11.5. በሞት ላይ ለዘላለም ለመንገስ

በዘመናት መካከል የሰዎችን ልጆች ሲያንቀጠቅጥ የኖረው ሞ ከቅዱሳን ጋር ያለው ግንኙነት ለዘላለም የሚቋረጥበት ዘመን ይመጣል ሞት የቁም፣ የአካልና የዘላለም/የነፍስ/ ተብሎ በሦስት ይከፈላል:: መነጠ ከሦስቱም የሞት ዓይነቶች ይታደጋል:: አንድ አማኝ አንዴ ከተነጠቀ ማንነ ከእግዚአብሔር ጋር በሕይወትና በዕርቅ ስለሚኖር የዘላለም ሞት አያገ ውም:: ከዚህም የተነሳ ነው ጳውሎስ ክርስቶስ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋ ቅዱሳን ሲያንቀላፉ ወይም በቅጽበተ-ዓይን ሲለወጡ *ሞት ለዘላለም ተዋ* ያለው:: መነጠቅ አማኝን የሞት ወዳጆችና አጃቢዎች ከሆኑት ከሲኦልና ከኃጢአት ለዘላም ይለያል:: ስለሆነም የተነጠቀ አማኝ በክርስቶስ አማካኝነት በሞት ላይ ነግሦአል ማለት ነው::1ኛቆሮ15:54:: አንድ ቅዱስ ሲነጠቅ በክርስቶስ የሆነውን ድል ተቀዳጅቷል ማለት ነው:: /ቁ. 57/ አማኝ ሲነጠቅ የሚቀበለው ታላቅና ክቡር ስጦታ «ድል *መንሳት*» ይባላል:: አማኝ ሲነጠቅ ሰይጣን ከአማኙ የግል ሕይወት ይናፍቅ የነበረውን ድል ነሺነትሙሉ በሙሉ ያስረክባል:: እንደ የአስቆሮቱ ይሁዳና ዴማስ ይጠባበቀው የነበረውን የአማኝ -ን ውድቀት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያጣል:: ሰይጣን ድል መንሳቱ ይቀርና ድል ይደረጋል/ባለድል መሆንን ሙሉ በሙሉ ይከለከላል/:: ስለሆነም ይህን ክቡር ህይወት ለመቀዳጀት ዘወትር መነጠቅን መናፈቅ ይኖርብናል::



## 11.6. በመፅናናት ለመኖር

በቅድመ መነጠቅ ያለው ሁኔታ በቀላሉ የሚኖርበት አይደለም:: አስጨናቂና የምጥ ጣር መጀመሪያ ጊዜ ነው:: ማቴ24፥6-7፤2ኛጢሞ3፥1:: ሁሉ ነገር ወደ ፍፃሜ የሚቸኩልበት ጊዜ ስለሆነ ትርምስ፣ ስቃይ፣ ዕልቂት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ መተላለቅ፣ ሥጋዊነት ወዘተ የሚበዛበት ዘመን ነው:: ያለው የፖለቲካ ይዘት፤የኤኮኖም ሁኔታ፡ የተፈጥሮ አደጋ ክስተት፡ ችነፈሩ፤ጭንቀቱ፡ ረሀቡ፡ የምድር ነውጡ፡ የአውሎንፋሱ አደጋ፡ የህዝብ በህዝብና የመንግስት በመንግስት ላይ መነሳት፡ የፍቅር መቀዝቀዙ፡ ወዘተ በጣም የሚያስጨንቅ ነው:: ስለሆነም በወቅቱ ያለውን ሁኔታ ተቃቁሞ በመጽናናትና በመኖር በዩሐ.14:1 እንደተጠቀሰው ወደ ተዘጋጀልንም ሥፍራ ለመድረስ የምንናፍቀው መነጠቅን በመጠበቅ መሆን አለበት:: መጽ/ቅዱስ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተፅናኑ ያለው፡ በደመና እንነጠቃለን የሚለውን ቃል በማለብ ነው:: /1ተሰ4፥17-18/:: ብዙ የሚያውክ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ሲመጣ መፍትሄው የመነጠቅን ቀን መናፈቅ ነው::

## 11.7. ራስን በቅድስና ለመጠበቅ

ጌታ እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ብሎአል:: ይህ የቅድስና ሕይወት እግዚአብሔርን ከምንመስልባቸው መንገዶች/መልኮች ውስጥ ዋነኛውና አንዱ ነው:: ቅዱስ በመሆን በጌታ ቤት መኖር በዘላለም ቅድስና የኖረውን ፈጣሪአችንን ለማየት እንድንናፍቅ ያደርገናል:: ቅድስና በአማኞች ህይወት ከሚያነሳሳባቸው ዋና ነገሮች ውስጥ ዋነኛው እግዚአብሔርን እንድናይ ማስናፈቁ ነው:: ዕብ12፥14:: አማኞች በሙሉ በቅድስና ሲኖሩ «እኛ አገራችን ከሰማይ ነው» /ፊሊጵ.3፥20/ ማለትን ሁልጊዜ ይለማመዳሉ:: ለመነጠቅ የሚናፍቀው ሰው ሁልጊዜ ራሱን በቅድስና ይጠብቃል:: ምክንያቱም የማይነጠቁ ፈሪዎች፣ ውሾች (የእግዚአብሔርን የሚመስሉ የሰይጣን አገልጋዮች)፣ አስማተኞች፣ ነፍሰ ገዳዮች ወደ ከተማይቱ የመግባት ዕድል ስለማይኖራቸው ነው:: ራዕይ 21:8::

### 11.8. ጌታ ያዘጋጀልንን ቦታ ለማየት

መነጠቅን እንድንናፍቀው የሚያደርገን ጌታ ያዘጋጀልንን ሥፍ ሲያሳየን የሚችል መንገድ በመሆኑ ነው:: ጌታ ኢየሱስ «በአባቴ ቤት ብ መኖሪያ አለ ሥፍራን አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ» ብሏል::ዮ.ሐ14፥1-3 ይህ የተዘጋጀልን ስፍራ ቅዱስ ስፍራ ነው:: ኃጢያት፣ ሞት፣ ሐዘን፣ ችግር የተፈጥሮ ቀውስ፣ ህመም፣ ማጣት፣ አደጋ (የአካል ጉዳተኝነት) ጦርነ ወይም ማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር የለበትም:: ዛሬ በምድራች የምናያቸወና የምንሰማቸው የቀውስ ዓይነቶች፤የፖለቲካ ተፅዕኖ፣ ዘረኝነት የፆታ ግጭት፣ የሰው ስጋ መብላት፣ ድህነት ወዘተ በሙሉ በሰማይ አይገ ም:: በዚያ ስንኖር፡ በዚህ ምድር ጣታችን ወይም አንገታችን ላይ ለጋብ በቀለበትነት ወይም በሐብል መልክ ለመጠቀም ጣርና ውድ የሆነብን ወር በተዘጋጀልን በሰማይ የእግራችን መቆሚያ ይሆናል::ራዕይ 21:18-19:: ጌ ባዘጋጀልን በሰማያዊ ስፍራ ከወርቅ ይልቅ እጅግ የከበሩት እንደ ወራውሬ ያክንት፣ክርስጵራስስ፣ በሉር፤አሜቴስጢኖስና የመሳሰሉት ክቡ ድንጋዮች/እንቁዎች ይገኛሉ:: ራዕይ 21፥19-20:: መነጠቅን መናፈቅ ያለብ ይህንን የከበረ ስፍራ ለማየት ነው::

### 11:9. ጌታ ኢየሱስን ለማየት

ለብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ የተተረከለት ያ ልዩ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ምን ይመስል ይሆን? እስከ ዛሬ በቢሲየን የሚቆጠሩ ታሪክ የተተረከላቸው ብዙ ኀያላን ነበሩ፤ ነገስታትን፡ መሪዎችን፡ አየን ታሪካቸውንም ሰማን፤ ገድላቸውንም አነበብን፡ ሞተው ግን መነሳታቸውንና ሰይጣንንም ሆነ ተከታዮቹን ሲያንበረክኩ ፈጽሞ አላየንም፤ አልሰማንምም:: ታሪካዊው ጌታ ኢየሱስ ግን ይህንን ማድረግ ችሏል:: ያንን የዓለም ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች ሲያነፁት ያልቻሉትን ኃጢአቴን በከበረው ደሙ ያጠበውን ከቃሉ መረዳትና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ዳግም ልደትን ያስገኘ ልንን፣ አባ አባት ብለን እንድንጮህ የልጅነት መንፈስ የሰጠንን ፣ ከሠይጣን ልጅነት ወደ እግዚብሔር ልጅነት የለወጠኝን፣ ከጠላቶቻችን ከአጋንንት ኃይል



ያላቀቀንን፣ ከአውሬው ዕጣ ፈንታ ነፃ ያወጣንን፣ ያዳነንን፣ ከውርደት ወደ ክብር ያሸጋገረንን፣ ያንን ክፉ ሳይሰራ ሲሰቃይ የሚያደረጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት ማንም ሲገልጽ ያልቻለውን ፍቅር በመስቀል ላይ የገለጠውን አፍቃሪና ለራሱ ያልሣሣውን ቸሩን መሲህችንን ጌታ እናየዋለን:: አዳኝነቱን ርህራሄውን ወሰን የሌለውን ጥልቅ የሆነ ፍቅሩን ብቻ ሣይሆን ሁለንተናውን ከዘላለም ክብሩ ጋር ሆኖ እናየዋለን:: ካልተነጠቅን ጌታን በሙሉ ክብሩ አናየውም:: በመነጠቅ ጌታን ለማየት ስንናፍቅ አብሮ የተያያዙ ልምምዶችንም እንፈፅማለን:: ለምሣሌ የጌታን መምጣት እናስቸኩላለን:: 2ኛ ጴጥ3፥12:: ጌታን ለማየት ከመናፈቃችን የተነሣ ስለመነጠቅ ባሰብን ጊዜ ለእኛ መገለጡን እናስቸኩላለን ማለት ነው:: በአጸደ-ሥጋ ስንኖር የመነጠቅ መለኮታዊ ስርዓት በህይወታችን ካላለፈ ጌታን አናየውም:: ስለሆነም ጌታን ለማየት መነጠቅን ልንናፍቅ ይገባል::1ተሰ4፥17::

### 11:10. የትንሣኤውን ኃይልና ምንነት ለማወቅ

ከሞት የተነሱ ቅዱሣንና ያንቀላፉ ቅዱሳን ሲለወጡ የሚለብሱት መንፈሳዊ አካል ተመሳሳይ ነው:: አንድ አማኝ ሲነጠቅ ወዲያው የክርስቶስን የሚመስለውን አካል ስለሚለብስ በትንሳዔ ያለውን ኃይል ይረዳል:: ትንሣዔ የመለኮት መንገድና አሰራር ነው:: ትንሳዔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከአስፈሪው ጠላት የመሰያያ አድማስ ነው:: መነጠቅ ሲሆን መለወጥ፣ መለወጥም ሲሆን የትንሳዔው ኃይል በዚያ ይታያል:: ለዚህ ነው በራዕይ 20:4-6 በፊተኛው ትንሳኤ ዕድል ፈንታ ያለው ብጹዕ ነው የተባለው:: ክርስቶስንና አዲሲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን እንድናይ ሥልጣን በሚያስጨብጠን ትንሳኤ ተሳታፊ ከመሆን የበለጠ ምን ደስታ አለ?

### 11:11 ተስፋ መቁረጥን ለመቋቋም

አበውም ሆኑ የዘመኑ ምሁራን ሲናገሩ «ከስህተት ሁሉ የከፋ ስህተት ተስፋ መቁረጥ ነው» ይላሉ:: ይህ አባባል ከታሪክም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አንጻር ሲታይ እውነትነት አለው:: እውነተኛ ተስፋ የተገኘ ህይወትን

እንደሚያስመልም ምግብ ነው። በአንፃሩ ደግሞ ተይዞ የነበረው ተስፋ ሲጠፋ ወይም ሲቆረጥ ያንኑ ያህል አጥንትን ያነቅዛል። የሰው ተስፋው ሲሞት ሕይወቱም አብሮ ሊሞት ይችላል። ስለሆነም ክርስቲያን በሕይወቱ ያለው የዘላለም ህይወት ተስፋ ተሚጥጦ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳይወድቅ ሁልጊዜ የመነጠቅን ቀን መጠበቅ ይኖርበታል። ተስፋ ሲባል ደግሞ ዓይነቱ ብዙ ነው። ተስፋ ሲበዛ እውነተኛ ተስፋ ላይሆን ይችላል። ኦሌ ኤሪክሰን <u>«የአንድ እራኝ ንግግር»</u> በተባለው ፅሁፋቸው ስለብዙ ተስፋ አደጋ « ተስፋ መቼም ተስፋ ነው፣ ብዙ ተስፋ ግን ምናምን ባዶ ከንቱና የሚሸነግል አለኝታ ነው» በማለት ፅፈው ነበር። ይህ እውነት ነው። የጠቢቡ ሰለሞን ተስፋ ብዙ በመሆኑ ነው አክባሪ ፈጣሪውን ለማንገሥና ለመታዘዝ ጊዜ ያጣው፤ በምድራዊ ቋንቋ መልካም ቢሆንም ብዙ ተስፋ አዕምሮን ይይዛል፡ ልብን ያከብዳል፣ የፀሎትንና የቃሉን የጥናት ጊዜ ይወስዳል። ብዙ ተስፋ እንደተስፋው ዓይነት ኀዘን ያበዛል። ልብንም ያከብዳል። ስለሆነም ተስፋ የተደረገበት ሁሉ የባለተስፋውን ህይወት ይቆጣጠራል፤በዚህ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች /አማኞች ከመባከናቸው የተነሳ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይወድቃሉ። ስለሆነም ወደ ራስ ማንነት የሚመጡትን ብዙ የተስፋ ዓይነቶች በመቆጣጠር ሁሉንም ተራ በማስያዝ ባመቺው ጊዜ ልንጠቀምባቸው ወይም ደግሞ ልንቃወማቸው ይገባል። ሆኖም ግን የጌታን በአየር መመለስና የመነጠቅን ቀን አጥብቆ የሚከታተል ክርስቲያን ራሱን ይቆጣጠራል፡ይገዛል፡ በመጠንም ይኖራል።

### 11:12. <u>ክፉን ፀንቶ ለመቃወም</u>

እውነተኛ ክርስቲያን መንፈሳዊ መታወቂያ አለው፤ይህም መታወቂያው የመስቀሉ ሕይወት ነው። መስቀሉን ተሸክሞ ዕለት ዕለት ጌታን የሚከተል አማኝ ዘወትር መልካሙን የዕምነት ገድል የሚጋደል ነው። ይህ ክርስቲያን ክፉ ኃይላትን በመቃወም ይመላለሳል። የተለያዩ ክፉ ቀናትና ልዩ ልዩ ፈተናዎች ሲገጥሙት ተቃውሞው ፅኑ ነው፤ የክፉን አሠራር በመቃወሙ ክርስቶስ ኢየሱስን ይመስላል። ንፅረተ-ዓለሙ (አመለካከቱ) ወጥና ስርዓት ያለው ነው። አይወላውልም። በክፉው ቀን ለመቃወም የሚያስችለው የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የለበሰና ሊለብስም የተዘጋጀ ነው። ኤፌ 6፥14-18። ክርስቶስ እንደሚመጣና እንደሚነጠቅ አምኖ የሚጠባበቅ አማኝ ኃይል ይኖረዋል። ከዚህም የሚወጣ ተስፋው ኃያልና ፅኑ ነው። የመስቀሉን ሕይወት አይጋፋም።



# ክፍል አስራ ሁለት

## <u>ማስጠንቀቂያ</u>

*<u>ማስጠንቀቂያ</u>* ከቶውንም ያለ ምክንያት አይሰጥም፤ ማስጠንቀቂያ ከሚመጣው ጉዳ ነገር ለማምለጥ፣ ራስን ለማዘጋጀት፣ ራስን ለማንቃት እጅግ ይጠቅማል። ማስጠንቀቂያ ነገሮችን በቅድሚያ ቀምሞ ለመደቆስ ያነሳሳል። ካስፈላጊውም የረብ ቦታ ያደርሳል። ማስጠንቀቂያ በማቴ. 24:39 ያላወቁ አለቁ ከተባለባቸው የኖህ ዘመን ሰዎች የከፋ ህይወት ያወጣል። ጌታ የሰጣቸውን የማትጊያ ንግግሮች (መልዕክቶች) እጅግ ልንጣበቅባቸው ይገባል።

### 12.1 <u>በአንድ ወፍጮና እርሻ ለምንሠራ</u>

ጌታ ኢየሱስ ከተናገራቸው አስደናቂ ትንቢቶች ውስጥ አንዱ በማቴ24:40-41 ያለው ነው። ቃሉም <u>በዚያን ጊዜ</u> ሁለት ሰዎች በእርሻ ላይ ይውላሉ፣ አንዱ ይወሰዳል ሌላውም ይቀራል ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ አንዷ ትወሰዳለች ሌላይቱም ትቀራለች የሚለው ነው። በዚህ ቃል ውስጥ በቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሀረግ «በዚያን ጊዜ» የሚለው ነው። ይህ ጊዜ የቱ ነው? ጊዜው የሎጥንና የኖህን ዘመን የሚመስለው የሰው ልጅ ዘመን ነው። ሉቃ 17:26-30። ወፍጮ እርሻና ህንጻ ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። በክርስትና እርሻ/ህንጻና ወፍጮ ላይ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንደሚኖሩ ያመለክተናል። 1ኛቆሮ3:9። በክርስትና እርሻ ላይ በመጨረሻው ዘመን አንዱ ወደ ጌታ ሊወሰድ ሌላውም ላይወሰድ የሚችል ሰው እንደሚኖሩ ያመለክተናል።

በአሁኑ ጊዜ በስመ ክርስትና ቤተ ዕምነት ብቻ ከ300 የሚበልጡ ንዑሳን ቤተ ዕምነቶች ተመሥርተዋል። ቤተ ዕምነቶቹ ሁለቱንም ዓይነት ፆታ ይዘዋል። ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ሁለቱም ዓይነት ሰዎች በአንድ ዓይነት ዕምነት ላይ ሆነው አንዱ ሲወሰድ ሌላው መቅረቱ ነው።

በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የሰዎች ወደ ፀሎት ቤት አመጣጥ አነሳሹ ኃይል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንጌልና እምነት አለመሆኑ ነው:: በፀሎት ቤት ውስጥ በአፋቸው አማኝ ነን እያሉ በድርጊት የድፍረት ኃጢያት የሚሠሩ፣ ለጥቅም ብለው የሚያመልኩ፣ ወላጆቻቸው አማኞች ስለሆኑ እነርሱን ለማስደሰት የሚፀልዩና የሚዘምሩ፣ የፀሎት ቤቱ አቀማመጥ ደስ ስላላቸውና ዕድሉ ስለተገኘ ለረጂም ጊዜ የሚመላለሱ፣ እጮኛ ፍለጋ የሚመጡ፣ ከቤተ ክርስቲያን የስጋ ጥቅም ለመግኘት የሚመላለሱ፣ በአጃቢነት የሚኖሩ፣ ጥሩ ጓደኛ ስላላቸው የሚያገለግሉ ወዘተ ይታያሉ::

ሰዎች ራሳቸውን እንክርዳድ ነኝን? እባብ ወይስ ጊንጥ ነኝን? ብለው መፍረድ ወይም በቃሉ ሥልጣን ማንነታቸውን ሊመረምሩ ይቸግራቸው ይሆናል:: ስለሆነም ከምክንያቶች የተነሳ ተመላስለው ሊኖሩ ይችላሉ:: በተፈጥሮ ቀልጣፋነታቸው ፕሮግራም መሪ፣ ባለዕውቀት በመሆናቸው ሰባኪ የሆኑ፤ የሙዚቃ መሣሪያ የመጫወት ችሎታ መያዛቸው የአምልኮ ወይም የመዘምራን ቡድን መሪ መሆናቸው አገልጋይ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ሆኖም ግን ትክክለኛውን የድነት ህይወት አላገኙት ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ነው ጌታ መጥቶ የራሱ የሆኑትን ሲወስድ ሌሎች ባሉበት የሚቀሩት:: ይህ ምንኛ አሳዛኝና ምስኪንነት የበዛበት ህይወት ነው?

ስለሆነም በስመ ክርስትና በየቤተ-ዕምነቱ ያለን ክርስቲያን የተባልንና ነን! ነኝ! ብለን የምናምን አጥብቀን ልንጠይቀውና ሳንንሳፈፍ በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ስለማንነታችን ለምንጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ልናገኝለት የሚገባ ነገር እንዳለ ሊተኮርበት ይገባል:: ይኸውም የኋለኛው መለከት ቢነፋ በቅጽበተ-ዓይን ከሚለወጡት ወይም በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ፈንታ ከሚኖራቸው ክፍል ነኝ ወይስ አይደለሁም? ለሚለው ጥያቄ በእርግጠኝነት መልስ ማግኘቱ ላይ ነው:: የመነጠቅ ጉዳይ ዕውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ መሆኑ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ ብሎ መነጠቅ አለመነጠቁን የሚያውቀው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ



ው ማለት ከተጠራጣሪነት ተለይቶ ሊታይ አይችልም:: አንድ ሰው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካል ውስጥ እንዴት መግባት ይችላል? ሰው መዳኑ እርግጠኛ መሆን ይችላል? ለመነጠቁስ? ለእነዚህ ጥያቄዎች መጽ/ቅዱስ ግልፅ መልስ ይሰጣል:: ስለሆነም ሬጋ ብሎ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ልብንም ሰፋ አድርጎ ቃሉን በቀንና በሌሊት በመመርመር ርግጠኛ የሆነውን ነገር መረዳት ተገቢ ነው::

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የክርስቶስ ተከታዮች ወይም የክርስትና ዕምነት ተከታዮች በቤተ ዕምነት ደረጃ ዋነኞቹ ከ300 በላይ ደርሰዋል፣ ንስተኞቹ ወደ ሺህ የሚደርሱም አሉ:: ለምሳሌ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት፣ ሜተዲስት፣ ካቶሊክ፣ አርቶዶክስ፣ ተሃድሶ አርቶዶክስ፣ተሃድሶ ካቶሊክ፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ አድቬንቲስት፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ የጂሆቫ ምስክሮች፣ ሐዋርያት ወዘተ በሙሉ በክርስትና ዕምነት ሥር ይመደባሉ:: ጥቂቶች ባይቀበሉም ሁሉም በክርስትና ወፍጮ ላይ ወይም ህንጻና እርሻ ላይ ይሠራሉ:: መለከት ሲነፋ ከውስጣቸው የሚነጠቁ ሲኖሩ የማይነጠቁ አሉ ማለት ነው፡ በቤተ ዕምነቱ ሥር ሆነው እንዴት ሳይነጠቁ ይቀራሉ? ለዚህ መልሱ ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸውን ልምምዶች መመልከቱ ይጠቅማል:: ባጭሩ ግን ለመመለስ የክርስትና ዕምነት ተከታይ አባላት ሦስት ዓይነት ክርስቲያኖች መኖራቸውን ልብ ማለት ነው::

አንድ ክርስቲያን 1. ፍጥረታዊ 2. ስጋዊ/ነፍሳዊ/ 3. መንፈሳዊ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል:: *ፍጥረታዊ ክርስቲያን* ስንል ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተዋሃደ /በተቀናጀ/ አሠራር ህይወቱ ያልተመሠረተ ነገር ግን እንደተወለደ በስም ክርስቲያን የተባለ ሆኖም ለሰው በማይታይ ለእግዚአብሔር ግን በሚታይ ሁኔታ ክፉ የሚሰራ እርሱ ፍጥረታዊ ክርስቲያን ይባላል:: ይህ ሰው ሐጢአትን እንደውኃ ይጠጣል እንደ እንጀራ ይበላል:: አስገዳጅ ሁኔታ በተፈጠረበትና ባመቸው ጊዜ ክፉ ስራን መስራት ትክክል እንዳይደለ እያወቀና እየተረዳ ያልፈለገውን ክፉ ስራ ይሠራል::

አስመስራትን አይችልም። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስላሌለው ነው። ሐሥ. 2:1-4፣1:8፣ሉቃ. 24:49። ያምናል ዕምነቱ ግን ፊር የሰቀቀ ነው። በዚህ ዓይነቱ ሰው የፈሪሃ እግዚአብሔር ማንነት ዘወትር ባጠገቡ እንዳለ አይሰማውም። ስለሆነም እንደተፈጠረ ያለ ነው በሐሳቡ ግን ክርስቲያን ነኝ አማኝ ነኝ ጌታን አፈቅራለሁ፣ እወደዋለሁ ሲል ይችላል ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ ክርስቲያን ገና ንስሀ ያልገባ ፍጥረታዊ ሰው ነው። ስለሆነም አልዳነም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ቋንቋ ንስሀ ሦስት ክፍሎች በቅደም ተከተል ይያዛል። ይኼውም 1. _ኃጢያተኛ መሆንን ማወቅ ነው፡_ ይህም የኃጢአት ሰንኮፍ ገና በማህፀን ሳለ በተፈጥሮ አብሮት የተወለደና የኖረ መሆኑን እስካለው የህይወት ደረጃ በሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆኑትን እንዳሳዘነ ገብቶት መልሶ ጌታውን በማስቀጣቱ የተፀፀተ ማስት ነው2. በኃጢአቱ ካዘነና ከተፀፀተ በኋላ ወደ እግዚአብሄር በሠራው ክፉ ሥራ _የተናዘዘ ወይም ኃጢያቱን ለጌታው የተናገረ_ 3. በኃጢአቱ ተፀፅቶ ከተናዘዘ በኋላ ከኃጢአት ለመራቅ ወስኖ ወደፊት _ከሐጢአት ለመራቅና በቅድስና ለመኖር ውሳኔ ያደረገ_ ሰው ንሥሀ ገብቷል ይባላል።

ይህ ሰው /ወንድም ሆነ ሴት/ ከእግዚአብሄር ጋር እርቅ ያደረገና ከጥንተ-አብሶ /ውርስ ኃጢአት/ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የታጠበ ከመሆኑም በላይ ሰይጣናዊ ኃይላት /ሰይጣንና አጋንንቱ በማንነቱ ላይ ሥልጣን የሌላቸው ነው። በመስኮታዊ አሠራር የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በየትኛውም የክርስትና ዕምነት ሥር ባሉ ቤተ ዕምነታት ስር ቢኖርም ይህ ሰው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ይነጠቃል። በአንጻሩ ግን በሐጢአት የሚኖርና በርኩሰት የሚመላለስ ከሆነ በተመሳሳይ ቤተ ዕምነቶች ውስጥ ቢሆንም የስም ክርስቲያን ስለሚሆን የመነጠቅ እድል አይገጥመውም።



*ማንኛውንም የዚህ ዓይነት ክርስቲያን እንዳይነጠቅ የሚያደርገው ፍጥረታዊ ክርስቲያን መሆኑ ነው።* ሁለተኛው የክርስቲያን ዓይነት *ስጋዊ ወይም ነፍሳዊ* የምንለው ክርስቲያን ነው። ሥጋዊ ክርስቲያን ክርስቶስን አምኖ፣ ንስሀ ገብቶ ወደ ቅድስናው ሙላት ለመድረስ ትግል የሚያደርግ ሲሆን ከመንፈሳዊ ልጅነት፤ ካለማወቅና ከድካም የተነሳ ኃጢአትን የሚለማመድ ነው። ይህም ቢሆን ንስሀ ይገባል። በሠራው ሥራ ነፃነትና ሰላም አይሰማውም። ይፀፀታል። የነዚህን የሁለቱንም ዓይነት ክርስቲኖች ታሪክና ልምምድ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንና ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ህይወት መረዳት ይቻላል።1ኛቆሮ3:1-4። የዚህ ዓይነቱ ሰው ኃጢአቱ ስለተሰረየለትና አባ አባት ብሎ የሚጠራበት የልጅነት መንፈስ ስለተሰጠው መለከት ሲነፋ ይነጠቃል።

ሦስተኛው *መንፈሳዊ ክርስቲያን* የምንለው ነው። ይህ ሰው በመንፈሳዊ ህይወቱ ያደገ፣ የጠነከረ፣ የፅድቅን ቃል ለይቶ የሚያውቅ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሚታይበት፣ በመንፈሳዊ ጉዳይ የሚተጋ፣ ፈጣሪውን የሚያገለግልና ዕውነተኛ የሆነ ነው። 1ኛ ቆሮ2:6-16። ይህ ሰው የኋለኛው መለከት ቢነፋ ይነጠቃል። አንድ ክርስቲያን ከሦስቱ የክርስቲያን ዓይነቶች ውስጥ የትኛውን እንደሚመስል ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ ይህም ይቻላል። እንግዲህ ክርስቲያን ነኝ ባይ ሁሉ ልብ ሊለው የሚገባው ምስጢር ያለው እዚህ ላይ ነው። የአንዲቱ መወሰድ የሌላዪቱም መቅረት ወይም የአንዱ መነጠቅና የሌላውም መቅረት ምሥጢር ጉዳዩ ያለው እዚህ ላይ ነው።

## 12.2 የልብ መክበድ

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲኖር ለደቀመዛሙርቱ ካስጠነቀቃቸው ዕውነቶች ውስጥ አንዱ በምድራዊ ነገር ልባቸው እንዳይከብድ ማስተማሩ ነበር ሉቃ. 21:34። ጌታ ስለትዳርም በማለብ ልባችሁ እንዳይከብድ ሲል የሚያውቀው ምሥጢር መኖሩን ያመለክተናል። አንድ የመኪና ባትሪ ሲሰራና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ ባትሪው ኃይሉን ቢቀንስ እንዲሰራ ቻርጅ

ይደረጋል/ኃይል ይሞላል/ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ወንድም በምድራዊ ነገር ልቡ ከበደ ሲባል በምደራዊ ነገር ቻርጅ ተደረገ ወይም የሕይወቱን አብላጫ ክፍል ለምድራዊው ነገር አዋለ ማለት ነው:: አንዲት እህት ወይም ወንድም ልቧ ከበደ ሲባል አማኙ በግልም ሆነ በቡድን 1. ለመፀለይ 2. ቃሉን ለማንበብና ለማጥናት 3. ወደ ፀሎት ቤት ሄዶ ለማምለክ ማለትም ለመፀለይ፣ ለመዘመር ርዳታ ለማድረግ፣ ለሌለው ለማለብና ለመለገስ፣ ለማያዊውን በረከትና ህይወት ለማሰብ ጊዜ አጣች ማለት ነው:: ስለ ትዳር በማሰብ ሲል ትዳር የሚያመለክተው ትንሽ ልጅም ይሁን ትልቅ ለው ለምድራዊ ኑሮ የሚከፍለው ማናቸውም ዓይነት ዋጋ ተግባርና እንቅስቃሴ ነው:: በቀድሞ ዘመን ትዳር ሲባል ሁለት ተቃራኒ ፃታዎች ተጋብተው አብረው መኖር ሲጀምሩ ነበር:: ሆኖም ግን ትዳር ማለት ያላገቡም ሆኑ ያገቡ ሰዎች የዕለት ዘላቂ ኑሮአቸውን ለማከናወን የሚወሰዱት እንቅስቃሴዎችና ተግባራት ናቸው::

ከበደ ማለት ወደ ታች ተሳበ ወይም ሚዛን ደፋ ማለት ነው፤ የሰው ልቡ ማለትም ዝንባሌውም ሆነ ስሜቱ መረዳቱም ሲከብድ ከምድራዊ ነገር ጋር ሲተሳሰር መንፈሳዊነቱ ይወድቃል፣ ዕውነተኛነትን ይጥላል፣ በመቀጠልም አንድ ጊዜ ወደ ዓለም ሌላ ጊዜ ደህሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያያል፤ በነገርም ገቢ ይሆናል:: ግድየለሽና ትህትና የተለየው ይሆናል፤ አንድ ቀን እንቅፋት የሚጥለው መሆኑን ይዘነጋል:: ንፁህ ወይም ቅዱስ አድርጎ ራሱን ሲቆጥር በውስጡ ግድፈት መኖሩን ይዘነጋል:: ተመስገን ጌታዬ ሞላ ጎተራዬ ከማለት ይልቅ ተመስገን ሆዴ ሞላህ ብሎ ፈጣሪውን አናንቆ ሆዱን ያሞካሻል:: እውነተኛ አምላኩን ሲከፋው አይገድደውም፤ሆዴን ብቻ አይክፋው! ይላል:: የዚህ ዓይነት ሰው በምድር ስለመረፈቅ ዘውታሪ ስለሆነ ስለመነጠቅ ማሰብ ጉዳዩ አይደለም:: ለዚህ ሳይሆን ይቀራል መንገድ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ልባችሁ እንዳይከብድ ያለው! ***በከበደ ልብ ብዙ መሰኮቶችና በሮች ለሰሚኖሩ የሚመላለሱበት ይበዛል***:: መመላለሻ ከሆነ ደግሞ ይረገጣል፤ ነፃነት የሚጠፋው እዚህ ላይ ነው ስለሆነም ልባችን አይክበድ!!



## 12.3 የመራቅና መቅረብ ክስተት

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና በከፍተኛ ደረጃ ከሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች አንዱ «ከእነዚህ ደግሞ ራቅ» የሚለው ነው:: በአንድ በኩል መራቅ ካለ በሌላ በኩል ደግሞ መቅረብ ይኖራል:: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ከምን መራቅ እንዳለባቸው አጠንክሮ ገልጾአል:: ለምሳሌ በ2ኛጢሞ 3:1-9 ጳውሎስ ከ25 የማያንሱ የመጨረሻው ዘመን ሰዎችን የኃጢአት ልምምዶች ይዘረዝርና ቁ.5 ላይ ከነዚህ ደግሞ ራቅ ይለዋል:: ይህ ራቅ የሚያመለክተው ከሰዎቹ ተለይቶ ገዳም መግባትን ሳይሆን እዚያው አጠገባቸው ሆኖ እንደሎጥ በኃጢአት ሥራቸው ፃድቅ ነፍስን እያስጨነቁ በኃጢአት ሥራቸው ሳይተባበሩ መኖርን ነው:: 2ኛጴጥ2:7-8፤ቲቶ.3:9-11:: ክፉና መልካም፣ ኃጢአትና ፅድቅ፣ ሰይጣንና እግዚአብሔር ፍፁም ተቃራኒና የማይታረቁ ማንነቶችና ክስተቶች ናቸው:: እንደዚሁም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ቅርፃዊ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ይዘታዊ ልዩነታቸው ከፍተኛ ነው:: ያላቸው የይዘትና የዓላማ ልዩነት በመሐላቸው ያለውን የግንኙነት ርቀትና ቅርበት ይወስነዋል:: ወደ ሰው ለመቅረብ ተብሎ ከእግዚአብሔር አይራቅምና:: ምክንያቱም አደጋ ስላለው ነው::

መዝሙረኛው ዳዊት «እነሆ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና፣ ከአንተ ርቀው የሚያመነዝሩትንም ሁሉ አጠፋሃቸው» ሲል ከእግዚአብሔር መራቅ በቀጥታ የጊዜአዊውንም ሆነ የዘላለማዊውን ጥፋት እንደሚያመጣ ተረድቶአል:: ስለሆነም የወሰነው «ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» በማለት ነበር:: መዝ. /73/:27-28:: ስለመቅረብና ስለመራቅ ስናስብ አንድ አስቸጋሪ ነገር አለ:: ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስና በድህረ-ቤተ ክርስቲያ ምስረታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሰዎች ወድደው ነው ከእግዚአብሄር ርቀው የጠፉት? አውቀው ይሆን ፈጣሪያቸውን የካዱት? ወይስ ደግሞ ሃሌ ሉያ እያሉ እየዘመሩ ሆኖም የተቦረቦሩ፣ የሰበኩ ሆኖም በጌታ ያልረኩ፣ ቃሉን ያስተማሩ ሆኖም በክፋት የመረሩ ብዙ አይደሉምን?

ሰው በቀን ከ3 እስከ 5 ጊዜ ለስጋው እንደሚበላ ሁሉ ከፈጣሪውም ሳለመራቅ ለመንፈሳዊ ህይወቱም በተከታታይ መመገብ አለበት:: ሲበላም እንጀራውን በመራራ ቅጠል የመብላትን ያህል ወይም በአፉ ቃሉ እየጣፈጠው በሆዱ መምረሩን እየተገነዘበ መመገብን ሳይረሳ መሆን አለበት:: ራዕይ10:8-11:: በዘመኑ ክርስትና ሴቱ ሆያሆዬ ወንዱ አበባየሆይ የሚል ይመስላል! ሰው እንዴት ከፈጣሪው ይርቃል? ለዚህ በቂ መልስ ለማግኘት የራቁ ሰዎችን ህይወት መለስ ብሎ ማጤን ነው:: ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያርቀው 1. ሰው ነው:: ይሄ ሰው ጎደሎ ወይም ግማሽ ሰው ነው:: ጎደሎ ሰው በአፉ ፈጣሪውን እያሞካሸ /ያከበረ እየመሰለ/ በድርጊት የሚክደው ነው:: ይሄ ሰው አሰናካይ ነው:: 2. ዓለም /Cosmos/ ዓለም ሲባል ማንኛ ውም ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርብ ግለሰቡን ማርኮ /አንቆ የሚይዘው ኃጢአት አሳቃፊ ልምምድ፣ ምኞት፣ ሲስተም ወይም ምድራዊ ቅንባሮ፣ የተቃራኒ ፆታ ፍቅር፣ ክብር፣ ስግብግብነት፣ በሙሉ በ2ኛጢሞ3:1-9 የተጠቀሱት ሁሉ ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቁታል:: 3. አጋንንት: አጋንንት ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቁታል:: እነርሱ በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በችሎታ፣ በልምድ፣ በሽፍጠኛነት፣ በአፈጣጠር ወዘተ ሰውን ይበልጡታል:: ሰው በልዩም ሆነ በጋራ ፀጋ ስለተጠበቀ /Special & Common Grace/ በፈጣሪው እርዳት መኖር ቻለ እንጂ መናፍስት ሰውን መጫወቻ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር:: ለምሳሌ፣ እኛ ከተነጠቅን በኋላ እነዚህ በጌታ ሐይል የተያዙና የተከለከሉ አጋንንት ሰውን እንዲያሰቃዩ መለቀቃቸው አይቀርም :ራዕይ9:1-10:: ያኔ ለአውሬው ተከታዮች ወዮ! ከእግዚአብሔር ርቀው ለሚሳደቡ ሰዎች፣ ስቃያቸውን ባንወድድም ከትንቢቱ ቃል አንፃር ስለነዚህ ከእግዚአብሔር ስለራቁ ሰዎች ወዮ እንላለን:: ራዕይ 9 በሙሉ ይነበብ:: ራዕይ16:12-15::

ክርስቲያን ጥንቁቅ ነው የሚባለው እውነተኛ አምልኮን ሲያመልክ ነው: ከእውነተኛ አምልኮዎችም ዋነኛው በያዕቆብ 1:27 «እንደተገለጸው በዓለም ከሚገኘው ዕድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው» ታዲያ ዛሬ ያለ ጋብቻ



በልቅ ወሲብ በመርካት እንኑር፣ እንደፈለገን እናስወርድ፣ የሰው ስጋ እንመገብ፣ ሰውን ገድለን ወደ ሌላ ዓለም እናሸጋግረው፣ ወዘተ በግል ብልሹ ፍልስፍናና ሃይማኖት አዕምሮአችን ሲመረዝና ህይወታችን መኖር ሲጀምር ዝም ከተባለ፣ ኃጢአቱ እንደ ፅድቅ ከተቆጠረ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላል? ፍፁም ዘበትና የማይታሰብ ነው:: ስለሆነም ለመነጠቅ የሚፈልጉ ሁሉ መንፈሳዊ ርቀት /Spiritual Distanciation From God/ የት ቦታና ሁኔታ ላይ እንደሚጠነሰስ አስተውሎ አውቆ ስለመራቅ መጠንቀቅ ያሻል:: በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ ኢ.ቲ.ሲ. እማር በነበረበት ጊዜ ቢክ አንደርሰን በመባል የሚታወቁ መምህር በማስዳ የአምልኮ ፕሮግራማችን ላይ ቃል ሲያካፍሉ አንድ የማይረሳ ንግግርን አስተላልፈው ነበር:: ይኸውም ምንም እንኳን እኛ ሙሉ ጊዜአችንን ሰጥተን መጽሐፍ ቅዱስን የምንማር ብንሆንም ካልተጠነቀቅን በስተቀር ከእግዚአብሄር ልንርቅ እንደምንችል የሚያሳስብ ነበር:: ቀላል ማስጠንቀቂያ አይደለም::

## 12.4 <u>የግል የፀጋ ስጦታ ልምምዶች ለመነጠቅ ዋስትና ስላለማስገኘታቸው</u>

ይሄ ዘመን የእነ ዘመነ እንኮዬ/የእነ እንደልቡ ዘመን ነው:: ካመቸና ካስኬደ ቀጥል የሚባልበት፣ አስተዋይነትና ጭምትነት ከሰው ህይወት የኮበለለበት ዘመን ነው:: ግለአማክሎአዊነት /ግላዊነት/ ኃይል ያገኘበትና የምዕራቡ ዓለም ፍልስፍናና ስነ ልቦናዊ አመለካከት እንዲሁም አንፃራዊ ዕውነትና አንፃራዊ ሥነምግባር /Relative Truth and Relative Ethics/ ሥር እየሰደዱ ያሉበት ዘመን ነው::

አትንኩኝ! ተዉኝ! ሁኔታው ባወጣው ያውጣኝ! በጉዳዬ ጣልቃ አትግቡብኝ፣ ጅቡ ቢበላኝም ይብላኝ፣ ብሞት ለራሴ ብኖር ለራሴ የሚባልበት ዘመን ነው:: ዕውነት የሚባል ፅዩፍ ሆኖ የታየበት ጊዜም ነው:: አሞፅ 5:10 ፣ 2ኛጢሞ4:3-4/:: ላንተ ዕውነት የሆነልህ ለእኔ ውሸት ሊሆን ስለሚችል፣ ላንቺ ክፉ የሆነው ለእኔ መልካም፣ ላንተ መልካም የሆነው ለእኔ ክፉ፣ ለአንዱም ኃጢአት የሆነው ለሌላው ፅድቅ ሆኖ የሚታይበት አመለካከትና

የአንፃራዊነት አካሄድ እየተበራከተ የመጣበት ጊዜ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን መንፈስ: መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ ቢል እሺ. ለእርሱ ዕውነት ሊሆን ይችላል ተብሎ ግለሰቡ እንደልቡ እንዲፈረጥጥና እንደፈለገ እንዲያቧትር ወይም አንድ ወፍ ገድሎ ሳለ ሺህ ወፎች ገደልኩ ሲል የሚሳቅለትና የሚጨበጨብለት ጊዜና ልምምድ ውስጥ ገብተናል::

ከዚህም የተነሳ ቀድሞ በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራው እውነተኛ መንፈሳዊ ልምምድ /በፀጋ ስጦታዎች መጠቀም/ ዛሬ በአንዳንድ ቦታ መንፈስ ቅዱስ ከማዳኑ የተነሳ ለስሜት ወለድና አጋንንት ወለድ መንፈሳዊ መሰል እንቅስቃሴና ልምምድ ሥፍራ ሲይዝ ይታያል::

ሰው መንፈስ ነፍስና ስጋ አለው:: ወይም ሰው ውስጣዊ ሰውነትና ውጪአዊ ሰውነት አለው:: ሰው በውስጣዊ ሰውነቱ ከመንፈሳዊ ዓለም ጋር ተራክቦ/ኅብረት/ ሲያደርግ በስጋዊ አካሉ አማካይነት ደግሞ ቁሳዊ ከሆነው ዓለም ጋር ኅብረት ወይም ግንኙነት ያደርጋል:: ሰው በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ተጠቅሞ ከማንነቱ ጋር ተራክቦ እያደረገ ያለው መንፈሳዊ ኃይል ምንጩ ከየት እንደሆነ ካልለየ በስተቀር አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል:: በክርስቶስ አማኝ የሆነ ክርስቲያን ጥንቃቄ እስካላደረገ ድረስ አጋንንት ሊነግሩት፣ ሊያስተምሩትና ሊናገሩት ይችላሉ? ይህንን ሐሳብ በአጽንኦት ሊገልጽልን የሚችለው ጥቅስ በ1ኛጢሞ 4:1-2 ያለው ነው:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ:-

«መንፈስ ግን በግልጥ: በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» የሚለው ዕውነት ቢሆን በዚህ መንገድ አማኝ የነበሩ ሰዎች ከክፉ ኃይላት ጋር ተራክቦ ካደረጉ በኋላ ሀይማኖታቸውን እንደሚክዱ ያመለክተናል:: የሚካደው ሃይማኖት ትክክለኛ ው እስከሆነና ክህደትን አስተላላፊዎቹም በውሸተኞች ሰዎች የሚጠቀሙ አጋንንት/መናፍስት ከሆኑ ሰዎቹን ለማግኘት ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ ዘዴዎችና መቅረቢያዎች እንዳላቸው ማሰብ አያዳግትም:: ታሪኳ በሐሥ.



16:16-18 ተጠቀሰው የሟርተኝነት መንፈስ የነበረባትን ሴት መንፈስ የስብከትን የሙገሣ ዘዴ ተጠቅሞ ሐዋርያው ጳውሎስን ሊያስተው ሞክሮ ነበር:: መንፈሱ ተባባሪ፣ የወንጌል አገልጋይ_መስሎ በልጅቷ ሲናገር ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባይነቁበት ኖሮ ልጅቷን ተከታይ ሆነው ሊስቱ የሚችሉበት ክስተት ሊገጥማቸው ይችል ነበር:: ዛሬ አንዳንድ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነን ባይ ቤተ ዕምነቶች ምን ያህሉ ከዚህ የስህተት አሰራር የፀዱ ይሆን?

የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረችው ኤልዛቤል የጌታን ባሪያዎች በማሴሰን ታስት ነበር፤ ጎላ ባለ መልኩ መሳት ባለበት ቦታ ከክፉ ኃይላት ጋር ግንኙነት ወይም የእነርሱ ተፅዕኖ የለም ማለት አይቻልም:: የአስቆሮቱ ይሁዳን ታሪክ ስንመለከት ሰይጣን ሊቆጣጠረው ሲል በሀሳቡ ክፉ ሀሳብ አስገባ ከዚያም ራሱ ገባበት:: ለመሆኑ አስቆሮቱ ይሁዳ ከ12ቱ ጋር በተመረጠና ሥልጣን ተሰጥቶት ለአገልግሎት በወጣ ጊዜ ሽባ ተርትሮ፣ የሞተ አስነስቶ ድውያንን ፈውሶ፣ በፀጋ ስጦታዎች ተጠቅሞ ተዐምራት አድርጎ ነበር? ወይስ ዝም ብሎ ለ3 ተከል ዓመታት አጃቢ ነበር? መልካም፤ ይህንን ለአንባቢያንና ለመንፈስ ቅዱስ መተው ይሻላል::

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ሰዎች አሉ? አንድ ሰው እለ እንበል ይህ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመላለስንና መስራትን እንደ አገልግሎት አያይም፤ ሆኖም ግን ችሎታው ስላለው ይሠራል:: ስራውም መሰበክና መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ነው:: ይህ ሰው ለመስራትና ለዕለት ኑሮው ገንዘብ /ገቢ ለማግኘት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመላለሰው ስለዳነ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ አይደለም:: የዚህ ዓይነቱን ሰው ሰይጣን እንደምን ይመለከተዋል? እውነተኛ አማኞችን ለመግደያ ይጠቀምበት ይሆን? በዩሐ. 16:1 እንደተጠቀሰው ትንቢት መፈፀሚያ ሊሆን ይችል ይሆን? አዎን እንግዲህ የመነጠቅን ቀን በናፍቆት የሚጠብቅ ክርስቲያን ወደዚህ ዓይነት መጠለፍ ውስጥ እንዳይገባ በብርቱ ሊጠነቀቅ ይገባዋል:: እንግዲህ ራስን መመርመር ጠቃሚ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው:: 1ኛቆሮ.11:32-35::

በርዕሱ ላይ እንደተጻፈው የፀጋ ስጦታዎች ልምምድ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ዋስትና እንደማይሰጡ ተገልጦአል:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲጠቀሙባቸው በእርግጥ ትልቅ መፅናናትን ወደ ጌታ መጠጋትን ሊያስገኙ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዕምነትን ሊያሳድጉ ይችላሉ:: ሆኖም ግን የፀጋ ስጦታዎቹ በግል ህይወታችን ስለተገለጡ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምንገባ እርግጠኞች ነን ማለት አይቻልም ለማለት ነው:: ይህ እውነት የሚሆነው ሰይጣን ራሱ ልክ የፀጋ ስጦታዎችን የሚመስሉ አጋንንታዊ የማታለያ፣ የመጥቀሚያ እንቅስቃሴ ሊያደርግ ስለሚችል ነው:: ይህንን ሐሳብ በበለጠ ለመረዳት ማቴ7:22፣ 2ኛቆሮ11:13-15፤ 2ኛተሰ2:9-11፣ ራዕይ13:12-14 ማንበቡ ይጠቅመናል::

ሐዋርያው ጳውሎስ እኔ ለሰዎች ከሰበክሁ በኋላ የተጣልሁ እንዳልሆን ራሴን እየጎሰምሁ አስገዛለሁ ሲል በእርሱ ደረጃ እንኳን ካገለገለ በኋላ መጣል /ከንቱ መሆን ሊኖር እንደሚችል ቃሉ ያስረዳናል:: በተለይ በማቴ7:22 ላይ የተጠቀሱት ዓይነት ሰዎች ጌታ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ሊላቸው ለመለኪያነት ማስረጃ ያቀረቡት በፀጋ ስጦታዎች መጠቀም መቻላቸውን ነበር፤ እግዚአብሄር ፀጋውን ሊያፈስስ ይችላል፡ ያንን ሲያደርግ ግን ሰዎች እንዲያምኑትና ንስሀ ገብተው ህይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ለመርዳት ነው:: ሆኖም ግን ራሳቸውን እንደ ንፁህ ሰው የሚያዩበት ከሆነ ትዕቢትን ያመጣል:: ስለሆነም ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነስቶ ይጀምራል የሚለውም ቃል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው እዚህ ላይ ነው:: ራስን በቅድስናና በንፅህና እየጠበቁ እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ እንጂ የፀጋ ስጦታዎች በሕይወቴ ስለሰሩ ወደ እግዚአብሔር መንግስት በሙላት እገባለሁ ማለት እንደማያስችል ሊተኮርበት ይገባል:: በተጨማሪም በምድረ በዳ በጣም አስደናቂ በሆነ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ /በድንቅ፣ በተዐምራትና በምልክቶች/ ታጅበው ኖረው በመጨረሻ ግን ከሁለት ሰዎች በስተቀር በምድረ በዳ የቀሩትን እስራኤላውያን ልብ ልንልና ለተግሳጽ የሚሆን



ትምህርት ልንወስድ ይገባናል፤ ድንቅ ማየት መንፈሳዊ ላያደርግ ይችላል:: 1ኛቆሮ. 10:1-12::

## 12.5 የእግዚአብሔርን ኃይል የጣለ አምልኮ

ሐዋርያው ጳውሎስ የመጨረሻውን ዘመን ሰዎች ከገለጠባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የአምልኮት መልክ ኖሮአቸው ኃይሉን የካዱ መሆናቸው ነው::1ጢሞ3:5:: የአምልኮት መልክ ማለት ማንኛውም ውጪአዊ በሆነ መልኩ ሰው የሚረዳው፣ የሚያየውና የሚሰማው ግርግር ማለት ነው:: ሰባኪነት፣ የመጽ/ቅዱስ አስተማሪነት፣ ዝማሬ፣ ፀሎት፣ ፕሮግራም መምራት፣ ማስመለክ ወዘተ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይቻላል:: አምልኮ ውጫዊና ውስጣዊ የሆነ መልክ አለው::

### 12.5.1. ውጫዊና ውስጣዊ አምልኮ

ስለሁለቱም ምንነት በዝርዝር ለመተረክ ሁኔታ ባይፈቅድም መረጃ ለማግኘት የግድ ስለ ሰው ስብዕና መመልከት ይኖርብናል:: የሰው ስብዕና በሁለት ይከፈላል:: ይኸውም ልብስ ስብዕናና ዕውን ስብዕና ናቸው:: ልብስ ስብዕና ስንል ማናቸውም ሰው በአይኑ ተመልክቶ በጆሮው ሰምቶ ብያኔ ወይም አስተያየት ሊሰጥበት የሚችለው እንቅስቃሴ ነው:: ሰው አስመስሎ ለማሳመን የሚገልጣቸው የሚያደርጋቸው ለገሃዱ አለም የተጋለጡት ልምምዶች በልብስ ስብዕና ደረጃ ይፈረጃሉ::

እውን ስብዕና የምንለው ደግሞ የግለሰቡን የውስጥ ማንነት አመልካች የሆነ፡ ግለሰቡ ለብቻው የሚያውቀው ወይም እግዚአብሔር የሚያውቀው የሕይወት አቋም ሐሳብና ዝንባሌ እውን ስብዕና ይባላል:: የማማከር አገልግሎት ምሁራን እንዳመለከቱት እነዚህ የስብዕና ዓይነቶች 1. በተጣጣመ መልኩ 2. በተቃረና መልኩና 3. በተዘበራረቀ መልኩ በሰው ህይወት ሊገለጡ እንደሚችሉ ይናገራሉ:: ስዚህ እውነት ማስረጃ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን መመልከት ይጠቅማል::

አምኖንና አቤሴሎም ሁለቱም ዓይነት የሰብዕና ልምምዶች ታይተውባቸዋል፤ አምኖን አሞኛል ብሎ ለትዕማርና ለዳዊት መልዕክት ሲልክ የውስጥ ሰብዕናው ግን በወሲብ ስሜት ተይዞ ነበር /2ኛሳሙ13/:: አቤሴሎም ወደ አባቱ ወደ ዳዊት በችኮላ ቀርቦ ሲስመውና በማለዳም ወጥቶ ሕዝቡን ሰላም እያለ ልቡን ሲሰርቅ በልብሰ ሰብዕና ደረጃ የአባቱ ረዳት ተባባሪና አክባሪ ይመስል ነበር:: በዕውን ሰብዕናው ግን መፈንቅለ መንግስት አድርጎ በዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ ነበር:: እስቲ አቤሴሎምን በአንድ ሁኔታ እንመልከተው:: ለምሳሌ የእስራኤላውያን መንፈሳዊ የክብር በዐላት በሆኑ ጊዜ በነዚያ ቀናት ህዝቡ ዳዊትም ፈጣሪያቸውን ሲያመልኩ ሲወጡ ዳዊት በንፁህ ልብ ጌታውን ሲያመልክ አቤሴሎምም በህዝቡ መሃል አብሮ ያመልክ ነበር:: አሁን የዳዊት ልብና የኤሴሎም ልብ በእግዚአብሔር ፊት ምን እንደሚመስል መገመት አያዳግትም:: የዳዊት አምልኮ በልብሰ ሰብዕና በዕውን ሰብዕና አንፃር ጤናማ /ለእኛ ያልታወቁ እንዳሉ ሆነው/ ሲሆን፤ የአቤሴሎም ግን የሚጋጭ ነበር:: ወይም የአቤሴሎም አምልኮ በልብሰ ስብዕና ደረጃ ነው ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በቀባው በዳዊት ላይ የመነሳት ድብቅ ሰብዕና ስለነበረው ነው::

ዛሬም ቢሆን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዚህ ዓይነት ብዙ ሰዎች አሉ:: ልባቸው እንደ ዴማስ ፈፅሞ ዓለምን የወደደች ገና ዓለምን ወደ መውደድ ያዘነበለ ወይም የተነሳሳ፣ ተጠራጣሪነት ያለባቸው፣ የእግዚአብሔርን ሟችነትና አለመኖር በመቀበል ዳርቻ ላይ ያሉ ይኖራሉ:: የእነዚሁ ሰዎች ሰብዕና የተደበላለቀ ነው:: ውሳኔ አላደረጉም እንጂ ሰብዕናቸው እርስ በርሱ ይጋጫል:: ለምሳሌ ታሪኩን በ3ኛ ዩሐንስ 9-10 የምናነብበው ዲዮጥራጢስ በአንድ በኩል አገልጋዮች የሆኑትን እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ ያሉትን ሰዎች ይቃወማል፤ ይለያያል፣ ያለ አግባብ ከቤተክርስቲያን ሰዎችን ያወግዛል፤ የዚህ ሰው ዋነኛ ዓላማ በምዕመኑ መሐል አለቃ ወይም ባለስልጣን የመሆን እውን ስብዕናው ስላለው ነው:: ይህ ሰው በሐዋርያት ደረጃ ያሉትን የጌታ አገልጋዮች ማክበር ካቃተው ልብሰ



ስብዕናውንና እውን ስብዕናውን አስታርቆ ለመኖር የተቸገረና ማንነቱ የተደበላለቀበት ሰው ነው:: ይሄ ሰው የአምልኮት መልክ አለው፤ሆኖም ግን የጌታን መንፈስ ቅዱስና ከእርሱ የሚስርፀውን የጌታ ኃይል (ሐሥ. 10:38፣1:8) በደንብ ያውቀው ይሆን ? የዚህ አገልጋይና የሚመራቸው ምዕመናንስ ሕይወት ፍፃሜ ምን ይሆን? ከአምኖናዊው አቤሴሎማዊ ስብዕና ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል::

የመነጠቅን ቀን ተስፋ የሚያደርግ ክርስቲያን ከሚያካሂዳቸው ታላላቅ ተጋድሎዎች ውስጥ ዋነኛው እውንና ልብሰ ሰብዕናውን አስታርቆ መኖር መቻሉ ነው:: ዕውነተኛና ትክክለኛ አምልኮ የሚባለው ሰው በውስጡ እንዳለ በውጫዊው ማንነቱም ሲሰራ ነው:: አስመሣይነት ፣ ቅጥፈት ፣ ግብዝነትና ታይታ በሌለበት ልባዊ አካሄድ ማምለክ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል:: ለዚህም ዓይነት አምልኮ ሰውን ብቁ የሚያደርገው ሰው የውስጥ ሰውነቱ (መንፈስና ነፍሱ) 2ኛቆሮ4:16-18 በሚቀድሰው የዕውነትና የህይወት ቃል ተቀድሶ ሲነፃ ነው:: ዮሐ6:63 ፣17:17:: እግዚአብሔርንም ሆነ ሰውን ከልብ ለመውደድ ቀጥሎም ዕውነተኛ አምልኮን ለማካሄድ መሠረቱ ነፍስን ማንፃት ነው::1ኛ ጴጥ1:2::

ዳግመኛ የተወለደ ሁሉ በውስጡ ተዘርቶና አድጎ ፍሬ በሚያፈራው ቃል ሲሞላ ለስጋዊነትና ለዓለማዊነት ስፍራ አይኖረውም:: ገላ 5:21-22፤1ኛ ጴጥ1:23:: በህይወቱ የመንፈስ ፍሬ የበዛለት ክርስቲያን አማኝ እውንና ልብሰ ስብዕናው ሣይጋጭበት በንፁህ ህሊና ፈጣሪውን ያመልካል:: ስለሆነም ከመጨረሻው ዘመን የአስመሣይ አማኞች የተዘቡ የአምልኮ ልምምዶች ያመልጣል:: ይህ ሰው (እህት ሆነች ወንድም) ለመነጠቅ ራሱን አዘጋጅቷል ማለት ነው::

የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል የሚለው ትንቢት እንዳይፈፀምብን ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል:: ዓለማችንን ቃኘት ስናደርግ የግልሙትና ባህሪ ሊኖራቸው የሚችሉ የአውሬው መንፈስ ያገኘ

ቸው ቤተ ክርስቲያናት ሊኖሩ እንደሚችሉ በራዕይ 17 እና 18 ተጠቅሷል። በተለይም በዮሐ. 16:1 « እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ» ከምኩራባችሁ ያስወጧችኋል፤ ከዘህም በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» የሚለው ለአምልኮት መልክ ዓይነተኛ ምሣሌ ነው። ልብ ሊባል የሚገባው ዕውነት እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አምላኪ ነን ማለታቸው ነው፤ ሆኖም ግን የእውነተኛ አምላኪዎች ገዳዮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በጣም ሃብታሞች ሆነው ድሆች በመሐከላቸው ገብተው እንዳያመልኩ የሚያደርጉ ወይም ደግሞ በሙያ (ሣይንቲስቶች፣ ዶክተሮች፣ በዝርያ የሚገናኙና ወዘተ) ብቻ በአንድነት ሆነው ለማምለክ የተሰባሰቡ እንዳሉ ይሰማል፣ ይነበባል። አካሄዳቸውን እስካልመረመሩ ድረስ በስጋ እየዘሩ መሆናቸውንና ውጤቱም መበስበስን ማጨድ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። የኋለኛው መለከት ሲነፋ ለመቅረት የሚጋለጡ ፈጪዎችና አራሾች/ገንቢዎች እነዚህ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 12.6. ራስን ለመታለል አደጋ ስለማጋለጥ

ህይወት፣ መንፈስ፤ ዕውነት፣ መንገድ፣ ብርሃን፣ መብራት፣ ሕግ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ብዙ የከበሩ ዕውነቶችን ይዞአል። ጳውሎስ ለገላትያውያንና ለቆሮንቶሳውያን አማኞች ሲፅፍ «አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና» ገላ. 6:3። ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፤(1ኛቆሮ10:12) ሲል የመታለል ሕይወት ሊደርስባቸው እንደሚችል ያመለክታል። የገላትያ ክርስቲያኖች ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን ወንጌል፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ሆኖ የተረከላቸውን እውነት በልዩና በተሳሳተ ወንጌል ለወጡት ።ገላ1:6-8፣3:1-2። ይህንን ሲያደርጉ አስፍስፈው የሚፈልጓቸው ሐሰተኞች በአካባቢአቸው መኖራቸውን ዘንግተው ነበር። ገላ4:17። ራሳቸውን በእርስ በርስ መነካከስ፣ ነፃነት በመሰል ባርነት፣ ለሥጋዊነት፣ አጋልጠው ነበር። በተጨማሪም በምዕ. 6 ላይ የሳቱ ሰዎችን በየዋህነት ማቅናት ተዘንግቶ ነበር፤ ለዚህም መንፈሳዊነት የተዘነጋበት ህይወት ልምምድ ውስጥ እንደተገባ



ይታያል። ጠቅለል ባለ መልኩ የገላትያ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ወደ ማታለል አዘማሚያ ውስጥ ገብተው ነበር ማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ መልኩ ዛሬም በእግዚአብሔር ቤት ሲኖሩ ሰዎች ራሳቸውን ሲያታልሉ እንደሚችሉ ሲዘነጋ አይገባም። ለምሳሌ ሁለት በአንድ ወፍጮ ሲፈጩ አንዲቱ ስትነጠቅ ሌላይቱ አልተነጠቀችም በክርስትና ህይወት መኖሩ በቸልታ ስለተመለከተች ነው። በእርሻ የሚያርሰውም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም ዓይነት አማኞች በክርስትና ሲኖሩ እንደቀላል ነገር ቆጥረው ኖረው አንዱ ወደ ክብር ሲሄድ እነርሱ መቅረታቸውና መዋረዳቸው ራሳቸውን ማታለላቸው አይደለም? ያሰ ጥርጥር ነው። መንፈሳውያን የሆኑ ይመስላቸዋል ግን አይደሉም። 1ኛቆ. 19:37። 6 ዘጠኝን/9/ ስለመሰለች ዘጠኝ ናት ማለት አይቻልም፤ ስድስት ናት እንጂ።

ታሪካቸውን በ1ኛቆሮቶስ የምናነበው ቆሮንቶሳውያን ጳውሎስ እስራኤላውያን እንዴት በምድረበዳ ወድቀው እንደቀሩ የተረከላቸው ያለ ምክንያት አልነበረም። ሳይቆሙ የቆሙ፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳይበረቱ የበረቱ፣ መንፈሳውያን ሳይሆኑ የሆኑ መስሎ ታይቷቸዋል። ለምሳሌ ሲጣሉ ሲጨቃጨቁ፣ እኔ የጳውሎስ ነኝ የአጵሎስ ነኝ ወዘተ እያሉ ሲለያዩ ራሳቸውን እንደመንፈሳዊ ሰው መቁጠራቸው መታለላቸው ነበር። ከዚህ አቋማቸው /ከስጋዊ ክርስቲያንነት/ ቶሎ ተመልሰው ክርስቶስን ካልመሰሉ በስተቀር ውድቀት በፊታቸው እንዳለ /1ኛቆሮ10:12/ ያመለክታቸዋል። እንዲህ ሳይሆኑ ሆኖ መገኘት ራስን ማታለል ነው።

በአሁኑ ዘመን አንዳንድ በቤተ ክርስቲያን ያሉ አማኞች ስለ መፀለይ ግድ የሌላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሳያነብቡ ሲውሉና ሲያድሩ ምንም የማይሰማቸው፣ ሲጠሉ፣ ሲጣሉ፣ ሲያጣሉ፣ ሲሰርቁ፣ ሲዋሹ፣ ሲያሟርቱ፣ ሲያለያዩ፣ በስመ-ክርስትና ሲነግዱ፣ ሲያጭበረብሩ፣ ሲሰብኩ፣ ሲዘምሩ፣ ከቤታቸው ጣሪያ ሥር ያሉ ቤተሰባቸውን ሳያገለግሉ፣ መንፈሳዊውን ነገር በስጋ ሲተኩ፣ አስመሳይነት ነግሦ እውነተኝነት ሲከሳና ሲኮስምን

የማይሰማቸው፣ የጌታ ቤት ፈርሶ የራሳቸውን ሲሰሩ ምንም የማይሰማቸው፣ የጌታን ምፅዓት በመድረካቸው እንዳይሰበክ ረቂቅና ግልጽ ገደብ ሲያበጁ ወዘተ ምንም የማይመስላቸው ሕሊናቸው በጋለ ብረት ተጠብሶ /1ኛጢሞ4:2-3/ ደንዝዘው የሚኖሩ አሉ:: ታዲያ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እንዳላታለሉ በምን ያረጋግጣሉ? *መታለል ገደል መንከባለል* ማለት ይሄ አይደል? መሰከት ቢነፋ እንነጠቃለን ይሉ ይሆን? የዚህን ዓይነት ህይወት በ1ኛ ቆሮ. 6:10 እና በገላ. 5:21 የሚለማመዱ ክርስቲያን ነን ባይ ሰዎች «የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም» የሚል ቃል እንደተፃፈባቸው ግልፅ ነው:: 1ኛ ቆሮ.6:10፤ ገላ. 5:21:: ስለሆነም ራሳችንን እንዳናታልል:: አሜን በተባለለት ቃል እንኑር:: አሜን!!

## 12.7. ተግቶ በርን የመጠበቁ ጉዳይ/ልምምድ

ጌታ ኢየሱስ ግልጽ ወዳጅ ነው:: የክርስቶስ ወዳጅነቱ ከሚገለጥባቸው ዋነኛ መንገዶች ውስጥ አንዱ ዕውነትን ማስታወቁና ማስተማሩ ነው::ይህንንም የዚህ ዓለም ወኪል ገዢ ከሆኑት ለአንዱ ለጲላጦስ እውነት ልናገር /ልመስክር ተወልጃለሁ ብሎ ከተናገረው መረዳት ይቻላል:: ዮሐ18:36-37:: ጌታ ለደቀ መዛሙርቱና ለተከታዮቹ እውነትን በመናገር ፍቅሩን ከገሰጠባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ሊጠቁ የሚችሉባቸውን አቅጣጫዎች በማመልከቱ ነበር:: ይህንንም ጌታ በማርቆስ 14 ላይ እንዴት እንደተናገረ ማግኘት እንችላለን::

«ስለዚያች ቀን ወይም ሰዓት የሰማይ መላዕክቱም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም፣ ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፣ ትጉ፣ ፀልዩም፣ ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደሄደ ሰው ነው:: ለባሮቹ ሥልጣን ለእያንዳንዱም ሥራውን ሰጥቶ *በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ*፣ እንግዲህ በማታ ይሁን በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮህ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ



እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ:: ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ ትጉ::» ቁ32-37::

ከላይ ከተጠቀሱት ሐሳቦች ውስጥ ስለ መነጠቅ ስናስብ ልዩና ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገባ ዕውነት አዘል ቃላት ውስጥ በረኛ፣ ትጉ፣ ተጠንቀቁ፣ ፀልዩ፤ አዘዘ፣ ድንገት፣ ተኝታችሁ፣ ለሁሉ እላለሁ ይገኛሉ:: «ትጉ» /መትጋት/ የሚለው ቃል ብቻ 4 ጊዜ ተጠቅሷል:: የቃሉ መደጋገም ምን ያህል ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ያመለክታል:: «ትጉ» የሚለው ቃልና፣ ተጠንቀቁ፣ ፀልዩ፣ ንቁ፣ የተሰኙት ቃላት ተቃራራቢ ናቸው:: የመትጋት አስፈላጊነትና የመተኛት አላስፈላጊነት ተደጋጋፊነታቸው የማያጠያይቅ ነው:; አለመትጋት ባለበት መተኛት አለ፣ የመተኛትም ውጤት በአጠገብ ላለ ክፉ መጋለጥ ነው:: የተኛ ሰው ስለ አካባቢው ምንም አያውቅም:: የተኛ ሰው ትኩረት ቢያደርግም በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ /ህልም/ በሚደረጉ ተዕይንቶች ላይ ነው:: የተኛ በሩቅ ሊከሰት ስላለው አደጋና ጉዳት አያውቅም ቢያውቅም ተመልሶ ይተኛል:: በመንፈሳዊ አነጋገር ብንወስደው ቁ.34 ላይ «<u>በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ</u>» የሚለው ዐረፍተ ነገር ብዙ ነገርን ያመለክታል:: አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ያስቀመጠው የከበሩ እውነቶች አሉት:: ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ፣ የፀጋ ስጦታዎች፣ የመንፈስ ፍሬዎች፣ አገልግሎት፣ መንፈሳዊ ገድል፣ ስለ ክርስቶስ መመስከር፣ ድሆችን መርዳት በዓለም ከሚገኝ ርኩሰት ራስን መጠበቅ ወዘተ ይገኛሉ:: ባጭር ቃል ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ምንም ዓይነት መልካም ስጦታ የለም:: ሆኖም ግን በሕይወቱ የታዩና ሊታዩ ያሉ መንፈስዊ ስጦታዎች ተወግደው የስጋ ሥራዎች እንዲገቡበት ውጊያ ያካሂዱበታል:: እንግዲህ የክርስቲያን በረኛነቱ የሚለካው እዚህ ላይ ነው::

በአገር አቀፍም ሆነ በዐለም አቀፍ ደረጃ ከልዩ ልዩ አገሮች የእግር ኳስ ተጫዎች ስፖርተኞችን ስንመለከት የበረኛው ብርቱነት ከሌሎች አጋር ተጫዋቾች ጋር ተደምሮ ለቡድኑ አሸናፊነት ወሳኝ ነው:: በሠለጠነው መሠረት በረኛው ካልተጋ ቡድኑ ይጠቃል:: በረኛ መሃል ሜዳ ገብቶ ወይም

የ3ና የ5ን ቁጥር ቦታ ተክቶ ሊጫወት አይፈቀድለትም እንዲህ ካደረገ ይቀጣል:: ከጨዋታ ውጪም ሲገለል ይችላል:: በተመሳሳይ መልኩ አንድ አማኝም ወደ ህይወቱ ገብቶ መንፈሳዊነቱን ከሚያስለቅቁ ወይም ወደ መንፈሳዊነት ደረጃ እንዳይደርስ ከሚገዳደሩ ረቂቃን መንፈሳዊ ቀበሮዎች (ገላ: 5:16-21፣ <u>ሮሜ.1:28-32፣1ኛቆሮ</u> 5 እና 6፣ 2ኛጢ.ሞ3:1-9፣ ራዕይ 21:8፣22:15) ወዘተ ሕይወቱን ማጠር ይኖርበታል:: በተለይ በ2ኛጢ.ሞ3:1-9 የተጠቀሱት አሉታዊ ክስተቶች በህይወቱ ከታዩ ላለመነጠቅ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊተኮርበት ይገባል::

ዕብራውያን 12:17 ስናነብ የበረከት ሕይወቱን ስላስቀማው ኤሳው እንመለከታለን:: ኤሳው ብኩርናውን ካስነጠቀ በኋላ መልሶ ለማግኘት ቢፈልገውም ሊያገኘው አልቻለም:: ኤሳው ያንን ሂደት እንዴት ተግቶ ስመቋቋም እንደ ብርቱና ጠንቃቃ በረኛ አልተጋም? በቅድመ መከራ የሚደረግ ትጋት ብዙ ሲጠቅም በድህረ መከራ የሚደረግ ትጋት በእሳት የማለፍ ያህል በመጠኑ ይጠቅማል:: ምክንያቱም ወዲያው የሺሁ ዓመት ሥርዐት ስለሚቀጥል ተግቶ ድነትን የፈለገ ሊደርስበት ይችላል:: በዚህ ምድር ትጋት፣ አስፈላጊ ነው፣ ከመነጠቅ በኋላ ደግሞ በዘላለም ቅድስናና ፅድቅ ውስጥ ስለሚገባ እዚያ ትጋት አያስፈልግም:: ለትጋት ጊዜ አሁንና በቅድመ መነጠቅ ነው:: ክርስቲያኖች በማየትና በመስማት ወደ ሕይወታችን ከሚዘምቱ ረቂቃን የህይወት አሉታዊ ትዕይንቶች ልንጠነቀቅ ይገባል::

## 12.8. <u>ለመከራ ያለው መነኩሴ መጽሐፉን ሸጠ</u>

ስደት መልኩ ብዙ ነው:: ስደት የማይመስል ስደት አለ፣ ድብቅ እንዲሁም ግልጽ ስደት አለ:: እግዚአብሔር ወይም ሰይጣን የሚያመጣውና የውጭ ሰው የሚያመጣው፣ ሰው ራሱ በብስለት ጉድለት የሚያመጣውም ስደት አለ:: እንዳንድ የስደት ዓይነት ክርስቲያኑን ሲያበረታው ሌላው ዓይነት ደግሞ ይጥለዋል:: ማቴ.13:21::



ከሁሉ ግን የከፋው የስደት ዓይነት ስውር ስደት ነው:: ስውር ለአሳዳጁም ሆነ ለተሳዳጁ እምብዛም አይታወቅም:: ስውር ስደት የሚመጣው ጠቃሚ፣ አስደሳችና በጎ መስሎ ነው:: ስውር ስደት በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃው ወደ አሉታዊ ልምምድ የሚያደሉ ስጋውያን ክርስቲያኖችን ነው:: የስውር ስደት ዋነኛ አቀንቃኝ ዲያብሎስ ነው:: የተወሰኑ ክርስቲያኖች ህይወታቸው የትኛው ዓይነት አሉታዊ ልምምድ ላይ (አለመፀለይ፣አለማንበብና ከቅዱሳን ጋር ንፁህ ህብረት አለማድረግ) ሲጠቁ እንደሚችሉ ስለማያውቁ ሁኔታዎች ካላመቹ በስተቀር የገሃነም ደጆች ፊት ለፊት ስደትን አያመጡባቸውም::

ከንባባት እንደምንረዳው ክርስቲያን አማኝ በግልና በህብረት ፀሎት፣ በግልና በህብረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ትምህርት፣ ከቅዱሳን ጋር ባላቸው ህብረት የሚተጉ ከሆኑ ከወቅቱ ስደት ድነዋል ማለት ይቻል ይሆናል:: ይህም ከሌሎች መንፈሳዊ ልምምዶች ጋር ተደምሮ ነው:: ከ400 ዓመታት በፊት አሜሪካ በተቆረቆረችበት እስከ 1950ዎቹ ዓመታት ድረስ ሕዝቡ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና አስተምህሮ፣ ለፀሎትም የነበረው አክብሮት በጣም ከፍተኛ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል:: ባለፉት 40 ዓመታት መጀመሪያ ላይ ግን አስቀድሞ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ይሰጥ የነበረው የመጽሀፍ ቅዱስ አስተምህሮና ፀሎት ከክፍሎች ወጥቶ በየፀሎት ቤቶች ይግባና ይሰጥ ተብሎ ሲወሰን ውድቀት በአገሪቱ ላይ ማንዣበብ እንደጀመረ ንባባትና የሰዎች ንግግሮች ያረጋግጣሉ::

በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ከሚተላለፉ ስብከቶች ውስጥ እንዱና ዋነኛው «<u>ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለስ</u>» የሚል ነው:: ለምን ይህ ስብከት አስፈለገ? ይህ ጥሪ፣ ትምህርትና ስብከት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አብዛኛው ወይም ከፊሉ ሕዝብ ከመጽ/ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ ልምምድ ውስጥ ስለገባ ነው: በዲቪና በልዩ ልዩ መንገድ ከተለያዩ አገሮች ወደ አሜሪካ የገቡ ሕዝቦች የየአገራቸውን፣ ባህል፣ ሐይማኖት፣ ቋንቋና ልምምዶች ይዘው

ገብተዋል:: የተወሰኑት የምዕራቡ ዓለም ህዝቦች ደግሞ ወደ ሉላቀፋዊነት /Globalization/ የሚያተኩር የመቀባበል አዝማሚያ ስለ ሚታይባቸው እምልኮአቸውንም ሆነ መንፈሳዊ አስተምህሮአቸውን በአዳዲስ አመለካከቶች ዕምነቶችና ልምምዶች እየተኳቸው ስለሆነ ለቅዱሳን ሰዎች የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ዕምብዛም ዋጋ አልተሰጠውም:: አልፎ አልፎ መጽ/ቅዱስ አይሁዳውያን የፃፉት ቃል ነው የሚልም የሐሳብ ስንዘራና ትንታኔም ስለሚያቀርቡ በየምክንያቱ ለእግዚአብሔር ቃል ዋጋ መስጠቱ ቀንሷል::

በቀደሙት ዘመናት የአንድ እውነት እርግጠኝነት መለኪያው ምንድነው ሲባል በማዕከላዊነትና በዋነኝነት ይጠቀስ የነበረው *የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ* የሚል ምላሽ በመጥቀስ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን ከአንዳንድ *ሥነ* መለኮታውያንና ፈላስፎች አስተምህሮ በመነሳት ለአንድ እውነት አስረጋጭ ምስክር ሊሆን የሚችለው <u>ተሞክሮ</u> /Experience/፣ <u>አመክንዮ</u> /Rationalization/፣ <u>*አንፃራዊ-ሥነምግባር*</u> /Relativized Ethics/፣ ባህል /Culture/፣ ሳይንስ /Science ወዘተ ናቸው የሚል ምላሽ በመስጠት ላይ ይገኛል:: ከላይ የተጠቀሱት የእውነት ማፅኛዎች እንደየሁኔታው አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆኑም እንደ ዋነኛ የእግዚአብሔር እውነት ማጽኛና መስካሪዎች ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም::

ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በመጥቀስና በመቀበል ዋነኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ከእጃቸው ያስመለጡ ብዙ ሰዎች ዛሬ በአለማችን ይገኛሉ:: ከዚህም የተነሳ የህይወት መመሪያ የሆነው ዕውነት ስለተቀማ፣ ክፉና ደጉንም የመለየት አቅም ስለጠፋ ጨለማውን ብርሃን፣ መልካሙን ክፉ፣ ፅድቁን ኃጢአት፣ ልኩን ስህተት፣ ፈጣሪውን የሞተ፣ ሰውን አምላክ፣ ሲኦልን የሌለ፣ ገነትን ሌላ ዓለም፣ የሰዎችን መናፍስት የአጋንንት፣ ቅዱሳን መላዕክትን አጋንንት፣ በሲኦል ያሉትን ሞተው የተነሱ፣ መግደልን ፅድቅ፣ እንስሳትን ሰዎች፣ ሰዎችን እንስሳት ወዘተ ወደ ማለት



ደረጃ ተደረሰ:: ዳሩ መመሪያ የሌለው፣ መንገድንም የማያውቅ ፍጡር እንዴት ወደ ትክክለኛው ሕይወት ይደርሳል? በአሁኑ ጊዜም የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት መጽሐፍ ቅዱስን *ታላቁ ውሸት* ብለው ስለሚያጣጥሉትና ስለሚዋጉት አንዳንድ ክርስቲያኖችም ይህ ክፉ ሐሳብ ተፅዕኖ እያደረሰባቸው ይገኛል:: መጽሐፉን ጣሉ፡ ራሳቸውንም ጣሉ፡ ስለሆነም ለእግዚአብሔር ፍርድ የተጋሰጡና የሚጋሰጡ ሆኑ *ለመከራ ያለው መነኩሴ መጽሐፉን* ሸጠ የተባለው ይህ አይደል? ስለዚህ ቅዱሳን ሁላችን መጽሐፍ ቅዱሳችንን አጥብቀን ልንይዘው ይገባል:: ባለሙያዎቹ ***የተሸጠ ዕቃ አይመለስም*** ይላሉ:: የተሸጠ ዕቃና ከእጅ ያመለጠ ንብረት አንድ ናቸው:: አንድ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ እያለ በትክክል ሊጠቀምበት ካልቻለ ከእጅ ካመለጠው እቃ በምን ይለያል? መልሶስ እጅ ለማስገባት ትልቅ ዋጋ ያስከፍል የለም::

## 12.9. <u>ከተሳሳቱ አመለካከቶች አደጋ ስለመጠበቅ</u>

ከእነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው::

### 12.9.1. <u>ስለ ጌታ ዳግም ምፅዐት</u>

12.9.1.1. በጌታ ዳግም ምፅዐትና በመነጠቅ መሃከል ልዩነት የለም

12.9.1.2. ክርስቶስ ሲመጣ አይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል ተብሎ ተፅፎአል /ራዕይ1:7/:: የወጉት እስራኤላውያን/ሌሎችም/ በምድር ገጽ ላይ ተበታትነዋል:: ታዲያ ኢየሱስ ሲመጣ አንዱ ንፍቀ ክበብ ጨለማ ሌላው ብርሃን ከሆነ የወጉት ሁሉ እንዴት ያዩታል? ይህ የምፅዐት አመለካከት ስህተት ነው ይላሉ::

12.9.1.3. የጌታ ኢየሱስ መመለስ መንፈሳዊ መመለሱ ነው ይላሉ:: ይህም ማለት ክርስቲያኖች በሙላት በምድሪቱ ከኖሩና መንፈሳዊነት ካየለ ይህ ጌታ መመለሱን ያሳያል::

12.9.1.4. የክርስቶስ በሰዎች ልብ መኖር ነው::

12.9.1.5. ሰው በምድር ኑሮው አብቅቶ ሲሞትና ወደ ጌታ ሲመለስ ያ ምፅዐት ነው::

## 12.9.2. ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

12.9.2.1. መነጠቅ ማለት ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላና ኃይል ተቀብሎ በዚህ ዓለም ጣጣ ላይ የበላይነት ተቀዳጅቶ በሥጋ ሥራ ላይ አሸናፊ ሲሆን ነው ይላሉ::

12.9.2.2. በተመስጦ መሆን ነው::

12.9.2.3. በአዕምሮ ወደ ልዩ ዓይነት ራዕይ ወይም ሕልም ውስጥ መግባት ነው::

ስለ ጌታ ምፅዐትና ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከላይ የተጠቀሱት አመለካከቶች ትክክለኛነት የላቸውም:: አንዳንዶቹ ከመነጠቅ ጋር ባልተያያዘ ትንሽ ተቀራራቢ ትርጉም ይኖራቸዋል::

ስለ ጌታ ኢየሱስ ምፅዐት በመንፈሳዊ ወይም በራዕይ ደረጃ የማይፈፀም ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ማስረጃዎች አሉ:: ከነዚህም ማስረጃዎች ውስጥ ዋነኞቹ የክርስቶስ በቃሉ መናገሩ፣ የነቢያቱ፣ የመላዕክቱና ሌሎችም አገልጋዮች ምስክርነት መስጠታቸው ነው:: የሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ድምጽ በግልጽ ከሰማይ መስማቱና ከእርሱም ጋር ንግግር ማድረጉ ጌታ ኢየሱስ በሰማይ በአብ ቀኝ መሆኑን እስጢፋኖስ እየተወገረ በነበረበት ጊዜ ወደ ሰማይ ሲመለከት ክርስቶስን ማየቱ /ሐዋ 7 እና 9/፣ ጌታ ኢየሱስ ወደ ላይ ሲወጣ መታየቱ ወደፊትም እንደሚወጣ በቂ ማስረጃዎች ናቸው:: በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስን ምዕራፎች ስንመረምር ስለ ጌታ ምፅዐት በብሉይ ኪዳን ብቻ 1527፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ 318 ጊዜ ባጠቃለይ ከ1845 ጊዜ ወይም በ17 ቁጥሮች ውስጥ አንድ ጊዜ መጠቀሱ ተረጋግጧል:: ይህ እውነት ነው:: ከዚህም በላይ በክፍል አንድ ከምልክቶቹ አንጻር በዝርዝር ይገለጸል::



## 12.9.3. ስለ ቀናትና ዘመናት

በተጨማሪም ስለ ጌታ ዳግም ምፅዐትም ሆነ ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜአትና ዘመናትን ጠቅሶ በዚህ ቀን በዚህ ወር እንዲህ ይላል ማለትም ፈፅሞ ስህተት ነው:: ለምሳሌ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንመልከት::

12.9.3.1.1. ዊሊያም ሚለርና አድቬንቲስቶች በክርስቶስ በ1943/4/ ላይ ይመጣል:

12.9.3.1.2. የጂሆቫ ምስሮች ቤተ-ዕምነት መሥራች ቻርለስ ራስል ክርስቶስ ኢየሱስ በ1914 መንግስቱን በምድር ሊመስረት ይመጣል:

12.9.3.1.3. የዓለም አቀፉ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆኑት ኽርቨርት ደብልዩ አርምስትሮንግ ክርስቶስ በ1972 ይመጣል:

12.9.3.2. ኤድጋር ዊሲንነት መነጠቅ በ1988 እንደሚሆን 58 ምክንያቶችን አቅርበው ነበር::

12.9.3.3. የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባልና የአለማቀፋዊት አሸናፊ ቤተ ክርስቲያን ነቢይት የአርማጌዶን ጦርነት በ1990 ዓ.ም ይሆናል ብላ ነበር:

12.9.3.4. የአዲስ ኪዳን ነቢይት ነኝ ባይዋ ሜሪ ስቲዋርት ረልፍ ክርስቶስ ከ1990 ዓ.ም በፊት ይመለሳል ብላ ነበር:

12.9.3.5. የዳሚ ሚሽነሪ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው የደቡብ ኮሪያው ሊ.ጃንግሪም መነጠቅ ጥቅምት 1992 ዓ.ም ይሆናል ብሎ በብዙ አሳማኝ ማስረጃዎች ስለተናገረ ወደ 30,000 ያህል አባላት ያላቸውን ንብረታቸውን ሸጠውና አውርሰው ሴቶች ለመነጠቅ እንዲቀልላቸው ፅንሳቸውን አስወርደውና ነጫጭ ልብሶች ለብሰው የመነጠቁን ቀን ሲጠብቁ ሳይሳካ ቀርቷል::

12.9.3.6. ሃሮልድ ካምፒንግ የተባለውና በአሜሪካ በሬድዮ ፕሮግራም የሚያገለግለው ፓስተር መነጠቅ በ1994 ይሆናል ብሎ ነበር:

12.9.3.7. ደብሰን ኢድ የተባሉትም አገልጋይ ክርስቶስ በ2000 ዓ.ም ሊመጣ እንደሚችል 50 ማስረጃዎችን አቅርበው ነበር /የዘመን አቆጣጠር ኢ.ኤ.አ. ነው/::

ከላይ የተጠቀሱትን ትክክል ያልሆኑና ትንቢትነታቸው በታሪክ ተፈትነው ያልተፈፀሙ ንግሮቶች በወቅቱ በተቀባዮቻቸው ዘንድ ችግር ሳይፈጥሩ አልፈዋል ማለት አይቻልም::

ማንኛውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ትንቢት ሁሉ ስህተት መሆኑ በጊዜ፣ በታሪክና በመንፈስ ቅዱስ መስካሪነት ይረጋገጣል:: ስለሆነም የጌታን በአየር መመለስና እርሱን ለመቀበል ስለመንዝ ስናስብ ከተጻፈው ሳናልፍ መሆኑን መዘንጋት የለብንም::

መቼም ጊዜው የአዲስ ኪዳንና የሥልጣኔ ዘመን ስለሆነ ታለፈ እንጂ እንደ ቃሉ ቢሆን እነዚህ ትንቢቶቻቸው ያልተፈጸሙ ተንባዮች በድንጋይ ተወግረው መሞት ነበረባቸው:: ምክንያቱም ብዙ አደጋ ስለ ፈጠሩ ነው::

ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር... እርሱ ይገደል:: ... ነቢዩ የተናገረው ቃል ባይፈጸም ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው:: ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው:: ዘዳ. 18:20-21:: እነዚህ ሰዎች በምዕመኑ ዘንድ ችግር ፈጥረዋል:: ችግርም የፈጠሩት የውዥንብርን መንፈስ ስላመጡ ነው:: መለኮታዊ ነገር በጣም የተከበረ ነው:: የእምነት ጉዳይ ስለሆነ ትንቢት በጉጉት ይጠበቃል፣ ሳይፈፀም ሲቀር ግን ያሰናክላል:: የሚያሰናክለውም፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉትን በእግዚአብሔር ዕውነት ላይ እንዲጠራጠሩ፣ አገልጋዮችን እንዲርቁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችና ነቢያቱ ላይም ጥያቄ እንዲያድርባቸው፣ በማድረግ የጌታ ምፅዐትም ሆነ የቅዱሳን መነጠቅ ስህተት ነው ወደሚል ድምዳሜ እንዲመጡና እምነታቸው እንዲላላ በማድረግና ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉትም ወደ ጌታ ቤት እንዳይመጡ በር በመዝጋት ነው::



ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን በስሙ የሚነሱ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትና ክርስቶሶች ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በማወቅ እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ ማቴ24:25፤ እነሆ በዚህ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፤ አትመኑ በማለት ጠንከር አድርጎ ተናግሮአል:: በዓለም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከጌታ ምፅዐት ጋር በተያያዘ የሀሰት ትንቢት ተናግረው ከፍተኛ ዕልቂት ከፈፀሙት ውስጥ ዋነኞቹ ጂም ጆንስ፣ ዴቪድ ኮሬሽና ጆሴፍ ኪብዌትሪ የማይረሳ ጠባሳ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስቀመጡ ናቸው:: ጂም ጆንስ የዛሬ 30 ዓመት አካባቢ የምፅዐት ቀን ቀርቧል ብሎ በስብከቱ በማስፈራራት በአሜሪካ 914 ሰዎችን ገድሎአል፤ መሲህ ነን ባዩ ዴቪድ ኮሬሽ ኢ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ዋኮ በተባለች የአሜሪካ ከተማ ለ100 ያህል ሰዎች ዕልቂት ምክንያት ሆኖአል::

የጆሴፍ ኪብዌትሪ የፈፀመው የእልቂት ዓይነት በዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያውና አስቃቂው ነው:: ኪብዌትሪ በዩጋንዳ ራሱን በተሳሳተ ሃይማኖት ውስጥ ያስማራና የዓለም ፍጻሜና የአርማጌዶን ጦርነት በዲሴምበር 31,2000 ይሆናል በማለትና ሰዎች ንብረታቸውን እንዲሸጡ ወይም እንዲያወርሱ በማነሳሳት ከ925 በላይ ክርስቲያኖች እንዲያልቁ ያደረገ ነው:: ሚያዝያ 10,2000 የታተመው የታይምስ መጽሔት ከሞቱት ሰዎች ውስጥ 155 ሰዎች በሩጋዚ፣ 153 በድኖች በቡሁንጋ፣ 81 ሰዎች በሩሾጁዋ ተቀብረው እንደተገኙና፣ 530 ሰዎች በካኑንጋ በዚሁ የኑፋቄ ዕምነት ተከታይ በሆኑት ግቢ ውስጥ እንደሞቱና በእሳት ተቃጥለው እንደተገኙ ተዘግቧል::

እነዚህ ሰዎች የፕሮቴስታንት አማኞች ናቸው:: በስመ የፍጻሜ ዘመን አስተምህሮ ግን ሕይወታቸው ያለ አግባብ ጠፍቷል:: ታዲያ የዚህ ዓይነት ዕልቂት እንዲፈፅም አነሳሽ ኃይሉ ማንነው? ተጠያቂው ማንነትስ የት ይገኛል? ይሄ በዮሐ.8:44 እንደተጠቀሰው የሐሰት አባትና ነፍስ ገዳይ የሆነው የዲያብሎስ ሥራ ነው:: ታዲያ ከዚህ ሁሉ አማኝ ውስጥ አንድ እንኳን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ የሚሰማና ለእውነት የሚታዘዝ ወይም ደግሞ ሃይ

የሚል ጠፍቶ ያ ሁሉ ሕዝብ በጎረቤት አገር በዩጋንዳ ያለቀው? የዚህ ዓይነት ታሪክ ነገ ኢትዮጵያ ውስጥ ይደገም ይሆን? ወይስ እኛ የተለየን ስለሆንን ሲያልፍም አይነካን! እንል ይሆን? እንግዲህ « <u>ዛሬ አጥሬን የነቀነቀ ነገ ቤቴን ያፈርሳል</u> » በሚል የአበው ምሳሌ ወገባችን በመታጠቅ መብራታችንን ልናበራ ይገባናል:: የጥንቃቄ ትልቁ ሥራ አማኙን መጠበቁ ላይ ነው:: የጥንቃቄም መሠረት ዕውቀትና ማስተዋል ናቸው::ምሳ2:11:: ማስተዋልንም ያላስከተለ ዕውቀት ከመገልበጥ/ከጥፋት አይታደግም:: ፊልጵ. 1:11፣ ሆሴዕ 4:14::

የጌታ ዳግም ምፅዐትም ሆነ የመነጠቅ ትምህርት እጅግ የሚስብና የሚያነቃቃ ነው:: ቅዱሳን እንፅናናበታለን፣ እንበረታታበታለን: ምክንያቱም የተባረከ ተስፋችን ስለሆነ ነው:: ቲቶ2:11-13:: አንድ ጊዜ መነጠቅ ሕይወት ውስጥ ከተገባ ኃጢአትን፣ መላትን፣ ሥጋዊነትን፣ መከራን፣ የምድሪቱን መርገም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለይቶ መሄድ ነው:: መነጠቅ ወደ ዘላለም ሕይወት መግቢያ ከፍተኛው በር ነው: መነጠቅ ይህንን ያህል የሚባርክና ሕያው ተስፋን የያዘ ከሆነ በማስተዋል ካልተለማመዱት አሉታዊ /Negative/ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል:: 2ተሰ2:2:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች «በቃል፣ በመልዕክት ቢሆን ወይም በመንፈስ የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአዕምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን» ያለው ችግር ስለገጠመው ነበር:: የመነጠቅ ነገር በጥንቃቄ ካላዩት አዕምሮን ያናውጣል::

ቀደም ብሎ ታሪካቸውን በአሉታዊ መልኩ ያነበብነው የመነጠቅ ቀን ናፋቂ አማኞች እዚያ ቀላልና ከባድ አደጋ ውስጥ ሊወድቁ የቻሉት ከዕውቀትና ከማስተዋል ማጣት/ማነስ የተነሳ ነው:: ይህ አሉታዊ ታሪክ እኛ ንም እንዳይደግመን ልናተኩርበት ያሻል:: በተለይም ምልክቶች እየፈጠኑና እየበዙ ሲሄዱ ማስረጃነታቸው ግልጽ ሆኖ እየታየ ሲመጣ ነቃና ረጋ ማለት ያስፈልጋል:: ተማሪ በትምህርቱ፣ ነጋዴ በንግዱ፣ አስተማሪ በማስተማሩ፣



ሁሉም በየስራውና አገልግሎት ዘርፉ በደረሰበት ሊመላለስ እንጂ ሊናወጥ አይገባውም:: /አይገባትም/:: ይህ ትምህርት በተሰጠባቸው በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎችም ክፉ ሊያናውጣቸው የሞከራቸው ወገኖች ነበሩ:: ከማውቃቸው ውስጥ ዋነኞቹ አንድ ወንድም የመነጠቅ ቀን ቀርቧል ብሎ ተው እያልኩት ቤቱን መሸጡ፣ አንድ ሌላ ወንድም ደግሞ እጮኛውን እንደዮሴፍ በስውር ሊተዋት ሲል ጌታ በመገሰጥ መከልከሉ፣ አንድ አካባቢ ደግሞ ክርስቶስ እ.ኤ.አ በ1992 ስለሚመጣ ትምህርት መማር ምን ያደርግላችኋል ተብለው ተማሪዎች መናወጣቸውና የመሳሰሉት ናቸው::

<u>እነዚህ ስህተቶች ሊፈጸሙ የቻሉት አሁን እየተፃፈ ያለውን የማስጠንቀቂያ ትምህርት</u>

<u>በጥንቃቄ አስተውሎ ካለመስማትና በተሳሳተ መንገድ ከመተርጎም የተነሳ ነው::</u>

የትንቢቶችን መፈፀም እያየን የጌታን መቅረብና የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ እንረዳለን እንጂ ቀንንና ሰዓትን ወራትንም በማስላት የአዕምሮን ሚዛን ልናዛባና ልናስለቅቅ አይገባም:: መነጠቅ የሚፈፀመው: ሁለቱ በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፣ ወይም በአንድ እርሻ ያርሳሉ እንደተባለ ሁሉም በየመስኩ ተሠማርቶ ሳለ በድንገት ነው፤በመስካችን ላይ ሆነን ዕምነታችንን ሳንጥል ተግባራችንንም ሳንፈታ፣ ልባችንንም ጌታን እስክንረሳ ክብደት ውስጥ እንዲገባ ሳንፈቅድ ስንኖር የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ከተዘጋጀን እንነጠቃለን:: መንፈሱን ማዳመጥ ከቻልን ሮሜ8:14፣16፣ እርሱ ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል፣ ሊመጣ ያለውንም ያሳስበናል፣ ሐ16:12-13: በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን ጌታ በድንገት መጥቶ ይወስደናል:: ቤቱም ያስገባናል:: ባጭሩ ሕይወታችንን ልንመራ የሚገባን እንዲህ ነው::

ክርስቶስ ሲመጣ፣ የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ሲነሱ እኛም በቅጽበተ ዓይን ከተነሱት ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል ከሚነጠቁት ክፍል እንጂ ከሚቀሩት ክፍል እንዳንሆን ጌታ ፀጋውን

*ያብዛልን:: እውነት የሆነውና ዕውነትን የሰጠን፣ በዕውነቱ እየቀደሰና ወ… እውነት እየመራ በእውነት የሚያኖረን እውነተኛም የሆነው ጌታ ኢየሱ… ቶሎ ይምጣልን::አሜን!!*

## 12.10. ሥራ-ፈት ስለመሆን

ሥራ-ፈት ማለት እግዚአብሔር ለሰው እንዲያከናውነ የሰጠው… ተግባር መልቀቅ ወይም መተው ማለት ነው:: ሰዎች ዓላመዎቻቸው… ተግተው እንዳይፈጽሙ የሚያደረጉዋቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ ተስፋን በተሳሳተ መንገድ መረዳት አንዱ ነው፡፤

ለክርስቲያኖች ከተሰጡን የተባረኩ ተስፋዎች ውሰጥ ዋነኛው የጌታችን የክርስቶሰ ኢየሱሰ ወደ እኛ መምጣትና የእኛም ወደ እርሱ መሰብሰብ ነው:: ጌታን ከምናይባቸው መንገዶች ውስጥም ትልቁ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ነው:: ሆኖም ግን ቀደም ብሰን እንደተመለከትነው ተሰፋን በተሳሳተ መንገድ ተረድተው ችግር የፈጠሩና የተጎዱም እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል:: ለምሳሌ ሰለ መነጠቅ ሰናስብ አንዱ የምነጠቅና ያም የተሻለ ሕይወት ከሆነ ለምን በዚህ ምድር ላይ መከራ እቀበላለሁ፤ ለምንስ ትምህርቴን አጠናለሁ? ምን ያደርግልኛል? ለምንስ ቤት እሰራለሁ? ለምንስ እነግዳለሁ? ጋብቻስ ምን ያደርግልኛል? ቢልና እጁን አጣጥፎ ቢቀመጥና የመነጠቅን ቀን ቢጠብቅ የተባረከውን ታላቅ ተስፋ ለከፋ ጉዳት ሲያደረገው ይችላል:: ስለሆነም የዚህ መልዕክት አንባቢና አድማጭ ሁሉ ስለመነጠቅ ሲያስብ በመጠን መኖርንም ሳይዘነጋ ዓላማንና ተግባርን፤ በምድርም ሊጨብጥ ያሰውን ከመድረስ ወደ ኋላ ሳይል በደረሰበት መመላለስን እንዲቀጥል ደራሲው በጥብቅ ያሳስባል::



## 12.11. ጌታ ይመጣል ወይም አይመጣም፤ መነጠቅ አለ፤ ወይም የለም፤ ብቻ!!

የዚህ የማጠቃለያ ርዕስ ዓላማ ኢየሱስን ተቀብለው መዳናቸውን ላረጋገጡና ወደ ክርስቶስ አካል ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ለወሰኑ ብቻ ነው::

መሀል ሰፋሪነት በጣም አደገኛ ልምምድ ነው:: ይህ ልምምድ እንኳን ከጌታ ይቅርና ከራስም ያርቃል:: ወደ ሰይጣን ማህበርም ይቀላቅላል:: ምክንያቱም መሀል ሰፋሪነት ተጠራጣሪነት ነውና ምንም ዓይነት በረከት ከጌታ አያስገኝም:: በቃሉም የሚጠራጠር ሰው ከጌታ አንዳች ያገኝ ዘንድ አይምሰለው ተብሎ ተጽፎአልና:: ያዕ.1:8:: ወላዋይ ክርስቲያን እንደ ሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ለመተፋት ያዘጋጀ ነው:: ራዕይ 3:15-17:: ወላዋይ ሆኖም ክርስቲያን ነኝ ባይ አማኝ በፈጣሪው የእውነት ቃል ላይ ተጠራጣሪ ተሳዳቢ ነው:: ሰቃሉ ፍርሀትና አክብሮት የለውም፤ ቢኖረውማ ገና ዱሮ በመታዘዝ ይገልጠው ነበር:: ወላዋይ ክርስቲያን ፍሬ ማፍራት አይችልም:: ምክንያቱም ክቡር የሆነው ቃል በዕምነት ስላለተዘራ ለበቅል ስለማይችል ፍሬ ከማፍራት ይልቅ የሚቀርበው ለመቆረጥና ማገዶ ለመሆን ነው::

ወላዋይ ወይም ተጠራጣሪ ክርስቲያን ለእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የጎን ወጊ አጥንት፤ የመቀመጫ ሚስማር፤ የእግር እሾህ፤ናቸው:: እውነተኞች አማኞችንና ጌታን ክርስቶስ ኢየሲስን ሲያሳዝኑ፤ መንፈስ ቅዱስንም ሲያስከፉ ይኖራሉ::

ስለሆነም ክርስቲያን ነን ካላችሁ ሁለት ዓይነት ህይወት አትኑሩ:: ወይ በራድ (ከሀዲና የስይጣን ልጅ) ካልሆነም ትኩስ (አማኝና የእግዚአብሄር ልጅ) ሁኑ:: እንዲህ ከሆነ አቋማችሁ ክርስቶለ ይመጣል! ወይም አይመጣም! ይሆናል:: ይህ ነው ትክክለኛ ክርስትና፤ ይህ ነው ትክክለኛ ዓሰማዊነት!

## ማጠቃለያ

ባለፉት አስራ ሁለት ክፍሎች ስለ መነጠቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊነትና ከመነጠቅም የተለየ ስለመሆኑ፤ስለ መነጠቅ ዓይነቶችና ትዕይንቶች፤ለመነጠቅም መሟላት ስላለባቸው ልምምዶች፤ከታሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማገናዘብ ለማየት ችለናል:: መነጠቅ እውነት ነው:: እውነትም የሚያደርገው ከ6208 የመ/ቅ ትንቢቶች ውስጥ አንዱ ስለሆነና ትንቢትም የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ነው:: መነጠቅን በይበልጥ እውነት የሚያደርገው በታሪክ ያለፉ የሁለት ነቢያት የህይወት ልምምድ ነው:: እነዚህም ነቢያት ሔኖክና ኤልያስ ናቸው:: የነቢያቱን የሕይወት ልምምድ ልዩ የሚያደርገው ሞትን ሳያዩ በእምነት መወሰዳቸው ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው አካሔዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረጉ ነው:: ዘፍ. 5:24፤ 2ኛ ነገ.2:15:: ዕብር. 11:5-6:: የሁለቱም ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀና ጻድቅ በእምነት እንደሚኖር ያለ ኑሮ ነበር::

ማቴ. 17:1-4 ስናነብ በመገለጥ ተራራ ላይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ከታዩት ሁለት ነቢያት ውስጥ አንዱ ኤልያስ ነው:: ሌላውም ሙሴ ነበር:: የሁለቱም በዚያ መገኘት ያለ ዓላማ አይደለም:: ሙሴ የሙታንን የወደፊት ትንሳኤ የሚመለክርና የሚወክል ሲሆን ኤልያስ ደግሞ ሞትን ሳያዩ በሕይወት ሳሉ በቅጽበተ-ዐይን ተለውጠው በእግዚአብሔር መንግስት የሚገኙ -ትን የሚወክል ሆኖ ነው:: በሰማይ የዘላለሙ መንግስት የሚገኙት እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ናቸው:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ አሁን ያለነው ክርስቲያኖች ተለውጠን እንደ ኤልያስና እንደ ሔኖክ ጌታን በአየር ለመቀበል እንነጠቃለን:: በቅርብ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅዱሳን ከዚህ ዓለም በመነጠቅ ይሰወራሉ:: ይህም የሚሆነው በመነጠቅ ስርዐት ምክንያት ነው::



*ኤልያስና ሔኖክ አካሔዳቸውን ከጌታ ጋር አድርገው ወደ ሰማይ እንደተወሰዱ እኛም ለመነጠቅ የሚያስችል የጌታ የዘወትር ፀጋ ከመንፈስ፤ከነፍስና ከስጋችን ጋር ይሁን:: አሜን!!*

አሜን! አሜን የሆነከው ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና!!

## ልዩ ማስታወሻ

1. የቀን አቆጣጠርን በተመለከተ እ.ኢ.አ (እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ካልተባለ በስተቀር በሙሉ እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ነው::
2. የልጆችን መነጠቅ በተመለከተ የግል አመለካከታችንን መያዝ እንችላለን:: በዚህ ጉዳይ የተለያዩ አመለካከቶች ስላሉ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ተጽዕኖ ፈጥሮ መለያትን ማምጣት ዓላማው እንዳይደለ አንባቢ እንዲያተውለው ያሳስባል::
3. ስለ መነጠቅ ጊዜ ሦስት ዓይነት አመለካከቶች መኖራቸውን ስናነብብ የትንቢቱ አፈጻጸም በታሪክ ስለሚገለጥ ብዙ መቸገር አስፈላጊ አይደለም::
4. ጽሑፉ ውስጥ አንዳንድ ቦታ ተባዕት ጾታ ላይ ያተኮረ ቢመስል ለውን ባጠቃላይ ለመጥቀስ ስለተፈለገ እንጂ ልዩነትን ለመፍጠር እንዳልታሰበ ልብ ይባል::

## ሙዳየ-ቃላት

**ሀሰተኛው ክርስቶስ** እኔ እግዚአብሔር ነኝ እያለ (2ኛ ተሰ.2:4) የሚሳደበውና ትንሹ ቀንድ

እንቆቅልሽ ፊቺ፡ የአመፅ ሰው፡ የጥፋት ልጅና አውሬው፡ ተቃዋሚና ባለ

666ቱ በመባል የሚታወቀው የእውነተኛይቱ ቤተ/ክ ራስና ጌታ የሆነው

የክርስቶስ ተቃዋሚ፤ በስጋ የተገለጠው ሠይጣን ነው።

**ሁነት** የነገሮች ትዕይንት፤አፈጻጸምና አደራረግ

**ህያው አማኝ** ወንጌል ተሰብኮለት ጌታን በመቀበል ሐጢአቱ በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰርዮለት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን አግኝቶ አባ አባ በማለት ዘወትር የሚጸልይ፤ቃሉንም ሁልጊዜ የሚያጠናና ጠንካራ የሕይወት ትጋት ኖሮት ሌሎችንም እያተጋ የዘላለምን ሕይወት ያለማቋም የሚናፍቅ ክርስቲያን።

**ልብሰ-ሰብዕና** በውጪአዊ መልክ የሚታይ የሰው የህይወት ልምምድ፤ ምናልባትም ይህ ሰብዕና ከውስጣዊውና ዕውን ከሆነው ሰብዕና ጋር ተቃራኒ ወይም ተመመሳሳይ ሊሆን ይችላል፤ ትክክለኛውን ሕይወት የሚሸፍን ውጪአዊ የሕይወት እንቅስቃሴ ነው።

**ልዕለ-ተፈጥሯዊ** ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማናቸውም ዓይነት ሥራ፤ ለምሳሌ በአማኞች ሕይወት የሚታይ እንደ ተአምራት፡ ድንቆችና በሰው የማይደረጉ ምልክቶች።



**ሎጥ ዘመን (የ)** የሰዶምና የገሞራ ምድር ሰዎች አካሄድ የተበላሸበትና እንደ ግብረ-ሰዶም ዓይነት የሐጢአት ልምምዶች የተካሔዱበት ጊዜ ሆኖ እግዚአብሔር ሰውን በእሳትም ዲን ዝናም ያጠፋበት ጊዜ።

**መሰወጥ** በግሪክ አላሥ ሲሆን ትርጉሙ ወደ ሌላ ዓይነት መልክ መቀየር፤ሌላ መልክ መያዝ ማለት ነው።

**መረግድ** አረንጓዴ ቀለም ያነውና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው የከበሩ የመሰረት ድንጋዮች ውስጥ አንዱ፤

**መረፈቅ** መቀመጥ፤ ማረፍ፤ መወዘፍ፤ መረፈቅ ይህ እንደ ባህሉ አሉታዊ ትርጉምም አለው።

**መቶ አርባ (144000)** አይሁዶች፡ ወንድ ልጅ በመባል የሚጠሩና በመከራው አጋማሽ ላይ አራት ሺ አውሬውን ለመቃወም ሲነሱና አውሬውም ሲቃወማቸው ሲል በመከራው አጋማሽ ላይ ወደ ሰማይ የሚነጠቁ አይሁዶች።

**መንፈሳዊ ርቀት** አንድ አማኝ ሳያውቀው የቆመ መስሎት የውስጥ ሕይወቱ እየተሸረሸረ የሚሄድበትና ፈጣሪውን ከማምለክና ከትክክለኛው መንፈሳዊነት የሚለይበት አሉታዊ ልምምድ ነው። ለምሳሌ በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? ተአምራትስ አሳደረግንምን? ትንቢትስ አልተናገርንምን? ሲሉ ከቶም አላወቅኋችሁም እንደተባሉ።

**መንፈስ-በኩራት(የ)** ሰው በሐጢአት ምክንያት ሞቶ የነበረው መንፈሱ ጌታን ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዳግም ልደትን ሲያገኝና መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን ሲቀበል የሰው መንፈስ የሚያገኘው ትንሣኤ፤

**መከራው ዘመን (የ)**
የ 9.2 ን አጭር ማብራሪያ ይመልከቱ::

**መንፈቀ-መከራ**
የመከራው ግማሽ (5.2 ይመ.)::

**ሚስት (የበጉ)**
የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን፤ 144000 አይሁዶች፤የመከራውን ዘመን ቤተ ክርስቲያንና ሁለቱንም ነቢያት ጨምሮ ከትንሣኤና ከመነጠቅ ቀጥሎ በሰማይ በበጉ በክርስቶስ ሠርግ ላይ የሚገኙ ቅዱሳን የሚጠሩበት መጠሪያ ስም:: ይህ እስራኤልን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚያመለክት አይደለም::

**ማሴሰን (ሴሰኛ)**
አንድ አማኝ ንፁህ መንፈሳዊ ህይወትን እንዳይለማመድ ዓለማዊ ኑሮን ደባልቆ እንዲይዝና በመዳራት እንዲመላለስ የሚደረግ ዘዴ:: ለምሳሌ የራዕይ 2 የትያጥሮኗ ኤልዛቤል የጌታን ባሪያዎች ታሴስን እንደነበር ማለት ነው::

**ሞት ለዘላለም ተዋጠ**
ሞት በቅድሚያ በክርስቶስ ቀጥሎም በቅዱሳን ትንሣኤ ሰዎችን ይዞ የማስቀረት ሐይሉ ተወስዶ ባዶውን የቀረበት ወይም የሞትና የሲኦል መክፈቻ የተወሰደበትና የተሸነፈበት ጊዜና ሁኔታ::

**ሠርግ**
በ70ኛው ሱባኤ ማብቂያ ላይ የበጉ ሚስት አባላት (5ቱ የተነጠቁ ክፍሎች) በሰማይ ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው ከሰማይ ሰራዊት ጋር ሐሴት የሚያደርጉበትና የክርስቶስንም መንገስ አዋጅ የሚሰሙበት፤ ወደ ምድርም ለመመለስ የሚዘጋጁበት ሁኔታ (ራዕይ 19:4-10):

**ስመ የፍጻሜ ዘመን**
የትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊና መን/ቅዱሳዊ ወይም ቤተ ክርስቲያናዊ



**ተምህሮ**
ሳይሆን የዚህ ዓለም ፍጻሜ ደርሷል በሚል ሰበብ ሰዎችን የሚያጠፉበት እንቅስቃሴ ነው:: ለምሳሌ ጂም ጆንስ 914 ሰዎችን የጨረሰው፤ ዴቪድ ኮሬሽ 112 ሰዎችን የፈጀው፤ ጆሴፍ ኪብዌትሪና ሚስቱ ከ925 በላይ ሰዎችን ያስገደሉት በስመ ዘመነ ፍጻሜ መቅረብ አዕምሮን በማናወጥ ነው::

**ባው ሱባዔ**
ሱባዔ ማለት ሻቡዓ ከሚል የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሰባት ወይም ሳምንት ማለት ነው:: ስለ ሱባዔ በትንቢት መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው በዳን. 9:24-29 ባለው ክፍል ነው:: ሰባው ሱባዔ ማለት ሰባ ሰባቶች ወይም 70x7=490 ዓመታት ማለት ነው:: እነዚህም 490 ዓመታት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርጉት በደል፤ሐጢአትና መተላለፍ ሁሉ ተወግዶ፤ ስለ እነርሱም የተነገረው ትንቢትና የታየውም ራዕይ የሚፈጸምበትን እንዲሁም እነርሱ ወደ ዘላለም ቅድስናና ፅድቅ የሚገቡበትን ጊዜና ሁኔታ የሚያመለክት ነው::

**ሰባኛው ሱባዔ**
ይህ ከተነገሩት ሰባ ሱባዔዎች ውስጥ የመጨረሻውን ሰባት ዓመታት የሚይዝ ነው::በተነገው ትንቢት መስረት እስራዔላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ዕርቅ ማድረግ የነበረባቸው መሲሁ በተገደለ ጊዜ ከ34 እስከ 40 ዓመተ ምህረት ነበር:: የቤተ መቅደሱ ንጽህናና የአምልኮአቸው ትክክለኛነት እስከተጠበቀ ድረስ የሱባዔው አቆጣጠር ይሰራ ነበር፤ ሆኖም ግን በ34 ዓመተ ምህረት ማለትም በ69ነኛው ሱባዔ መሲሁን ሲገድሉ የሱባዔው አቆጣጠር ለጊዜው አቆመ:: ምክንያቱም ከእግዚአብሄር ጋር ስለተጣሉና የቤተ መቅደሱም አምልኮ ስላቆመ ነው::

ስለሆነም ሰባኛው ሱባዔ እስካሁን አልተፈጸመም:: ሆኖም ሰባኛው ሱበዔ የሚጀምረው በነቢዩ ዳንዔል እንደተነገረው እስራዔል አውሬው ክርስቶስ እውነተኛ ው መሲህ መስሏት ልትቀበለው ለአንድ ሱባዔ ውል በምታደርግበት ጊዜ ይሆናል:: ዳን. 9:27:: ይህ ጊዜ በራዕይ 12 እንደተተነበየው እስራኤል እንደገና በአውሬው የምትቸገርበትና ወደ በረሃ የምትሸሽበት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልሆነ ታላቅ የመከራ ጊዜ ነው:: ማቴ. 24:21-22፤ ሉቃስ 21:36:: ይህም የያዕቆብ የመከራ ዘመን የሚባለው ነው:: ይህ የመከራ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ በመላዕክቱና በሚስቱ ከሰማይ መውረድ ምክንያት አውሬውና ጭፍራዎቹ የሰማይን ሰራዊቶች ሊወጉ በሚከፍቱት በአርማጌዶን በሚጀመረው የፍጻሜ ጦርነት በክርስቶስ ኢየሱስ አሸናፊነት የሚጠቃልል ይሆናል::

**ሰርድዮን** — እንደ ደም በጣም ቀይ የሆነ ቀለም ያለውና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው ክቡረ ዕንቁዎች ውስጥ አንዱ ነው::

**ሰርዶንክስ** — ውኅ ሰማያዊና እንደ ደም በጣም ቀይ ሆነ ቅልቅል ቀለም ያለው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው ክቡር ድንጋዮች ውስጥ አንዱ ነው::

**ሰንፔር** — ከአልማዝ ቀጥሎ በጣም ጠንካራ የሆነና ሰማያዊ መልክ ያለው ሰማያዊቱ አየሩሳሌም ከተሰራችባቸው የከበሩ ዕንቁዎች ውስጥ አንዱ::

**(የ)ሰው ልጅ ዘመን** — ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ሦስት የእግዚአብሔር ቁጣዎች የሚገለጡባቸው ዘመናት ተጠቅሰዋል:: እነርሱም የኖህ፡ የሎጥና የሰው ልጅ ዘመናት ናቸው:: ሉቃስ 17:26-30:: የሰው ልጅ ዘመን



የጀመረው ክርስቶስ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ነው:: ሉቃስ በትንቢቱ ልክ ኖህና በሎጥ ዘመን እንደነበረ በሰው ልጅ ዘመንም እንዲሁ ይሆናል ብሉአል:: ስለሆነም ከጌታ ልደት ጀምሮ እስካሁንና እስከ ሺሁ ዓመት ፍፃሜ ያለው ጊዜ የሰው ልጅ ዘመን ይሆናል ማለት ነው:: የሰው ልጅ ዘመን ከሚታወቅባቸው ባህርያት ውስጥ ትልቁ የሰዎች ሐጢአት እጅግ ማየሉ ነው:: ትልቁ የሐጢአት መግለጫ ማለትም ሰው አምላክ ነው የሚባልበትና ሰዎች ወደማይስረይ የሐጢአት ልምምድ ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው:: ማቴ.24:36-39፤2ኛ ተሰ.2:4::

**ሲኦል** — ከመጀመሪያው ሐጢአተኛ ከሞተ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሐጢአተኛትንሳዔ የሚኖሩ ሐጢአተኞች እስከ ታላቁ ፍርድ ድረስ መንፈሳቸው የሚጠበቅበት ስፍራ::

**ሳይንሳዊ ፊክሽን** — በወቅቱ ሲታይና ሲሰማ ልብ ወለድ ሆኖ ከተወሰኑ ጊዜአት በኋላ ግን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በእርግጠኛነት መልኩ በታሪክ ሊገለጥ የሚችል በሐሳብ ደረጃ ያለ ጽሑፍ ወይም ንግግር:: በተመሳሳይ መልኩ ክርስቲያን ፊክሽንም አለ::

**ሺህ ሁለት መቶ** — አውሬው ከእስራኤል ጋር የሰባት ዓመት መከራ ውል አድረጎ

**ስድሳ(1260) ቀናት** — በመከራው አጋማሽ እስራኤልን ሲያሳድድ ከፊሉ ሕዝብ ወደ ሌላ ስፍራ የሚሰደድበትና የሚቆይበት ቀናት ቁጥር ነው:: እነዚህ ቀናት ከ42 ወራት (30 ቀናትx42=1260); ከዘመን ዘመናትና የዘመን እኩሌታ

ወይም ከ 3 ተኩል ዓመታት ጋር እኩል የሆነ ጊዜ ነው::

**የሺህ ዓመት** ከሰባኛው ሱባዔና ከአርማጌዶን ጦርነት ቀጥሎ በምድር ላይ በግልጽ

**መንግስት** ለዓለም መንግስታት እየታወቀ የሚፈጸም ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር የሚገዛበትና የሚያስተዳድርበት ዘመን::

**ሽማግሌዎች (24ቱ)** በቅድመ መከራ መነጠቅ በዘመናት ያለፉ ቅዱሳንን ወክለው በሰማይ በእግዚአብሔርና በዙፋኑ ዙሪያ ባሉት 24 ዙፋኖች ላይ የሚቀመጡ የዳኑ ቅዱሳን፤ ምናልባትም ከብሉይና ከኪዳን የሚወከሉ የካህናት አገልጋዮች ቁጥርም ሊሆን ይችላል::

**ቅጽበተ-ዐይን** እጅግ በጣም ፈጣንና በአዕምሮ ለማስላት የሚያስቸግር ፍጥነትና መለኮታዊነት ያለው ትዕይንታዊ እንቅስቃሴ::

**ቅድመ-መከራ** ከታላቁ መከራ በፊት ማለት ነው::

**በቁም መንፈሱ የሞተ፤** ሐጢአቱ ያልነጻና ጌታን ያልተቀበለ ሆኖም ግን አማኝ ነኝ የሚል::

**ቢረሌ** አንጸባራቂና ውኀ-አረንጓዴ ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሰረቶች ከተሰሩባቸው አስራ ሁለት ዓይነት ድንጋዮችአንዱ::

**ትንሣዔ** የሰው አካል ከሞተና ከተቀበረ በኋላ በመለኮታዊ አሰራር የማይጠፋውን: የማያረጀውን: የማይበሰብሰውንና ያልተዋረደውን አካል ለብሶ ሞትን ድል አድርጎ የሚነሳበት ሁኔታ::

**ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ** ማብራሪያ 5.3.3 ይመልከቱ::



**(የ)ኖህ ዘመን** በዘፍጥረት 6 እንደምናነብበው የሰው ልጅ ሐጢአት እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ሰዎች ሁሉ መንገዳቸውን ያነሳሹበትና ከኖህና ከቤተሰቡ በስተቀር ሁሉም ሰዎች በጥፋት ውኃ የጠፉበት ጊዜ ነው::

**አቡቀለምሲስ** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትዕምርቶችን (መልክቶችንና ምስሎችን) በማቅረብ በራዕይ፤ በህልምና በሌላም መልክ የሚገለፅ መልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ::

**አምቡዋታሪ** ወሬ አናፋሽ: ተናጋሪ ስራ ፈት: አዘጥዛጭ::

**አቤሴሎማዊ ወ** *አፉ ቅቤ ልቡ ጩቤ* እንደሚባለው ልክ አምኖን እህቱን ትዕማርን

**አምኖናዊ ሰብዕና** አሞኛል ብሎ እንዳመነዘራት፤ አቤሴሎምም አባቱን ዳዊትንና ወንድሙን አምኖንን የከበረ በሚመስል ሰላምታና ግብዣ አታልሎ የመፈንቅለ መንግስትና የሞት አደጋ እንዳደረሱ ልክ በተመሳሳይ መልኩ በመልካም አስመስለው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳት የሚያመጡ የግለሰቦችና የቡድኖች አካሔድ የሚጠራበት መለያ ነው::

**አመክንዮ** የማውጠንጠን ችሎታ: ምክንያት የመፍጠርና የማቅረብ ችሎታ::

**(የ)አመፅ ምስጢር** ፊት ለፊት ወይም በስውር ነገር ገሐድ ሳይወጣና ሳይታወቅ የሚደረግ የተቀውሞ አካሔድ፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ በአመዛኙ የአውሬውን ጥልቅ አሰራር ያመለክታል:: ከቤተ ክርስቲያን መመስረት ጀምሮ እስከ መነጠቅ ድረስ በስውር ይሰራ የነበረውን ተቃውሞ ከመነጠቅ ቀጥሎ የሚቀወመው ስለማይኖር በግልጽ መስራት ይጀምራል::

**አንጻራዊ ሥነምግባር** — ፍጹም የሆነ ሥነ ምግባር የለም:: ሥነምግባር እንደየባህሉና እንደየአገሩ ሊለያይ ይችላል:: በአንዱ ሕብረተሰብ ተቀባይነት ያለው በሌላው ተቀባይነት ላይኖረው ስለሚችል ሥነምግባር ፍጹማዊነት ሊኖረው አይችልም የሚል አመለካከት ነው::

**አንጻራዊ ዕውነት** — እውነት ፈጹማዊነት የለውም:: እውነት እንደየባህሉና አገሩ ይለያያል::

**አሜቴስጢኖስ** — ደማቅ ሰማያዊና ደማቅ ቀይ ቀለም ያለው ከ12ቱ የሰማይቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ውስጥ አንደኛው መሰረት የተሰራበት የከበረ ድንጋይ::

**አምናዊ-ድህረ መከራ መነጠቅ** — ማብራሪያ 5.3.1. ይመልከቱ::

**የአርማጌዶን ጦርነት** — ክርስቶስ ኢየሱስ በሰማይ የበጉን ሠርግ ሥርዐት ከፈጸመ በኋላ ከተነጠቁ ቅዱሳን ጋር አውሬውንና ጭፍራዎቹን በጽድቅ ተዋግቶ ድል የሚያደርግበት ሁኔታ ራዕይ 19:14-21::

**አውሬው** — በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ 15 ስሞች ያሉትና የቀንድ ስሙ ትንሹ ቀንድ: የችግር አስወጋጅ ስሙ ዕንቆቅልሽ ፈቺ: የማሳሳት ስሙ ሐሰተኛው ክርስቶስ: የንጉስ ስሙ ፊተ ጨካኝ ንጉስ: የቁጥር ስሙ 666: የሰው ስሙ አመጸኛ: የእንስሳ ስሙ አውሬው በመባል የሚታወቀው የፅድቅ ጠላት::

**አዲሱ አካል** — ጌታን አምነው ከሞት የሚነሱ ቅዱሳን የሚለብሱት የማይጠፉ: የማያረጅ: የማይበሰብስና የማይጠፋ እንዲሁም ሐጢአት መስራትና መውደቅ የማይችለው ዘላለማዊ የሰው መንፈሳዊ አካል ነው::

**አጥንት-አንቃዥ** — መንፈሳዊ ወኔን በመስለብ ማንነትን ለሐዘን የሚገልጥና የሚጎዳ ሁኔታ::



**አጸደ-ሥጋ** — አሁን በመንፈስ በነፍስና በስጋ ሁኔታ ያለው ያልሞተው ማንነታችን::

**ቤተክርስቲያን** — ወንጌል ተሰብኮላቸውና የክርስቶስን አዳኝነት አምነውና ተቀብለው በክርስቶስ ደም አማካኝነት የሐጢአትን ስርየት አግኝተው ስማቸውም በህይወት መዝገብ ተጽፎ በመንፈስ ቅዱስ መታተም አማካኝነት የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን ያገኙ ምዕመናን::

**እግዚአብሔር-ሞቷል አስተምህሮ:** — በእነርሱ ጊዜና ሁኔታ የፈለጉት እግዚአብሔር ስላልተገለጠ በፈጣሪ ትዕግስትና ታጋሽነት ላይ በማሾፍ እግዚአብሔር ሞቷል በማለት ተናገሩትን የፍሬድሪክ ኒቼንና የተከታዮቹን ተሳዳቢ ሥነ መስኮት የሚያመለክት ነው::

**ከፊል አምናዊ-ድህረ መነጠቅ መከራ** — ማብራሪያ 5.3.2. ይመልከቱ

**ኬልቄዶን** — ውሀ ሰማያዊ:ደብዘዝ ያለ ነጭ:ጥቁር ቡናማና በጣም ቀይና ቢጫ የሆነ አራት ዓይነት ሕብረ-ቀለማትን የያዘ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተሰራችባቸው አንጸባራቂ የከበረ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ::

**ክሪስቲሎቤ** — አረንጓዴ:ቢጫና ወርቅማ ዓይነት ኅብረቀለም ያለው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ከተሰራችባቸው በጣም የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ:

**ክርስጵራስስ** — ቢጫ: አረንጓዴና ሰማያዊ ዓይነት ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም

ደጆች ከተሰሩባት የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ::

**ወራውሬ** ፈዘዝ ያለና አረንጓዴና ቢጫ ዓይነት ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሰረቶች ከተሰራችባቸው የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ::

**ወንድ ልጅ** (ማብራሪያ 4.3.4. ይመልከቱ):: ባጭሩ ኢሳ. 66:7-8 እና ራዕይ 12:4-5 በማነጻጸር ሲፈታ ወንድ ልጅ የተባለው በቀጥታ የሚያመለክተው በመከራው ዘመን አውሬውን ለመፋለም ግምባራቸውን ታትመው የሚነሱ አይሁዳዊ የሆኑ 144000 የእግዚአብሔር ባሪያዎች ናቸው እንጂ ወንዱ ልጅ ኢየሱስን የሚያመለክት አይደለም::

**ወንዶችና ሴቶች** ሁለቱንም ጾታ የያዙ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔርን ልጅነት

**ባሪያዎች:** ሥልጣን ተቀብለውና መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ጌታን የሚያገለግሉ ቅዱሳን::

**(የ)ውሸተኞች** ከአጋንንት ረቂቅና ግልጽ የትምህርት ተጽዕኖ የተነሳ አዕምሮአቸው ደንዝዞ

**ግብዝነት** ዕውነተኛውን ህይወት ትተው በማስመሰል የሚኖሩ አማኝ ነኝ ባዮች::

**ዕውን-ሰብዕና** የልበሰ ሰብዕና ተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ሊሆን የሚችል ሆኖም የሰውን ትክክለኛ የውስጥ ማንነት የሚወክል የሰው የህይወት አቋም::

**ዘላለማዊ ዕድቅ** በክርስቶስ ያመኑ የሰው ዘሮች ሁሉ ወደፊት የሚገቡበትና የሚኖሩበት ሐጢአት የማይሰራበት ሁልጊዜ ልክ ሆነት ሕይወት::



**ዘመን መጣ** በራዕይ 9:15 እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ምድርን የሚያጠፉትን ለመቅጣትና ፈቃዱንና ዓላማውን ለመፈጸም የሚነሳበትን ሰዓት: ቀን:ወርና ዓመት የሚያመለክት::

**ዘውታሪ** ሁሌ አሳቢና አድራጊ::

**ያክንት** ቀይና ቢጫ ዓይነት መልክ ያለው የሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ከተገነቡባቸው የከበሩ ደንጊያዎች ውስጥ አንዱ::

**ድህረ-መከራ መነጠቅ** መነጠቅ ከመከራው ቀጥሎ እንደሚሆን የሚደግፍ ሐሳብ 5.3 ይመ.

**ድነት** ሐጢአትን በማወቅ በመናዘዝና በመራቅ ክርስቶስንም በማመን የሚገኝ የዘላለም ሕይወት::

**ገነት** ጻድቃን ሰዎች ከሞቱ በኋላ መንፈሳቸው እስከ ትንሳኤ ድረስ የሚቆይበት ከምድር በታችና በላይ ያለ ስፍራ:: ገነት አራት ዓይነት ሊሆን ይችላል: ይኸውም የንጋት ኮከብ የነበረው ሰይጣን ይኖርበትና ይገዛበት የነበረው ሕዝ. 28፤ቀጥሎ አዳምና ሔዋን ይኖሩበት የነበረው ዘፍ.3፤የአብርሐም ዕቅፍ በመባል የሚጠራው ሉቃስ 22፤ (አሁን ወና የሆነው ገነትና) በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ሲሞቱ መንፈሳቸው እስከ ትንሳዔ የሚቆይበት ሰማያዊ ስፍራ ዕብር. 12:23-26::

**ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን:** መለያቸው ገንዘብ ወዳድነት የሆነ: የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን የሚሉና (ዮሐ.16:1)፤ የአምልኮት መልክ ኖሮአቸው የፈጣሪን ሐይል የካዱ 2ኛጢሞ.3:5፤ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በግልፅ የሚናገሩ (ቲቶ 1:16) ከልዩ ልዩ ቤተ ዕምነቶች የተውጣጡና

| | |
|---|---|
| | በመጨረሻው ዘመን አውሬውን ተከተለው የሚነሱና የነቢያትን ደም በማፍሰስ የሚጠጡ አስመሳዮች:: ራዕይ 17:5-6፤18:24:: |
| ጥንተ-አብሶ | ከጥንት ከመሰረቱ ክሰው ዘር ሲወራረስ የመጣ የሐጢአት እርሾ:: |
| (የ)ጻድቃን-መንፈሶች ጉባዔ | እስከ ትንሳዔ በገነት የሚቆዩ ቅዱሳን አማኞች:: |
| ፊቱ መቆም | ክርስቶስ ኢየሱስ በታላቅ ክብርና ግርማ ሲገለጥና ሲመጣ የዓለም መንግሥታትና ጭፍራዎቻቸው በጌታ ቁጣ ፊት መቆም ተስኗቸው_የሚያሳዩትን መንቀጥቀጥና መሸሸ የሚያመለክት እንዲሁም በእርሱ ያመኑት በክብርና በነፃነት ሲቀበሉት የሚያሳይ ትዕይንት ነው:: |



## ምህጻረ-ቃላት

1. ሐ(ዋ)ሥ.= ሐዋርያት ሥራ ቲዎሎጂካል ኮሌጅ
2. መ.ቅ.= መጽሐፍ ቅዱስ
3. መን.ቅ.= መንፈስ ቅዱስ አውሮፓውያን አቆጣጠር
4. ሙ.ቃ.ይ.= ሙዳየ ቃላት
5. ኢ.ቲ.ሲ.=ኢቫንጀሊካል
6. ይመ.= ይመልከቱ
7. እ.ኤ.አ.= እንደ
8. እ.ኢ.አ.= እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ይመልከቱ:

## መዘክረ መጻህፍት


1. Demy, Timothy & lce, Thomas. Fast Facts on Bible Prophecy. Eugere, Oregon: Harvest House Publishers.
2. Dobson, Ed.(1997). Remarkable Events Pointing To The End. Grand Rapids, Michigon: Zondervan Pub. House.
3. Erickson, Millard J. (1977) . Contemporary Options in Eschatology. Grand Rapids, Michigan: Baker Book House.
4. Jennings Dake. (1963) . Dake's Annotated Reference Bible. Lawrenceville, Georgia: Dake Bible Sales Inc.
5 Froese, Arno. (1997). How Democracy Will Elect The Anti-Christ. Colombia, Sc: Olive Press Publishers.
6. Hindson, Ed. (2001). Understanding the End Times. Lyncburg: Jerry Fallwell Ministries.
7. Hunt,Dave & Mcmahon. (1985). The Seduction of Christianity. *Spiritua Discernment in the Last Days*. Eagene, Oregon: Harvest House Publishers.

8. Lahaye, Tim. (1972). The Beginning of the End. Wheaton, Illinois: Tyndale House Publishers.

9. Lugt, Herbert Vander. (1983). There is a New Day Coming. Grand Rapids, Michigan: Radio Bible Class.

10. Malgo, Wim. 50 Questions Most Frequently Asked About the Second Coming. Columbia, South Carolina: Midnight Call Inc.

11. Staton, Lewis Dr. (1988). The Final 42 Months. N. Carolina.

12. Walvoord, John F./1990/ Armageddon Oil and Middle East Crisis. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House.

13. Zeller, John/Dr/. (1968) . The Second Coming of Ages. Michigan: New Era.

14. ኦሌ ኤሪክሰን. (1965) የአንድ አራሽ ንግግር. አዲስ አበባ ኢትዮጵያ: ሴንትራል ማተሚያ ቤት::


## መጽሔቶች


15. Midnight Call. Sept.1992. pp.9-10.

16. Midnight Call. June. 1995. pp. 8-13.

17. Midnight Call. Sept. 1995. pp. 7-8.

18. Midnight Call. Feb. 1995. p. 18.

19. Midnight Call. July. 1995. p.28

20. Time Magazine, April 10,2000 pp.28-29.


——————//////////////——————



*ፍካሬ 666ትን* አዘጋጅተው በማስነበብ *ዘመኑን እንቃኝ ያሉን መጋቢ* ኮ ከበደ አሁን ደግሞ ለመነጠቅ ተዘጋጁ ሰዓቱ አልቋል ይሉናል:: የዘመን ተላ ላይ የደረስነው እኛ ከዘመኑ ጋር አብረን እንዳናልቅ ወደ ተዘጋጀልን ፍራ ለመሄድ የግድ በተጠንቀቅ መኖር አለብን:: ስለዚህ ደግሞ ይህች መጽሐፍ ትረዳናለችና እናንብባት::

*መጋቢ አበበ ሥዩም: የምሥራቅ አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ::*

ይህ መጽሐፍ ብዙ የሚያጽናና የሚያበረታታና ወደ ሰማይ መነጠቅን እጅግ የሚያስናፍቅ ነው:: መቼም በመነጠቅ እውነት ውስጥ መኖርና መመላለስ ታላቅ በረከትና ተስፋ ያለው ሕይወት ነው::ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ሰው ሁሉ ስለ ተመኘ በቻ ተነጥቆ ወደዚህ ሰማያዊ ተስፋ አይገባም:: በእግዚአብሔርም አይወሰድም:: ጽሑፉ የእያንዳንዳችንን ሕይወት የሚነካና በሚያነብበው ሰው ላይ ወደደም ጠላ በህይወቱና በአመለካከቱ ላይ ታላቅ በጎ ተጽዕኖን የሚያሳድር ነው:: በከፍተኛ ሁኔታ የየግልና የጋራ ሕይወታችንን ቻሌንጅ የሚያደርግ ነው:: ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሔኖክም ሞትን እንዳያይ በዕምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም፤(ዕብር.11:5) እንዲሁም በ1ኛ ዮሐ. 3:3 በእርሱም ይህንን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደሆነ ራሱን ያነጻል እንደሚል፤ አንባቢ ሆይ! ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ በጌታ ኢየሱስ አምኖ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነና ዕለት ዕለት በጌታ ኢየሱስ ደም ከሐጢአት እየነጻ በቅድስናና በሕይወት ንጽህና የሚኖር ብቻ ነው:: እያንዳንዳችን በዚህ እውነት ራሳችንን እንፈትን ዘንድ ይህንን ጽሑፍ ያቀረበልንን ወንድማችንን መጋቢ ተኩ ከበደን ጌታ አምላካችን አብዝቶ ይባርከው! አሜን::

ዶክተር ፍሬው ተገኔ:
ደቡብ አ.አ መሠረተ ክ/ቤተ ክርስቲያን

የቅዱሳን በአየር መነጠቅ በአጠቃላይ የነገረ ፍጻሜ ትምህርት የቤተ ክርስቲያን መድረክ እየተነፈጋቸው ካሉ ትምህርቶች መካከል የሚገኙ በመሆናቸው ይህ መጽሐፍ የረሳነውንና የተውነውን ትምህርት እንድናስታውስ የሚያነቃ ደወል ነው:: በነገረ-ፍጻሜ ዙሪያ ያሉትን የተለያዩ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች በመጽሐፉ ውስጥ በመጠቀሳቸው አንባቢያን የራሳቸውን አመለካከት እንዲያዳብሩ በር ከመክፈቱም በላይ ለተጨማሪ መረጃ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዲያጠኑ ስሜትን ይኮረኩራል:: የቅዱሳን መነጠቅ የዕምነታችን አንኳር ክፍል እንደመሆኑ በዚህ አንጻር መጽሐፉ ቁም ነገሮችን ያስጨብጣል:: በዚህ በመጨረሻ ዘመን የመነጠቁ ባርኮት ተካፋዮች እንድንሆን ከተሳሳተ ልምምድና አስተሳሰብም እንድንርቅ ጸሀፊው የሚያስተምሩትንና የሚመክሩትን ልብ ብለን ልናጤነው ይገባል::

ኢንጂነር ደሳለኝ አበበ

በኢትዮጵያ ገነት ቤተ ክርስቲያን የካራቆሬ ገነት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ: